ስለ ጤና - ከ«ቡልቡል» አዲስ አበባ...
ገጽ 24

የአዕምሮን ጦርነት ማሸነፍ
ገጽ 12

ለሴቶች ጤና የቆመው «ሔዋን»
ገጽ 20

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 236 ሚያዝያ 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# የኤሌክትሪክ መኪኖች ፋይዳ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

የትራንስፖርት አገልግሎት ከሌሎች የአገልግሎት ዘርፎች ቀዳሚውና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየሰፋና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዘመነ የመጣ ነው። ዘርፉ ለምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት መሠረታዊ ሚና ይጫወታል። የሰዎች እንቅስቃሴ፣ ንግድ፣ የሰው ልጆችን ከአደጋ መታደግ ዕድገትና ሥልጣኔን ከትራንስፖርት አገልግሎት ውጪ ማሰብ ይከብዳል።

ሰውና እቃን በጋማ ከብት ከማጓጓዝ አንስቶ በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችንም አልፎ የትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ዛሬ ላይ በአደጉ ሀገራት ዘንድ፣ ሰው ሳያሻቸው በራሳቸው የሚንቀሳቀሱ፣ በኤሌክትሪክ ገመድ ላይ የሚጓዙ፣ በተጨናነቀ የትራፊክ እንቅስቃሴ መካከል አልፈው መሄድ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን ማምረትና ሥራ ላይ ማዋል ተችሏል።

የኤሌክትሪክ መኪኖች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## የፋሲካ በዓል ግብይት

ማርቆስ በላይ

የበዓል ገበያ ከወትሮው በተለየ በገዥም፣ በሻጭም፣ በአሻሻጭም ይደምቃል፡፡ በሠንጋና በሙክት፣ በዶሮና በዕንቁላል፣ በአጠቃላይ በዓሉን በዓል በዓል በሚያስመስሉ ነገሮች ሁሉ ገበያው ይደራል፣ ይጨናነቃል፡፡ ገበሬና ነጋዴው ሰንጋ በሬውን በግና ፍየሉን፣ እንዲሁም ጤፍና ቅቤውን ወደ ገበያ አውጥቶ የሚሸጠው በበዓላት ወቅት ነው፡፡

በሾላ በግ ተራ ገበያ ደህና ሙክት

ስትንሳኤ በዓልና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ከበጋ መስኖ ስንዴ ከ82 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰበሰበ

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- ከ2016 የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እስካሁን ከ82 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት መሰብሰቡን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ

ከበጋ መስኖ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ትንሳዔ እርቅና ሰላምን ተግቶ የመፈለግ አርዓያ ነው

ሄለን ወንድምነው
ዜና ሀተታ

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ለመግለጽ ሲል የሕይወት ዋጋን ከፍሏል። የሰው ልጅን ወደ ሰው ልጆች ለማቅረብ ሳይገባው እንደተገባው ሆኖ መከራን ተቀብሏል። እስከ መሰቀልም ደርሷል። በሰሞነ ህማማት ሳምንት የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ እያንዳንዱ ቀን የሚታሰብበት የራሱ ታሪክ አለው።

በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩ ግጭቶችን በመፍታት ይቅር ለመባባል የሰው ልጆች ከኢየሱስ ክርስቶስ ምን መማር አለባቸው የሚለውን የሃይማኖት አባቶች ለዝግጅት ክፍላችን የሚከተለውን አባታዊ ምክር ለግሰዋል ።

መምህር አካለወልድ ተሰማ (ዶ/ር) ይባላሉ። በመንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽህፈት ቤት የሕዝብ ግንኙነት ህትመትና ሚዲያ ዋና ክፍል ኃላፊ ናቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ መከራን የተቀበለውና እስከ መስቀል የደረሰው የሰው ልጆችን ወደ ቀደመ ክብራቸው

ትንሳዔ እርቅና ሰላምን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፓስተር ጻዲቁ አብዶ


መምህር አካለወልድ ተሰማ (ዶ/ር)





ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር)

# የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን ሕጋዊ እና ምቹ በማድረግ ሕገወጥ ስደትን ለመከላከል እየተሠራ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- ሕገወጥ ስደትን ለመከላከል ሕጋዊ አሠራርን በማቀላጠፍ፣ ቀላልና ምቹ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች በሚፈልጉት ሀገር ለሥራ የሚሰማሩበትን እድል ለመፍጠር እየተሠራ እንደሚገኝ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ።

ሚኒስትር ዴኤታ ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በህጋዊ መንገድ የሚኬድባቸውን የመዳረሻ ሀገራትን ቁጥር በመጨመር፤ የሥልጠና እድሎችን በማስፋት እና ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት ሕገወጥ ስደትን ለመከላከል እየተሠራ ይገኛል።

ሕጋዊ ሥርዓቱን ተከትለው በየቀኑ ከአንድ ሺ 800 እስከ አንድ ሺህ 900 ዜጎች ወደ ውጭ ሀገር እንደሚጓዙ ጠቁመው፣ በዚሁ መሠረት ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከ200 ሺህ በላይ ዜጎች በሕጋዊ መንገድ ከሀገር መውጣታቸውን ገልፀዋል።

ዜጎች ሕገ ወጥ ሥራ ስምሪትን የሚመርጡት ሕጋዊ መንገዱ ሲጠብ እንደመሆኑ አሰራሩን ሪፎርም በማድረግ የውጭ ሀገር ሥራ ስምሪትን ህጋዊ እና ምቹ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሕጋዊ የውጭ ሥራ ስምሪት እየሰፋ ሲሄድ ሕገ ወጥ መንገድ እየጠበበ ይሄዳል፣ በሂደትም ይዘጋል የሚል እምነት አለን ብለዋል።

እንደ እርሳቸው ገለፃ፤ በሕጋዊ መንገድ ወደ ተለያዩ መዳረሻ ሀገራት ለሚሄዱ ዜጎች ከመዳረሻ ሀገራቱ ጋር በመነጋገር ዝቅተኛ የደመወዝ ወለል በማስቀመጥ እንዲሰማሩ እየተደረገ ይገኛል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት አሰራሮችን በማዘመን የውጭ ስምሪት ከሰዎች ንክኪ ነጻ በሆነ መንገድ እንዲከወን በማድረግ ዜጎች ወደቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሄደው ሲመዘገቡ በዲጂታል ሥርዓት መረጃቸው የሚቀመጥበት አሠራር ተዘርግቷል።

በርካቶች በቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ገብተው እየሰለጠኑ ናቸው። ሥልጠናውን እንዳጠናቀቁ በተዘረጋው ዲጂታል ሥርዓት ምዝገባ በማከናወን ስምሪት የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ጋር በመቀናጀትም ወደ ውጭ ሀገር በሥራ ለሚሰማሩ ዜጎች ፓስፖርት ቅድሚያ እንዲሰጥ እየተደረገ ይገኛል ሲሉም ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር) አመልክተዋል።

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመቆጣጠር በታክስ ፎርስ እየተሠራ ቢሆንም አሁንም እዚህም እዚያም በደላሎች የሚሞከሩ ነገሮች ይኖራሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሕጋዊ ስምሪቱ ከሰፋ ዜጎች ሕገወጥ ስምሪቱን የሚመርጡበት ሁኔታ አይኖርም ብለዋል።

መዳረሻ ሀገራትን የማስፋት ሥራም እየተሠራ ነው። ከዚህ በፊት የተጀመሩና ዜጎች እየተሰማሩባቸው የሚገኙ ዱባይ፣ ሳዑዲ አረቢያና መሰል ሀገራት ላይ ተወስኖ የነበረውን በማስፋት በአውሮፓ ሀገራት እየተመቻቸ ይገኛል ሲሉም አብራርተዋል።

በጀርመን እና በስዊድን በብቃት የሰለጠነ የሰው ሃይል ማቅረብ ለመጀመር ታቅዶ ድርድር እየተደረገ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

በሀገር ውስጥ ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ሥራ ለመፍጠር እቅድ መያዙን የጠቆሙት ሚኒስትር ዴኤታው፣ በገጠርና በከተማ አበረታች ሁኔታዎችን እየተመለከትን ነው፤ ያሉ ጸጋዎችን ለይቶ በስፋት የማሰማራት ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ዜጎች በሀገር ውስጥ መንግሥት ትኩረት በሰጣቸው የግብርና፣ የማኑፋክቸሪንግ፣ የኮንስትራክሽን፣ የቱሪዝም፣ ዲጂታል ኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ እንደሚበረታቱ አመልክተው፣ ክህሎት መር የሥራ እድል ፈጠራ እንዲስፋፋ እየተደረገ እንደሚገኝና ዜጎች ወደ ሥራ ከመሠማራታቸው አስቀድሞ በቂ ክህሎት፣ እውቀት፣ ተነሳሽነትና የንግድ አስተዳደር ክህሎት እንዲጨብጡ እየተደረገ እንደሚገኝም ገልፀዋል።



# በክልሉ ከሦስት ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ላይ የተፋሰስ ልማት ሥራ ተከናውኗል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ:- ዘንድሮው በኦሮሚያ ክልል በ 3 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራ የተከናወነ መሆኑን የክልሉ ግብርና ቢሮ አስታወቀ፡፡

የኦሮሚያ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኤሊያስ ከድር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ እና የተጎዳውን የአካባቢ ሥነምህዳር ለማስተካከል የተፋሰስ ልማት ሥራ በትኩረት ተሠርቷል፡፡

በዚህም ዘንድሮ በክልሉ በተሠራው የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት በ 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የተፋሰስ ልማት ለማካሄድ ታቅዶ እንደነበር አንስተው፤ በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ሥራም ከ 6 ሺህ 460 በላይ ተፋሰሶችን በማልማት 3 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት መሸፈን መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በተፋሰሱ ሥራም እርከን መሥራትን ጨምሮ የአፍርና ውሃ ጥበቃ ሥራ የተሠራ ሲሆን፤ በ 9 ነጥብ 8 ሚሊዮን የማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎና የዜግነት አገልግሎት ተከናውኗል፡፡ ይህም አገልግሎት በገንዘብ ሲተመን 9 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ዋጋ የሚገመት ነው ብለዋል፡፡

አቶ ኤሊያስ እንደገለጹት፤ 539 ሺህ ሄክታር መሬትን ከሰውና እንስሳት ከንክኪ ነጻ ለማድረግ ታቅዶ 638 ሺህ ሄክታር መሬት ከሰውና እንስሳት ንክኪ ነጻ ማድረግ ተችሏል፡፡ ይህንም የአፈር ለምነትናን ምርታማነትን የሚጨምር ነው፡፡

በክልሉ በሚከናወነው የተፋሰስ ልማት ሥራ የአፈርና ውሃ ጥበቃ በመሠራቱ የአፈር መሸርሸርን በመቀነስ፣ ለግብርናው ምርትና ምርታማነት በማሳደግ፣ የተጎዱ አካባቢዎች መልሰው እንዲያገግሙ በማስቻል ለአወንታዊ የአየር ንብረት ለውጥ ጉልህ ሚና የሚጫወት ነው ብለዋል፡፡

በተጨማሪም የከርሰ ምድር ውሃ እና የተለያዩ ኩሬዎች በቅርበት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል ነው ያሉት አቶ ኤሊያስ ፤ማህበረሰቡ በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በንብ ማነብ፣ ፍራፍሬዎች በማልማትና በመሰል መስኮች እንዲሠማራ የሥራ እድል በለመፍጠርና ከገጠር ወደ ከተማ ያለውን ከፍተኛ ፍልሰት ለመቆጣጠር የሚያስችልም ነው ብለዋል፡፡

በዚህም በክልሉ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ የተፋሰስ ልማትና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎች



አቶ ኤሊያስ ከድር

የግብርና ምርትና ምርታማነት በመጨመር ትላልቅ ውጤቶች እንዳመጡ አቶ ኤሊያስ ተናግረዋል፡፡

ቢሮው የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ እንክብካቤ እና የልማት ሥራን በትኩረት እየተሠራ ነው ብለው፤ ይህንንም አጠናክሮ ለማስቀጠል እና ህብረተሰቡ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ያለውን ጠቀሜታ ተረድቶ ተሳታፊነቱን እንዲጨምር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በስፋት የሚሰሩ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

# በአማራ ክልል ለልማት ሥራዎች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ:- በአማራ ክልል ሰላም በመስፈኑ ለልማት ሥራዎች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ሲሉ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማሥተባበሪያ ማዕከል ኃላፊ አደም ፋራህ ገለጹ፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ እና በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማስተባበሪያ ማዕከል ሃላፊ አደም ፋራህ ከአማራ ክልል ከፍተኛ መሪዎች ጋር በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ የሚከናወኑ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን ተዘዋውረው ተመልክተዋል።

አቶ አደም የክልሉ ሕዝብ ሰላም እንዲመለስ የሀገር መከላከያ ሠራዊት እና የክልሉ የፀጥታ መዋቅር ከፖለቲካ አመራሩ ጋር በመሆን ከፍተኛ ሥራ ማከናወናቸውንም ገልጸዋል።

አሁን ላይ ክልሉ የተሻለ ሰላም ማግኘቱን ገልጸው፤ ይህም ሕዝብን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የልማት ሥራዎችን ለማከናወን ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው ብለዋል።

አሁን ላይ ከክልሉ ጀምሮ የዞን እና የወረዳ አመራሮች የአካባቢያቸውን ሰላም በቁርጠኝነት እያስከበሩ የልማት ሥራዎችንም በከፍተኛ ተነሳሽነት እያከናወኑ እንደሚገኙ ተመልክተናል ብለዋል አቶ አደም። በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ በርካታ የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሌማት ቱሩፋት ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ እንደሚገኙ መመልከታቸውንም አቶ አደም ፋራህ ገልጸዋል። የዓሣ እርባታ፣ ከብት ማድለብ፣ ዶሮ እርባታ እና ሌሎችም የእንስሳት ዘርፍ ሥራዎች በሰፊው መከናወናቸው ሀገሪቱ የያዘችውን የሌማት ቱሩፋት እንቅስቃሴ የሚደግፍ ነው ብለዋል። ወጣቶችንም ተጠቃሚ እያደረገ እንደሚገኝ



ገልጸዋል።

አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደ ሀገር ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸው ናቸው ያሉት አቶ አደም፤ በአማራ ክልል በርካታ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሥራቸውን እያከናወኑ ነው ብለዋል። ለአብነትም በባሕር ዳር ከተማ ውስጥ የተመለከቱት ግዙፍ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ለሀገሪቱ የእንስሳት ሀብት እድገት ጉልህ ሚና የሚጫወት ስለመሆኑም ተናግረዋል።

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የእንስሳት መኖ ችግር አለ፤ ይህም የዘርፉ ማነቆ ነው ብለዋል አቶ አደም። በባሕር ዳር ከተማ የሚገኘው የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ከአካባቢው አልፎ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎችም ምርቱን በማዳረስ እና ችግሩን በመፍታት የሌማት ቱሩፋት ሥራዎችን ማገዝ የሚችል ስለመሆኑም ገልጸዋል።


አቶ አደም ፋራህ ከሀገር ውስጥ ፍጆታ በተጨማሪ ምርት ወደ ጎረቤት ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ለመሆን አስቦ መሥራት እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል። ለዚህም የገበያ ትስስርን ማጠናከር ተገቢ ነው ማለታቸውን አሚኮ ዘግቧል፡፡

# "የቀለጣ ከተማ የወሰን ማስከበር ሥራ መጓተት ለወልደሃኔ - ዱርጊ የመንገድ ግንባታ እንቅፋት ሆኗል"

- የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር

# "የወሰን ማስከበር ሥራው በግንቦት ወር ይጠናቀቃል"

- የጠምባሮ ልዩ ወረዳ



አዲስ አበባ፡- የወልደሃኔ - ዱርጊ የመንገድ ግንባታ በፍጥነት እንዳይጠናቀቅ የቀለጣ ከተማ የወሰን ማስከበር ሥራ እንቅፋት እንደሆነበት የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ። የጠምባሮ ልዩ ወረዳ በበኩሉ የወሰን ማስከበር ሥራውን ሙሉ ለሙሉ በግንቦት ወር እንደሚያጠናቅቅ ገልጿል።

በኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሶዶ አካባቢ የግንባታ ፕሮጀክቶች ጽህፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር ሰለሞን ሞላ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የወልደሃኔ - ዱርጊ የመንገድ ግንባታ ከሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ እየተገነባ ያለ ፕሮጀክት ነው።

መንገዱ 41 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ሲሆን ግንባታው ሲጠናቀቅ ደቡብ ምዕራብ ክልል- ዳውሮ ዞን እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል- ጠምባሮ ልዩ ወረዳን ያገናኛል ያሉት ኢንጂነር ሰለሞን፤ መንገዱ በፍጥነት እንዳይጠናቀቅ የጠምባሮ ልዩ ወረዳ ቀለጣ ከተማ አካባቢ ያለው የወሰን ማስከበር ሥራ መጓተት እንቅፋት ሆኗል ብለዋል።

ይህም በወሰን ማስከበር ሥራው የሌሉ ንብረቶች ጨምሮ የማስመዝገብ፣ ሕገ ወጥ የቤት ግንባታ እና የተለዩ ንብረቶችን አለማስነሳት የሚታዩ ችግሮች መሆኑን ጠቅሰው፤ የመንገዱን ግንባታ በቀሪው ሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ የወሰን ማስከበር ሥራ በፍጥነት ሊጠናቀቅ ይገባል ብለዋል።

ግንባታውን ኤምሲጂ ኮንስትራክሽን ከሜልኮን ኮንስትራክሽን ጋር በጥምረት እየሠራ መሆኑንም ገልጸዋል።

የጠምባሮ ልዩ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ሀብታሙ በላይነህ በበኩላቸው፤ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ ቀለጣ ከተማ አካባቢ ያለውን የወሰን ማስከበር ሥራ ሙሉ በሙሉ በመጪው በግንቦት ወር 2016 ዓ.ም እንደሚጠናቀቅ ገልጸዋል።

በካሳ ሕጉ መሠረት ግንባታው ከመጀመሩ በፊት የካሳ ክፍያ እንዲከፈል ያስገድዳል። ነገር ግን ማህበረሰቡን በማሳመን ከካሳ ክፍያው በፊት የመንገድ ግንባታው እንዲጀመር ተደርጓል ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ የመንገዱ ዲዛይን ከተጠና በኋላ የተሰሩ ቤቶችን የማጣራት ሥራ እየተሠራ ነው። በዚህም ሕገ ወጥ ቤቶች ላይ ርምጃ እንደሚወሰድ ገልጸዋል።

የወልደሃኔ - ዱርጊ የመንገድ ግንባታ ሁለት ክልሎችን ያገናኛል። የመንገዱ ግንባታ ሲጠናቀቅም በሁለቱ ማህበረሰብ መካከል ያለውን የንግድና እርስ በእርስ ግንኙነት ያጠናክራል። ከዚህም ባለፈ ከመሠረተ ልማትና ከሥራ እድል ጋር ተያይዘው የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ያስችላል ብለዋል።

የወልደሃኔ - ዱርጊ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተጠሪ መሀንዲስ ኢንጅነር ሳምሶን አለማየሁ በበኩላቸው፤ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ፣ ከዲዛይን በኋላ የተሰሩ ሕገ-ወጥ ግንባታዎች፣ የወሰን ማስከበር ሥራዎች አለመጠናቀቅ በተለይ በቀለጣ ከተማ፣ የሲሚንቶና የብረት ዕጥረት በፕሮጀክቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ፕሮጀክቱ 41 ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው ያሉት ኢንጂነር ሳምሶን፤ መንገዱ ሲጠናቀቅ ደቡብ ምዕራብ ክልል- ዳውሮ ዞን እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል- ጠምባሮ ልዩ ወረዳ ያገናኛል ብለዋል።

ሁለቱም ዞኖች ማለትም ከምባታ ጠምባሮ እና ዳውሮ ዞን ለማገናኘት ቀድሞ 250 ኪሎ ሜትር ርዝመት ሲጓጓዙ የነበረው መንገድ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ወደ 49 ኪሎ ሜትር እንደሚቀንስም ተናግረዋል።

እንደ ኢንጂነር ሳምሶን ገለፃ፤ በከሰል ድንጋይ ምርት ምርታማ የሆነውን ዳውሮ ዞን የገበያ ትስስርን ያጎለብታል፡፡ የኢንቨስትመንት እድሎች በመፍጠር የገበያ ትስስርን ያጎለብታል፡፡

የመንገዱ ግንባታ የተለያዩ ችግሮች ቢያጋጥሙም ከዕቅድም ከጊዜም አንፃር የተሻለ አፈፃፀም እያሳየ ሲሆን እስከ መጋቢት 2016 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የፕሮጀክቱን 12 በመቶ ሥራ ማጠናቀቅ መቻሉን ገልጸዋል።



## ለግድቡ ግንባታ ቀሪ ሥራ ከዳያስፖራው ሶስት ሚሊዮን ዶላር ለማሰባሰብ እየተሠራ ነው

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- ለዓባይ ግድብ ግንባታ ቀሪ ሥራ የሚሆን ከዳያስፖራው ማህበረሰብ ሶስት ሚሊዮን ዶላር ለማሰባሰብ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ገለጸ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ በላይነህ አቅናው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የግድቡ ግንባታ አሁን ያለበት ደረጃ እንዲደርስ የዳያስፖራው ሚና ጉልህ ነው። የግድቡ ግንባታ ከተጀመረ ጀምሮ ድጋፍ በማድረግ ዳያስፖራው እስከ አሁን 55 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ድጋፍ አድርጓል።

አሁንም የግድቡን ግንባታ ቀሪ ሥራዎች ለማጠናቀቅ ዳያስፖራውን በማስተባበር ሶስት ሚሊዮን ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዷል።

ከህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ጋር በጋራ በመሆን አዲስ ኮሚቴ ተዋቅሮ የታቀደውን ገንዘቡ ለማሰባሰብ እንቅስቃሴ መጀመሩን አቶ በላይነህ ተናግረዋል።

ሀገር ውስጥ ካሉ ዳያስፖራዎች ጋር በቅርቡ ውይይት መደረጉን የተናገሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ የዓባይ ግድብ በኢትዮጵያውያን ተጀምሮ በመጠናቀቅ ላይ ያለ ትልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክት እንደመሆኑ ዳያስፖራው "እንችላለን" በሚል ጠንካራ መንፈስ የሚችለውን ሁሉ ለማድረግ ትልቅ ተነሳሽነት እና ቁርጠኝነት እንዳለውም አመልክተዋል።

በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ከሚኖሩባቸው ሀገራት በቀጥታ ገንዘብ ማስገባት የሚችሉበት አዲስ መተግበሪያ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መፍጠሩን ጠቅሰዋል።

ዳያስፖራዎች ሌሎች የባንክ አማራጮችንም በመጠቀም በቀጥታ ገንዘብ መላክ እንደሚችሉም ጠቁመዋል።

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ዳያስፖራዎችን በሩቅ ምስራቅ፣ በአሜሪካ እንዲሁም በአፍሪካ የሚገኙትን በቀጣና በመከፋፈል ድጋፉን ለማሰባሰብ እንደሚሠራ ነው አቶ በላይነህ የገለጹት።

ከገቢ አሰባሳቢ ኮሚቴው ጋር በመሆን እንዳስፈላጊነቱ ዳያስፖራው ወደሚገኝበት ሀገራት ሄዶ በማወያየት የታቀደውን ገንዘብ ለማሰባሰብ በትኩረት እንደሚሠራ ገልጸዋል።

## ማኅበሩ ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ስኬት የበኩሉን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገለጸ

አመለወርቅ ከበደ



ዮሐንስ በንቲ (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- ለሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ሥራዎች ውጤታማነት የበኩሉን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት ዮሐንስ በንቲ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማኅበሩ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በሚፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመስራት ቀደም ብሎ ስምምነት ተፈራርሟል፡፡

ኮሚሽኑ በምክክር ሂደቱ የሚሳተፉ ሰዎችን ከየወረዳው በሚመርጥበት ወቅት አሳታፊነቱንና ፍትሃዊነቱን ለማረጋገጥ ማኅበሩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዚህ ሂደትም በወረዳ የሚገኙ የማኅበሩ መዋቅሮች በተለይም ከትምህርት ማህበረሰቡ ጋር ተያይዘው በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊው ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ አጠቃላይ ከኮሚሽኑ በኩል ማህበረሰቡን ለመርዳት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች እንደሚሳተፍ አስረድተዋል፡፡

ምክክሩ ከሌሎች ሀገራት ተሞክሩ በመነሳት በኢትዮጵያ የቆዩና ከጊዜ ወደጊዜ እየተሸጋገሩ የመጡ ችግሮችን ለመፍታት እንደሚያስችል የተናገሩት ዶክተር ዮሐንስ፤ የመምህራን ማኅበሩም የምክክሩን ዓላማ በማመን አብሮ እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ዶክተር ዮሐንስ እንደተናሩት፤ አለመግባባቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ቀድሞ ተጎጂ የሚሆነው የትምህርት ዘርፉ ነው፡፡ በዚህም ትምህርት ቤቶች ይወድማሉ፤ መምህራን ፤ ተማሪዎች እና የትምህርት ማስረጃዎችም አብረው ይጠፋሉ፡፡

በመሆኑም ምክክር ኮሚሽኑ በሚያከናውናቸው ተግባራትና ከማኅበሩ በሚፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት ሲደረግ ቆይቷል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

ትምህርት የአዕምሮ ሥራ እንደመሆኑ የተረጋጋና ሰላማዊ አካባቢን ይፈልጋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሰላማዊ አካባቢን ለመፍጠር ማኅበሩ በመገናኛ ብዙሃን፣ በምክር ቤቶችና በሌሎች የውይይት መድረኮች አማካኝነት አስፈላጊውን ትብብር እያደረገ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ዓመታዊ የመምህራን ምክር ቤቶች ስብሰባ ላይ በተለየ መልኩ አጀንዳ ተቀርጾ ለምክክር ሂደቱ ስኬታማነት ውይይት እንደሚደረግ ጠቁመዋል፡፡

በማኅበሩ የውይይት መድረክ በሚኖርበት ወቅት ከሚሽኖች መጥተው ገለጻ እንዲያደርጉ ዕድል መሰጠቱን አብራርተው፤ ይህም መምህራን ስልምክክሩ ያላቸውን ጥያቄና አስተያየት እንዲያቀርቡ በር የከፈተ መሆኑን አንስተዋል።

ፕሬዝዳንቱ እንደተናገሩት፤ የምክክር ሂደቱ ባለቤቶች በዋናነት ኢትዮጵያውያን በመሆናቸው ሁሉም ዜጎች የምክክሩ ጠቃሚነት ተረድተው እነዲሳተፉ ማኅበሩ የጀመረውን ጥረት ይቀጥላል።

አንዳንድ ሀገራት የምክክር ሂደቱን ጀምረው ውይይቱ አሳታፊ ባለመሆኑ ውጤታማ አለመሆናቸውን አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ምክክር መምህራንና ሌሎች የማህበረሰቡን ክፍሎች አሳታፊ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

# የፋሲካ በዓልና ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመግዛት የመጡት አቶ አበባው ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ፤ በዘንድሮው የትንሳኤ በዓል በርካታ የእርድ እንስሳት የቀረቡበት ቢሆንም መጠነኛ የዋጋ ጭማሬ አሳይቷል ይላሉ።

በገበያው የአንድ በሬ ዋጋ ዝቅተኛው 35 ሺህ መካከለኛ 60 ሺህ ከፍተኛው እስከ 95 ሺህ ብር እየተገበያየ ነው ያሉት አቶ አበባው እሳቸውና ጓደኞቻቸው በ65 ሺህ ብር የቅርጫ በሬ መግዛታቸውን ይገልጻሉ። ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የተሻለ አቅርቦት መኖሩን ጠቅሰው፤ በዋጋ ረገድ መጠነኛ ጭማሪ ማሳየቱን ነግረውናል።

የፍየል ነጋዴ የሆኑት አቶ አማረ ሐብታሙ በበኩላቸው፡-ለዘንድሮው የትንሳኤ በዓል በርካታ የእርድ ፍየሎችን አቅርበዋል። ፍየል ዝቅተኛው ከ8 ሺህ ብር ጀምሮ እየሸጡ እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ መካከለኛ ፍየል 15 ሺህ ብር እና ከፍተኛ እስከ 25 ሺህ ብር እየተሸጡ መሆናቸውን ገልጸዋል። ከአምናው ጋር ሲነጻጸር የፍየል ዋጋ የተሻለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በሸጎሌ በግ ተራ በግ ሲገዙ ያገኘናቸው አቶ ተክሉ ዮናስ እንደገለጹት፡-የበግ ገበያ ከባለፈው የበዓል ገበያ ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ የዋጋ ጭማሪ አሳይቷል። ለምርጫ



በሚመች መልኩ በርካታ የእርድ በጎች ማግኘታቸውን አመልክተው፤ ለቤተሰባቸው 12 ሺህ 500 ብር በግ መግዛታቸውን ተናግረዋል።

በገበያው ዝቅተኛ በግ 7 ሺህ ብር እየተባለ ይገኛል የሚሉት አቶ ተክሉ፤ መካከለኛ 12 ሺህ እና ከፍተኛው 15 ሺህ ብር ድረስ እየሸጡ እንደሚገኙ ነው የገለጹት።

ሌላኛው የበሬ ነጋዴ አቶ መብራቱ ከበደ እንደተናገሩ፡- በገበያው የዋጋ ጭማሬው የመኖ ዋጋ መጨመር አርብቶ አደሩ የእርሻ ሥራ ላይ ትኩረት በማድረጉ ነው ይላሉ። በተጨማሪም በተገቢው መጠን የእርድ እንስሳት ወደ ገበያ አለመግባታቸው ለዋጋ መጨመር ምክንያት እንደሆነ ጠቅሰው፤ በገበያው በተለያየ መጠን የእርድ እንስሳትን ማቅረባቸውን ገልጸዋል።

እኛም የዘንድሮውን የትንሳኤ በዓል ምክንያት በማድረግ በሸጎሌ በግ ተራ ባደረግነው የገበያ ምልከታ በርካታ ቁጥር ያላቸው የእርድ እንስሳት ለገበያ ቀርበው ተመልክተናል። የከተማው ነዋሪዎችም እንደ አቅምና ፍላጎታቸው ሲገዙ ተመልክተናል።

# ትንሳዔ እርቅና ሰላምን ተግቶ የመፈለግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለመመለስና የቅር ባይነትን በተግባር ሊያሳይ መሆኑን ይገልጻሉ።

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች፣ አለመግባባቶችና መገፋፋቶች ይስተዋላሉ። ለሰው ደህንነት፣ ሰላም፣ አንድነትና ህብረት የማይበጁ ነገሮች እየታዩ ነው። የእነዚህም መነሻ እኔ ብቻ እኔ ብቻ ማለትና የእርስ በእርስ መገፋፋት ነው። የተፈጠረው ችግርን ደግሞ በይቅርታና በዕርቅ ለመፍታት ዝግጁ ያለመሆን ነው ይላሉ።

ትንሳኤ የሰው ልጆችን ከውድቀት የተነሱበትና ይቅርታን የተማሩበት ነው። እናም በሀገሪቱ ያሉትን ግጭቶች ለመፍታት እኛም ይቅርታና ዕርቅን ከትንሳኤ ልንማር ይገባል። ለሰዎች መልካም ነገርን በማሰብና ለበደሉን ይቅር በማለት፣ ዕርቅ በመፈጸም እና ሁሉም በተሰጠው ኃላፊነት ሰዎችን በአግባቡ ማገልገል በኢትዮጵያ ያሉትን ችግሮች መፍታት ይቻላል ነው ያሉት።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእኔ ተማሩ ብሏል። ይህንንም ሲል እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝ እንዳለው የሰው ልጆችም ፍጹም የዋህ፣ ትሁት እና በልባቸው ክፋትን የማያስቡ መሆን አለባቸው። በዓል ሲከበር በቤተክርስቲያን ተገኝቶ ሥርዓተ አምልኮውን ከመከታተል ባለፈ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ወገኖችን በማገዝ ሊሆን ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ፕሬዚዳንት ፓስተር ጻዲቁ አብዶ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን ሲል ማንም ሊከፍለው የማይችለውን ዋጋ ከፍሏል። ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበት ዋናው ምክንያት ሰውን ከአምላኩ ጋር ለማስታረቅ ነው ይላሉ።

የትንሳኤ በዓል የሚያስተምረው መሠረታዊ ቁም ነገር እርቅና ሰላምን ተግቶ መፈለግን ነው። ምዕመናኑም የክርስቶስን ፈለግ በመከተል በተለይም ሀገሪቱ ሰላምንና መረጋጋትን እጅግ በተጠማችበት ወቅት ልዩነትንና ክፉ ውጤትን ለማስቀረት ዋጋን ሊከፍሉ ይገባል ነው ያሉት።

ክፋት፣ ጭካኔ፣ በቀል፣ ተንኮልና ጥላቻ በትንሳኤው ኃይል ይዋጣሉ። እንደክርስትና እምነት ሞትንና ኢፍትሀዊነት ትንሳኤ በትንሳኤው ተሸንፈዋል። ሰዎች ይህንን በመረዳት ሰላምና አንድነትን አጥብቆ መፈለግ እንደሚገባ ይናገራሉ።

ምህርትና ይቅርታ መስጠት፣ በጉልበት፣ በተንኮል፣ በኃይል የሚገኝን ነገር መተው ከትንስኤ ልንማር ገባል። ኢየሱስ ለሰው ልጅ ዋጋን ለመክፈል ያስገደደው ፍቅር በመሆኑ የሰው ልጆችም እርስ በእርስ በመዋደድና ይቅር በመባባል በሀገሪቱ ዘላቂ ሰላምን ማስፈን ይገባል።

ጥላቻ፣ ቂም በቀል፣ ተንኮል፣ ክህደት እና የመሳሰሉት ተግባራት በማንኛውም እምነት ተቀባይነት የሌላቸው በመሆኑ ከእነዚህ ተግባራት በመውጣት ምህረትን፣ ይቅርታንና ፍቅርን ማሳየት እንደሚገባ ይገልጻሉ።

ሕዝበ ክርስቲያኑ የኢየሱስ ክርስቶስን የትንሳኤ በዓል ሲያከብር በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ምክንያት ከቤታቸው የተፈናቀሉና በችግር ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን በማሰብ ሊሆን እንደሚገባ ገልጸዋል።

# ከበጋ መስኖ ስንዴ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 የስንዴ ምርትን ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሠራ ባለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እስከ ሚያዚያ 21 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ82 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ተሰብስቧል፡፡

የግብርናውን ዘርፍ የስንዴን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በበጋ መስኖ፣ በበልግና በመኸር ወቅቶች በስፋት የማምረት ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ በ2016 የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት 120 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ለማግኘት ታቅዶ እስካሁን ድረስ 82 ሚሊዮን 670 ሺህ 200 ኩንታል ምርት ተሰብስቧል ብለዋል፡፡

በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች በ2016 በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን አውስተው፤ ከዚህም 120 ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡

በበጋ መስኖ ስንዴ በዘር ከተሸፈነው ሶስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ ከሁለት ነጥብ ሶስት ሚሊዮን በላይ የሚሆነውን መሰብሰብ ተችሏል ያሉት ስራ አስፈፃሚው፤ ከተሰበሰበው ሁለት ሚሊዮን 352 ሺህ 867 ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ ውስጥ አንድ ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በባህላዊ መንገድ እና 652 ሺህ 867 ሄክታሩ መሬቱ ደግሞ በኮባይነር መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የስንዴ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቅ ሚና እንዳለው ገልጸው፤ የበጋ መስኖ ለምቶ የደረሰውን ቀሪ ሰብል በወቅቱ በመሰብሰብ እቅዱን ለማሳካት ሰፊ ርብርብ እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ፣ የለም አፈር፣ የሰው ሃይል ሀብቷን በመጠቀም የስንዴን ምርትና ምርታማነት የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ እየተሠራ ባለውም ሥራ የስንዴ አቅርቦቱ ችግር የመቅረፍ፤ ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ ምርት የመተካትና የመሸፈን ሥራ ማከናወን ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የግብርና ምርቶችን በጥራትና በብዛት በማምረት የሀገር ውስጥ ፍጆታን ከማሟላት ባለፈ ለዓለም ገበያ ለማቅረብ በትኩረት እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

# የኤሌክትሪክ መኪኖች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሀገራችን ደግሞ፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ከነዳጅ ውጪ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖችን እየተዋወቀች ትገኛለች። መኪኖቹ በነዳጅ ከሚሠሩ መኪኖች ይልቅ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን የሚያስገኙ ስለመሆናቸው ምሁራን ያስረዳሉ።

የምጣኔ ሀብት ምሁሩ ቆስጠንጢኖስ በርኼ (ዶ/ር)፤ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ መኪኖች በተለይ ነዳጅ አምራች ላልሆኑ ሀገራት ለነዳጅ የሚያወጡትን ወጪ በከፍተኛ መጠን በመቀነስ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እንዳላቸው ይናገራሉ። ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የምታወጣው ለነዳጅ ግዢ መሆኑን ያነሱት ዶ/ሩ፣ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላለ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይል የማመንጨት አቅም ላለው ሀገር፣ በኤሌክትሪክ የሚሠሩ መኪኖችን መጠቀሙ የትራንስፖርት ዘርፉን በራስ አቅም የማንቀሳቀስ መልካም ጅምር ነው ይላሉ።

መኪኖቹ የአየር ብክለትን የማያስከትሉ መሆናቸውም ሌላው ጠቀሜታቸው እንደሆነም ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) አንስተዋል፣ ይህም የተፈጥሮ አካባቢን ከመጠበቅ አንጻር ሀገራችን የፈረመችውን ስምምነት ለማክበር የሚያስችል ነው ብለዋል።

የኤሌክትሪክ መኪኖች በነዳጅ ከሚሠሩ መኪኖች ይልቅ በተሻለ ዋጋ መገኘታቸውም እንዲሁ ሌላው ጠቀሜታቸው እንደሆነም ጠቅሰዋል።

መኪኖቹን የመጠቀም ፍላጎት እንዲጨምር በተለይም፣ መኪኖቹን ቻርጅ ማድረጊያ ቦታዎች ልክ እንደ ነዳጅ ማደያ ሁሉ መሟላት አለባቸው ይላሉ፤ ገንዘብ እያስከፈሉ መኪኖቹን ቻርጅ የሚያደርጉ የግል ዘርፍ ድርጅቶች ሊኖሩ እንደሚገባም ይመክራሉ።

በሌሎች ሀገራት ዘንድ የኤሌክትሪክ መኪኖችን መጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር በርካታ ወጪ እያፈሰሱ እንደሚገኙም አንስተዋል።

ስለመኪናው እውቀት ያላቸው ጋራዦች ጥቂቶች ናቸው ያሉት ዶ/ሩ፤ በዚህ ላይ እውቀት ያላቸው በቴክኖሎጂ የታገዙ ጋራዦችን ማስፋት እንደሚገባም አስተያየት ሰጥተዋል።

በፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ ዝግጅት ትግበራ ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ መሀመድ አዶሼ በበኩላቸው፣ ልክ እንደ ቆስጠንጢኖስ (ዶ/ር) ሁሉ የኤሌክትሪክ መኪኖችን በብዛት መጠቀም ይቻል ዘንድ ምቹ መሠረተ ልማትን መዘርጋት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ።

መኪኖቹ በተለይም በነዳጅ ሳቢያ የሚመጣውን የአየር ብክለት ለመቀነስ ጥሩ አማራጭ ናቸው ያሉት አቶ መሐመድ፣ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት የራሳቸው የሆነ እቅድ አዘጋጅተው እንደሚንቀሳቀሱ ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያም የበካይ ጋዝ ልቀትን መቀነስ የሚያስች የራሷ ዕቅድ አላት ያሉት አቶ መሐመድ፣ እንደ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ባቡር፣ የኤሌክትሪክ መኪና፤ ያለሞተር የሚሠሩ ሳይክል እና መሰል ተሽከርካሪዎችን መጠቀም የዕቅዱ አካል መሆኑን ያስረዳሉ።

የበካይ ጋዝ ልቀትን መቀነስ በአየር ብክለት ሳቢያ ጤና ላይ የሚመጡ ችግሮችን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውም ያብራራሉ። እንደ ቻይናና ሌሎች መሰል ያደጉ ሀገራት ከተሞቻቸው በበካይ ጋዝ እየተሞላ ነዋሪዎቻቸውም ለከፍተኛ የጤና ችግር እየተጋለጡ መሆናቸውን በማሳያነት ያነሱት አቶ መሐመድ፣ እነዚህን መኪኖች ጥቅም በቀላሉ የሚገለጽ አለመሆኑን ያስምሩበታል።

አቶ አሽናፊ አሰፋ፣ በአውቶ ኤሌክትሪክ የመኪና ቴክኖሎጂ ላይ ዕውቀቱ ያላቸው በሙያም ላለፉት 25 ዓመታት የሠሩ ናቸው፤ እርሳቸው እንዳሉት፣ በትራንስፖርቱ ዘርፍ ዘመኑ ያመጣቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች የመጠቀም ተገቢነት ላይ አጽንዖት ሰጥተው ይገልጻሉ። ቴክኖሎጂ ካፈራቸው ምርቶች መካከል የኤሌክትሪክ መኪኖች ከነዳጅ ከሚሠሩት ይልቅ የበለጠ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይናገራሉ።

እንደ አቶ አሽናፊ ማብራሪያ፣ በነዳጅ የሚሠሩ መኪኖች የሚያመነጩት መርዛማ ጋዝ ተፈጥሮን የሚያዛባ፣ የሰውን ልጅ እስከ ሞት አደጋ ሊያደርስ የሚችል ነው። በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ተገዝቶ የሚመጣን ነዳጅ ነው የሚጠቀሙት። ሌላው መኪኖቹ በሚበላሹበት ጊዜም መለዋወጫቸውን ለማግኘት የውጭ ምንዛሬን ይጠይቃል። ለመለዋወጫ የሚወጣው ገንዘብ ደግሞ እንደ ሀገር፣ ምጣኔ ሀብትን ያዛባል። ከመለዋወጫ ከሚወጣው ወጪ በተጨማሪ የነዳጅ መኪኖች ቶሎ ቶሎ የሰርቪስ አገልግሎት የሚያሻቸው መሆናቸውም ሌላው ችግራቸው ነው።

የኤሌክትሪክ መኪኖች ግን የአየር ንብረት ብክለትን የማያስከትሉ መሆናቸው ትልቁ ጠቀሜታቸው ሲሆን፣ የውስጥ እቃዎቻቸው በነዳጅ እንደሚሠሩ መኪኖች ብዙ ባለመሆኑ፣ ለመለዋወጫ ችግር እምባዛም አይዳረጉም። መለዋወጫቸው ብዙ ባለመሆኑም ቶሎ ለብልሽት የሚዳረጉ አይደሉም፤ ተጠቃሚውንም ከወጪ የሚታደጉ፣ መኪናን ለማስጠገን የሚወጣውን ጊዜም የሚቆጥቡ ናቸው።

አቶ አሽናፊ እንዳሉት፣ የኤሌክትሪክ መኪና የተራቀቀ ቴክኖሎጂን የሚጠቀሙ ናቸው። በነዳጅ ከሚሠሩ መኪኖች በተሻለ ሁኔታ ለአሽከርካሪው ነገሮችን የሚያቀሉ ሆነው የተሠሩ በመሆናቸው ተመራጭ ያደርጋቸዋል።

የኤሌክትሪክ መኪኖች ከላይ የተጠቀሱና ሌሎችም ተመራጭ እንዲሆኑ የሚያደርጓቸው ባህሪያት ቢኖሯቸውም በእኛ ሀገር ሁኔታ ተፈላጊነቱን ለመጨመር ከመሠረተ ልማት ላይ የተያያዙ ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎች መቀየር እንደሚያሻ ይመክራሉ።

መኪኖቹን በፍጥነት ቻርጅ የሚደረጉባቸው ቦታዎች አለመኖርን አቶ አሽናፊ ትልቁ ችግር ነው ብለው ይጠቅሳሉ። ለመኪኖቹ መለዋወጫ በሀገር ውስጥ በቀላሉ አለመገኘት፣ የኤሌክትሪክ መኪኖች የደረሱበትን ቴክኖሎጂ የሚመጥኑ የጋራዥ አገልግሎት በስፋት አለመኖርም በሀገራችን የመኪኖቹን ተፈላጊነት የሚቀንሱ መሆናቸውን ያስረዳሉ።

ለዚህም ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎች በየቦታው ሊኖሩ ይገባል በሚለው ሃሳብም ከዶ/ር ቆስጠንጢኖስና ከአቶ መሐመድ ጋር ይስማማሉ። ከዚሁ ጋር አያይዘው በሌሎች ሀገራት የኤሌክትሪክ መኪና አሽከርካሪዎች በየካፌው የቻርጅ አገልግሎት እንደሚያገኙም አንስተዋል።


ከዕውቀቱና ከመሠረተ ልማቱ በፊት ቴክኖሎጂው ቀድሞ ገብቷል ያሉት አቶ አሽናፊ፣ መኪኖቹ ከሚያስገኙት ጥቅም ተጠቃሚ ለመሆን አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ላይ መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመተባበር ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አለበት በሚለው ሃሳብ አስተያየታቸውን አሳርገዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

# ‹‹ክርስቶስ በሞቱ ፍቅሩን ገልጾ ይቅር እንዳለን የይቅርታ እና የዕርቅ ሰዎች ብንሆን መልካም ነው››

ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ



ምሕረት ሞገስ

ትውልዳቸው ትግራይ ክልል ተንቤን ውስጥ ገብረ ስብሐት ኢየሱስ ገለበዳ አካባቢ ነው። አቶ አብርሃ መስፍን እና ወይዘሮ ምፅላል ገብረ ሚካኤል ከወለዷቸው ዘጠኝ ልጆች መካከል ንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ ስምንተኛ ልጅ ናቸው። ባል እና ሚስቱ በቅዱስ ቁርባን በተክሊል የተጋቡ ሲሆን፤ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ሁለቱም በ80 ዓመታቸው ነው። የንቡረ እድ ኤልያስ እናት እስከ ሰባት ቤተሰብ ድረስ ካህን ናቸው። የአባታቸው ቤተሰብ ደግሞ ወደ ቤተ መንግሥት የቀረቡ ናቸው።

የንቡረ እድ ኤልያስ ቤተሰቦች በግብርና የሚተዳደሩ ሲሆን፤ ጊዜው እና ቦታው በሚፈቅደው ልክ የሞላላቸው፤ ከራሳቸው አልፈው ለሌላም የሚተርፉ ደጎና የሚባል ኑሮን የኖሩ ነበሩ። አቶ አብርሃ ልጆቻቸው እንዲዋሹ፣ እንዲሰርቁ ካለመፍቀድ ባሻገር ለልጆቻቸው እንደጎረቤቶቻቸው ነፃነት አይሰጡም ነበር። በዚህ ምክንያት ንቡረ እድ ኤልያስ እጅግ ተገድበው በግ እና ፍየል እየጠበቁ መኖር ግዴታቸው ነበር። ዕድሜያቸው ከፍ ሲል ግን ከቤተሰቡ ተለይተው ፊደል ለመቁጠር የታደሉት እርሳቸው ብቻ ሆኑ።

ፊደል ለመቁጠር ዕድል የሰጣቸው ደግሞ ገና በሕፃንነታቸው በሚያነሡት የተለያዩ ጥያቄዎች ምክንያት ነበር። በአቅራቢያቸው ቤተ ክርስቲያን በመኖሩ ሕፃን ሆነው ማታ ማታ ሰዎች የቄስ ትምህርት ጮኸው ሲማሩ ይሰሙና፤ ከአባታቸው ጋር ሲተኙ ‹‹እነዚህ ሰዎች ለምን ይጮሃሉ?›› የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ። ትምህርት እየተማሩ መሆኑ ሲነገራቸው ‹‹ትምህርት ምንድን ነው?›› የሚል ጥያቄ አቀረቡ። አባታቸው አቶ አብርሃ የሚያውቁት ዳዊት ሳይሆን የትውልድ ሐረግ ነው። ስለዚህ ለልጃቸው በራሳቸው እናት እና አባት በኩል እስከ ሃያ በሚስታቸው እናት እና አባት በኩል ደግሞ እስከ ሰባት የትውልድ ሐረግ አስቆጠሯቸው።

ንቡረ እድ ኤልያስ የትውልድ ሐረጋቸውን ሸምድደው ለመያዝ ብዙ ጊዜ አልፈጀባቸውም። ‹‹የማን ልጅ ነህ?›› ሲባሉ የቤተሰብ የትውልድ ሐረጋቸውን ያነበንባሉ። እናት እና አባታቸው ሰባት ትውልድ ላይ ቤተሰባቸው ይገናኛል። ስለዚህ እናቱን እና አባቱን አንድ የሚያደርግ ልጅ ተብለው ታዋቂነትን አተረፉ። ሰው ሲያደንቃቸው ተደሰቱ፤ ስለዚህ አባታቸው ‹‹ልጄ ትምህርት ይሆንለታል›› ብለው አሰቡ።

እናት የካህን ቤተሰብ በመሆናቸው ልጃቸው እንደ አባታቸው ካህን እንዲሆኑ እና የአባታቸውን መስቀል እንዲይዝ ፈለጉ። አባት በበኩላቸው የተወሰደባቸውን መሬት ተከራክረው ለማስመለስ ፀሐፊ ፍለጋ በመንከራተታቸው ልጃቸው ተከራክሮ እንዲያስመልስላቸው ተመኙ። ንቡረ እድ ኤልያስ ተማር ሲባሉ ፊደል ስለማያውቁ እና ጎረቤት ያዩትን ትልቅ ዳዊት ሲያዩ ያንን ሁሉ ማጥናት ይከብደኛል ብለው ስለፈሩ ለመማር ፈቃደኛ አልነበሩም። ስለዚህ ‹‹ከመማር ፍየል ጥበቃ ይሻለኛል›› ብለው ተማር የሚለውን የቤተሰብ ግፊት ከመፈጸም ይልቅ እምቢ ሳይሉ ሸሽት የጀመሩ ቢሆንም፤ አሁን ግን ተምረው ንቡረ እድ ሆነው አክሱምን ከማስተዳደር አልፈው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ እስከመሆን ደርሰዋል። አሁን በጠቅላይ ቤተ ክህነት የፕላን እና ስትራቴጂ ኃላፊ ናቸው። ከንቡረ እድ ኤልያስ አብርሃ ጋር ሕይወታቸውን፣ ጾሙን እና የትንሣኤ በዓልን በተመለከተ ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ፊደል መቁጠር እና የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዴት ጀመሩ?**

**ንቡረ እድ ኤልያስ፡-** በልጅነቴ ፈጣን ነበርኩ። ትምህርት ግን ፈርቼ ነበር። ተማር ስባል ፍየል ጥበቃ ይሻለኛል ብዬ እረኝነትን ብመርጥም አባቴ መማር አለብህ ብለው ተንቤን ወስደው ለቤተክርስቲያኑ መምህር ለቄስ ካህሳይ ‹‹ፍየል ጠብቅ፤ እርሻ ሥራ፤ አረም ንቀል፤ አጨዳ እርዳኝ ብዬ አልወስደውም፤ ይኸው ልጄን ሰጥቻለሁ›› ብለው አስረከቡኝ። በወቅቱ ፊደል አልገዙልኝም ነበር። መምህሬ ግን ፊደል አምጥተው እግራቸው መሐል አስቀምጠው በስንደዶ ሆሄያትን አስቆጠሩኝ። ቄሱ ፊደል ሰጡኝ፤ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር ተቀላቅዬ በሳምንት ፊደል ለየሁ።

አባቴ ልጅ ይብላ፣ ይጠጣ፣ አይብረደው እንጂ ከዚያ ውጭ ሲያጠፋ መቀጣት አለበት ይላሉ። እጅግ ቁጡ ናቸው። በተጨማሪ ልጅ ምንም ጎበዝ ቢሆን ብዙም አያደንቁም። በሳምንቴ አባቴ ፊደል መለየቴን ለማወቅ ጥያቄ ሲያቀርቡ አነበነብኩት፤ አላደነቁኝም። ‹‹ገና ነህ የፊደሎቹን ክንፎች መለየት አለብህ›› አሉኝ፤ የአባቴ ፍየል ጠብቅ የሚል ትእዛዝ ሙሉ ለሙሉ ቆመ። ውሎ እና አዳሬ ቤተክርስቲያን ሆነ። ለምሳ ከቤቴ ገብቼ ምሳዬን በልቼ፤ ለእራት የሚሆን ምግብ በአንሶላዬ ጠቅልዬ በዚያው አድራለሁ። በእንዲህ ያለ ሁኔታ በአንድ ዓመት ውስጥ ዲያቆን ለመሆን በቃሁ።

ጎበዝ አንባቢ ብቻ ሳልሆን በዜማም በጣም ጥሩ በመሆኔ ‹‹ይበቃሃል ድቁና መቀበል ትችላለህ›› ተባልኩ። አባቴ መቀሌ ወስደው ክህነት እንድቀበል ፈተና እንድወስድ አደረጉ። በፈተናው ጥሩ ውጤት አምጥቼ ድቁና ተቀበልኩ። ድንቁና ከተቀበልኩ በኋላ ወዲያው ወደ ቅዳሴ አልገባሁም። ልታይ፣ ልታይ ማለት አይገባም ተብዬ ለስድስት ወር ቆየሁ። በኋላ ቀድስ ተብዬ አዲስ ልብስ ተገዛልኝ። በዐሥር ዓመቴ ሊቀ ካህናቱ ልጃችን ድቁና አምጥቷል ተብዬ ዐውደ ምህረቱ (መድረኩ) ላይ ደብዳቤ ተነበበ።

ማንም ቢሆን ደብዳቤው ሲነበብ አጎንብሶ እጅ ይነሣል። ድቁና ተቀባይ የመምህራኑንም፣ የካህናቱንም ሆነ የምእመኑን እግር እየሳመ ይመረቃል። እኔም እንደ ሥርዓቱ አደረግኩ። ከአንድ ወር በኋላ ቅዳሴ ገባሁ። አባቴም በመደሰታቸው ለካህናቱ ሙሉ ግብዣ ተደረገ። ከዚያም ጨርሷል ተባልኩ እና ተመልሼ ወደ ቤት ገብቼ ማረስ ጀመርኩ። ነገር ግን የእናቴ ወንድም ስመ ጥር የቅኔ መምህር በመሆናቸው ‹‹ይህ ልጅ ጎበዝ ነው ይፈቀድለት እና ምግቡን እኛ እንችላለን ቅኔ ይማር›› ብለው አባቴን ጠይቆ። አባቴ ‹‹ልጄ ድቁና ይበቃዋል። ደብተራ እንዲሆን አልፈልግም እርሻውን ይረስ›› አሉ። አጎቴ ቅኔ እንድማር በጣም በመፈለጋቸው ጥያቄያቸውን አላቋረጡም። አባቴም እየቆዩ ማሰብ ጀመሩ።

የአጎቴን ጉትጎታ ምክንያት አድርገው አባቴ ለአንድ ዓመት እንድማር ሲፈቅዱልኝ እኔ አልፈልግም አልኩኝ። ነገር ግን ከሁለት ዓመት በኋላ የትምህርት ፍላጎቴ አገረሸብኝ። ተማሪዎች ድጓና ጾመ ድጓ ሲማሩ፣ በቤተክርስቲያን ማኅሌታዊ መሆን እና ቅኔውን መቀኘት እንደ ገና በአእምሮዬ ይመላለስ ጀመር። አልፈልግም ያልኩትን ትምህርት እንደገና ልጀምር ማለት ከባድ ሆነብኝ። ስለዚህ ሰኔ ላይ ከመስቀል በኋላ ጠፍቼ እማራለሁ ብዬ በመወሰኔ ለልብሴ እና ለሌላውም ነገር ገንዘብ ያስፈልገኛል ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ የአባቴንም ሆነ የእናቴን ገንዘብ የምታስቀምጠው እናቴ ናት። የምታስቀምጥበትን ቦታ አጥንቼ፤ በ1973 ዓ.ም መስከረም 29 ቀን 50 ብር ይዤ ከቤተሰቦቼ ቤት ወጣሁ።

በአውራጃችን መሪጌታ ፍሬ ሕይወት በየነ የሚባሉ ጣንቋ ምላሽ አርባህቱ እንስሳ (ጣሽማሊኽ አርባሃቱ እንስሳ) ይባላል። እርሳቸው ዘንድ የቃል ትምህርት ጀመርኩ። መሠረታዊ የዜማ ትምህርት ማለት ነው። ከውዳሴ ማርያም ጀምሮ እስከ ሠልስቱ በቃል መያዝ ያስፈልጋል። ያንን ካልተማሩ ዜማው አይገፋም፤ ዜማን በደንብ ማወቅም አይቻልም። ዝግ ይሆናል። ስለዚህ ለስምንት ወር እርሳቸው ዘንድ ተማርኩ። በመቀጠል አቋቋም የሚባል ትምህርት ለመማር አበር ገሌ ውስጥ ፂርባህ ተክለ ሃይማኖት በጣም ትልቅ መምህር ነበሩ፤ እዚያም ተማርኩ። አማራው፣ ትግሬው፣ ከፀለምትም፣ ከአገውም፣ ከትግራይም፣ ከበለሳም ከሁሉም ቦታ የሚመጣው ሌላ ሌላውም ሁሉም የሚማርበት ነበር። መምህር ዘፈረ ብርሃን ይባላሉ። ወደ እርሳቸው ሔድኩ። በመሪጌታ ደረጃ ያሉ የሚማሩበት ነው። ቀናኝና እዚያም በደንብ ተማርኩ። ሌሎቹ ትልልቅ ሆነው እኔ ሕፃን ስለነበርኩ እና የሕፃንነት ድምፅ ያምር ስለነበር መምህሩ በጣም ወደዱኝ። ትምህርታቸውም ግልጽ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ለማወቅ ብዙ አላዳገተኝም። አቋቋም የሚባለውን ትምህርት ለየሁ።

በ1975 ዓ.ም በደርግ እና በኢሕአዴግ መካከል በነበረው ጦርነት ምክንያት እንደልብ መንቀሳቀስ አይቻልም ነበር። በዚያ አካባቢ የፈለግኩትን ትምህርት መማር እንደማልችል ተረዳሁ። የትምህርት ፍቅር አድሮብኝ ስለነበር ትምህርት አቁም የሚለኝን እንደ ጠላቴ አየው ስለነበር በቦታው አንዴ ደርግ ሌላ ጊዜ ኢሕአዴግ እየመጣ ያፈናቅለናል። እኔ ብቻ ሳልሆን ተማሪዎች ሁሉ መላ መፈለግ ጀመርን። ጎንደር ሰላም መሆኑን ስለሰማን ወደዚያ በመሔድ እንደ ልብ ለመማር ስለወሰንን ለጊዜው ወደ ቤተሰብ ተመለስኩኝ። ጎንደር ለመግባት በእግር መሔድ ከባድ አደጋ ያስከትል ነበር። ዙሪያው እሳት ነው። ገንዘብ ባይኖረኝም እወጣዋለሁ አልኩ። አማራጬ መቀሌ መግባት እና በአውሮፕላን ጎንደር መሄድ ነው።

መቀሌ ገብቼ መምህር ሚካኤል አቡነ ሰላማ ፍሪምናጦስ ዘንድ ለስምንት ወር ቆየሁኝ። ለተማሪ እየጻፍኩ መጽሐፍ መሸጥ ጀመርኩኝ። ሰዎች ጽሑፌን ወደዱልኝ። መምህራንም ተጠንቅቆ ስለሚጽፍ ጽሑፉ ጥሩ ነው አሉ። ጻፍልን የሚለው ሰው በጣም በዛ። አልጽፍም እያልኩ በጭቅጭቅ በከፍተኛ ገንዘብ መጻፍ ጀመርኩ።

የአውሮፕላን ትኬት መቁረጫ ገንዘብ ተገኘ። በ51 ብር ትኬት ከመቀሌ ጎንደር ገባሁ። ወገራ ወደሚባል ደንክር ልደታ መምህር መርሐ ጽድቅ ዘንድ ሔድኩ። አቋቋሙን አጠናቀቅኩ። ለመምህርነት ሳይሆን ለጥሩ መሪ ጌታነት በቃሁ። በመምህርነት ለመመረቅ ጎንደር ከተማ ገባሁ። ጎንደርም በተመሳሳይ በልመና ሳይሆን ትምህርቴን ሳልጎዳ በመጻፍ ቀለቤን ቻልኩ። ትንሽ እየተለማመድኩ ስሔድ ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጀመርኩ። የ11 ብር ደሞዝተኛ ሆኜ ትምህርቴንም ሥራዬንም ቀጠልኩ። በተለይ ደጀ ሰላም ላይ የሚገኘው እህል ውኃ ደጎመኝ፤ በሂደት በከተማው ዕውቅና አገኘሁ። እንደተማሪ ሳይሆን ቃለ እግዚአብሔርን ለይቷል ተብዬ ተለየሁ።

የማውቀው ዜማ ጥልቀት እንዲኖረው በሚል ፊት አቦ መምህር ሠመረ አብ ዘንድ ድጓ እና ጾመ ድጓ በአጭር ጊዜ ተማርኩ። ምክንያቱም መጀመሪያ ስለተከፈተ እርስ በራሱ ትምህርቱም እየተደጋገፈ ቀጠልኩ። እዚያው ጎንደር ሰለሞን ገብረ ሚካኤል ከሚባሉ መምህር ዘንድ ቅኔ ተቀኘሁ፤ ዝማሬ መዋሥዕት ሲቀረኝ እንደ ትልቅ ዩኒቨርሲቲ ከሚቆጠረው ጋይንት መሔድ ስላለብኝ ወደዚያ አቀናሁ። ልክ እንደ ዩኒቨርሲቲ የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የተለዩ ቦታዎች አሉ። በእነዚያም ዝማሬ በደንብ ተማርኩ።

ዙር አምባ፣ እስቴ መካነ ኢየሱስ እና ቤተልሔም የጀርመን ተራድኦ ድርጅት የትምህርቱን ታላቅነት አይተው ለተማሪ 10 ብር፣ ለመምህር ደግሞ 50 ብር ይከፈሉ ነበር። የዙር አምባ ካህናት እጅግ የተባረኩ ናቸው። እነርሱ ሳይበሉ ቀድመው ተማሪዎችን ያበሉ ነበር። እዚያ ከድፍን ኢትዮጵያ የመጣ ተማሪ አለ። የጎጃም፣ የጎንደር፣ የአስመራ፣ የወሎ፣ የሸዋ፣ የኢሊባቡር እና ሌሎችም የሰባቱም ክፍላተ ሀገራት ተማሪዎች ነበሩ። እዚያ ዜማ፣ አቋቋም ጎንደር፤ ቅዳሴ ደግሞ ደብረ ዓባይ ትግራይ መማር እና የብቃት ማረጋገጫ መያዝ የግድ ነው። ያ ሁሉ ተማሪ ግጭት እና ጠብ የለበትም። የምንተሳሰበው እንደ እናት ልጅ ነው። አሁንም የሚናፍቅ ሕይወት ነው። በዚያን ጊዜ አብረውኝ የተማሩ በየሀገሩ የተበተኑ ወዳጆች አሉኝ። የኢትዮጵያውያን አንድነት እና ወዳጅነት በትክክል የሚታይበት ቦታ ነው። ቤተክርስቲያን በፍቅር አንድ ያደረጋቸው ናቸው። አንድ ሰው ከታመመ ሁሉም ማድረግ ያለበትን ያደርጋል። ሲበላም በፍቅር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከቤተሰብ ጋር መገናኘት ቀረ? ቤተሰብ ተረሳ ማለት ነው?**

**ንቡረ እድ ኤልያስ፡-** ቤተሰቦቼ ጎንደር የሀገር መጨረሻ ስለሚመስላቸው መጥተው አልፈለጉኝም። ተማሪው በሙሉ ቤተሰቡን አያስታውስም። ትምህርቱ ሃያ አራት ሰዓት ነው። ቤተሰብ ከታሰበማ ትምህርቱም አይገባም። ከጋይንት በኋላ ወደ ጎንደር ሄጄ የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን በአፄ ፋሲል ዘመን የተገነባው ፊት ሚካኤል ሄድኩ። እዚያ ያሉት ካህናት ጾም ሲሆን፤ ጾመ ድጓ እቆምላቸው ስለነበር ያውቁኛል። ሰው ሲፈለግ እኔን መርጠው እየጠበቁኝ ነበር። በድጋሚ ወደ ጎንደር የሄድኩት ትርጓሜ መጽሐፍ ለመማር ነበር። ነገር ግን ሥራው ሲገኝ፤ ትምህርቱን እና የደብሩን መሪጌትነት አያይዤ መሥራት ጀመርኩኝ። ደመወዝ 30 ብር ተፈቀደልኝ። ከዚያ አቋቋሙንም ሆነ ዝማሬውን ማስተማር ጀመርኩ።

በመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም ትርጓሜ መጻሕፍትን ተማርኩ። የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳንን ትርጓሜ ከሊቀ ሊቃውንት እየተማርኩ እያስተማርኩ ለሰባት ዓመት እዚያው አገለገልኩ። ትርጓሜ መራቀቅ ስለሆነ የተለያየ ቦታ መማር ጥሩ ነው በማለት አፄ ፋሲል ግንብ ውስጥ ከምትገኘው ግምጃ ቤት ማርያም ሐዲስ ኪዳን ተማርኩ፤ ትምህርቴን ሳጠናቅቅ ጎንደር የመቆየት ፍላጎት አልነበረኝም። ምክንያቱም ጎንደር ብዙ ሕዝብ አለበት። ሰው ወደሌለበት ሔጄ አስተምራለሁ ብዬ ሳስብ በመሐል አዲስ አበባ የነበሩ ጓደኞቼ ጠሩኝ። አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ከመቀሌ በአታ ፣ ከአስመራ ደግሞ መንደፍራ የሚባል ቤተ ክርስቲያን መማሪያውን ኮሌጅ ልናደርገው በመሆኑ ኑ አሉ። ወደ መቀሌ ባደላም፤ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የተከፈተበት ጊዜ ስለነበር አንድ ጓደኛዬ ላገባ ስለሆነ እሑድ እንድትገኝ ብሎ ወደ አዲስ አበባ ጠራኝ።

በዚያ ጊዜ አባቶች እነ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ሊያስቀሩኝ ፈልገው ስለነበር ይዘው አሳመኑኝ። ጓደኛዬን ትቼ መሔድ እችል ነበር። በአባቶች ጥያቄ ግን ልቤ ተሰበረ። እዚያው ማስተማሬን ቀጠልኩ። በአብነት ትምህርት ቤት፣ በሰንበት ትምህርት ቤት እና በስብከተ ወንጌል ሳስተምር ቆየሁ። ዘመናዊውንም ትምህርት በመጀመር እዚያው ቅድስት ሥላሴ እስከ ስምንተኛ ክፍል፤ ምኒልክ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ እስከ 12ኛ ክፍል ተማርኩ። በልማት ሥራ፣ በሰበካ ጉባኤ አባልነትም ከትልልቅ ሰዎች ጋር አብረን ሰርተናል።

በአገልግሎቴም አባቶች ዓይናቸውን ይጥሉብኝ ነበር። ወደ ውጭም ኬንያ ጅቡቲ እየሄድን ሁለት ሁለት እየሆንን እናገለግል ነበር። ፍላጎቴ ዘመናዊ ትምህርቴን መቀጠል ነበር፤ ነገር ግን አልሆነም። በአባቶች ለትልቅ ሥራ ለቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ኮሌጅ ዋና ዲንነት ተመርጠዋል ተባልኩኝ። አባቶች ሹመው እምቢ ማለት አይቻልም። ማስተማር እና መማር ብቻ እንደምፈልግ ብገልፅም፤ ‹‹ግማሽ ቀን ትምህርት ግማሽ ቀን ሥራ እያሉ ግዴታዎን ተወጡ፤ ምክትል ጎበዝ ሰው ይሾምልዎታል›› ተባልኩ። ትምህርት ቤቱ ስለተበጠበጠ እባክዎ ያስተካክሉት የሚል ግዴታ ተጣለብኝ። በጥሩ ሁኔታ ሥራዬን ሠራሁ፤ ማስተካከል ያለብኝን አስተካከልኩ።

ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ለአክሱም ንቡረዕድ ተፈለገ። ለዚህ ቦታ እንደገና አባ ኤልያስ ይመረጡ ተባለ። አባቶች ተከፋፈሉ፤ ‹‹ቦታው ከባድ እሳት ያለበት ነው። አክሱሞች ለፓትሪያሪክ እንኳ የማይታዘዙ በመሆናቸው ይከብዳቸዋል›› የሚል ክርክር መጣ። በርግጥ አክሱሞች ጠንከር ያሉ ናቸው። መንግሥትነትም፣ ክህነትም፣ መቀባቱም የሚሰጠው ከእዛ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ‹‹ክርስቶስ በሞቱ ፍቅሩን ገልጾ ይቅር እንዳለን...



ከ6ኛው ገጽ የዞረ

ነበር። ሌላ ቦታ የነገሠ እንኳ አክሱም ሄዶ እውቅና ካላገኘ የጽዮን ንጉሥ ካልሆነ በወንጌል ወርቅ ስሙ ካልተጻፈ እርሱ የኢትዮጵያ ንጉሥነቱ አይታወቅም። ይህ ከድሮ የመጣ ሥርዓት ነው።

የትኛውም ንጉሠ አክሱም የሚገባው በፈረስ ሳይሆን በእግሩ ነው። የአካባቢው ሰው ተመርጦ ነገሥታቱን እግራቸውን ያጥባል። ነገሥታት ደግሞ በአክሱም አያዝዙም። ነገሥታቱ የሚሸልሙትን እዚያው ይሸልማሉ። አብልተው አጠጥተው፣ ርስት ጉልት ሰጥተው ጸልዩልን ከማለት ውጭ የሚሉት የለም። አክሱም የተሾመ የቤተክርስቲያን የሃይማኖቱን ብቻ ሳይሆን የመንግሥትም ሥልጣን የእርሱ ነው። ንቡረ እድ ማለት ደግሞ ሁለተኛ መንግሥት ማለት ነው። ስለዚህ እዚህ ቦታ ላይ እንዳገለግል በ1995 ዓ.ም ደብዳቤ ወጥቶ ለንቡረዕድነት ተመረጥኩ። ሊቀ ጳጳሱ ራሱ ከሕዝቡ ጋር ሆድ እና ጀርባ ሆነው በመስቀላቸው አንሳለምም እስከ ማለት ተደርሶ ነበር። ያንን ፈተና ለመፍታት ከመስተዳድሩም ሆነ ከክልሉ ጋር ብዙ ሴሚናሮችን በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ሞከረን፣ ተሳካልን። እዛም ለሶስት ዓመታት ቆየሁ። ሁሉም ተስማምቶ ወደ ነበረበት ቦታ ተመለሰ። በመቀጠል ጠቅላይ ቤተ ክህነት ምክትል ሥራ አስኪያጅ ተብዬ መጣሁ። ለሰባት ዓመታት ስሠራ ቆይቻለሁ። እዚህ ላይ ትምህርቴን በመቀጠል በማኔጅመንት የመጀመሪያ ዲግሪ ተመርቅኩ። ቀጥዬ የሁለተኛ ዲግሪዬንም በቲዎሎጂ አጠናቅቄያለሁ። በትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅትም ሥራ አስኪያጅ ሆኜ ሰርቻለሁ። ቤቶች እና ሕፃናት አስተዳደርም ሥራ አስኪያጅ ሆኜ አገልግያለሁ። አሁን የቤተክርስቲያናችን ስትራቴጂክ ፕላን ኃላፊ ሆኜ እየሠራሁ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በክርስትና የተለያዩ አጽዋማት አሉ። አሁን ያለንበትን የጾም ወቅት ከሌሎቹ አጽዋማት ለየት የሚያደርገው ምንድን ነው?**

**ንቡረ እድ ኤልያስ፡-** ጾመ ሁዳዴ፣ ጾመ አርባ፣ ጾመ ኢየሱስ፣ ዐቢይ ጾም ይባላል። በክርስትና እምነት ታላቅ ጾም ነው። ታላቅ የሚያደርገው ደግሞ ጾሙን እርሱ ጌታችን ራሱ በመካከላችን ተገኝቶ በተግባር የሠራው ነው። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ አራት ላይ ተጽፎ እንደሚገኝ አርባ ቀን እና አርባ ሌሊት ያለ እህል እና ውኃ ጾሟል። በጾሙ ዲያቢሎስን አሸንፏል። በመንፈስ እና በሥጋ ማሸነፍ ይለያያል። የሥጋ ማሸነፊያ ቁሳቁስ ድንጋይ፣ ጦር ወይም ሌላ መሣሪያ ያስፈልጋል። የመንፈስ አሸናፊነት ግን በሞራል የበላይነትን መቀናጀት ነው። ዲያብሎስ አዳምን እና ሔዋንን በጣለበት መንገድ ጌታችንን ለመጣል ፈልጎ ነበር። ዳያቢሎስ ጌታችን በጾሙ ጊዜ እንጀራ እንዲበላለት ለማንሳት ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ጌታ ‹‹ሰው በእንጀራ አይኖርም በእግዚአብሔር ቃል እንጂ›› ብሎ አሸነፈው። ‹‹የዓለምን ሀብት እሰጥሃለሁ ለእኔ ስገድልኝ አለው፡፡›› ይህንንም ጌታችን፤ ‹‹ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገድ ይላል›› ብሎታል። መላዕክት በእጃቸው እንዲያነሱህ ሰሎሞን ከሠራው ቤተ መቅደስ እናት ላይ ‹‹ውደቅ›› አለው፤ ጌታችን ግን መጽሐፍ አምላክህን አትፈታተነው ይላል አለው። በመጨረሻም ጌታ ሰይጣንን ሂድ አለው። አሁንም ማሸነፍ የሚቻለው በዚህ ሞራል ነው፡፡

ጌታችን የሰይጣንን ሃሳቦች በሙሉ ጣለ። የመጀመሪያው አዳም ተሸነፈ። ሁለተኛው አዳም ግን አሸነፈ። እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ በአሸናፊው አሸንፈናል። ጌታችን የጾመው አርባ ቀን ነው። እኛ ግን የምንጾመው 55 ቀን ነው። 10ሩ ቀን የሕማማቱ ጊዜ ነው። አርባው ቀን የሚያልቀው ያለፈው ሕማማት ከመግባቱ በፊት ያለው ዓርብ ነው። ከቅዳሜ ጀምሮ እስከ ሳምንቱ ቅዳሜ ስቃዩን የምናስብበት ነው።

ጌታችን የተሰቀለበት መስቀል ተማርኮ ነበር። አንድ ክንፉ እኛ ሀገር ግሸን ማርያም ቢኖርም፤ መጀመሪያ ከአራት ሳይከፈል ተዘርፎ ፐርሺያ የአሁኗ ኢራን ሄዶ ነበር። በዚያ ጊዜ ኢራኖች እየሩሳሌም ላይ ዘምተው ክርስቲያኖችን እና አይሁዶችን ጨፍጭፈው መስቀሉን ይዘው ሄደው ነበር። የቤዛንታይን መንግሥት የአሁኗ ቱርክ ትልልቅ የክርስትና ጉባኤዎች የሚካሔዱባት ሀገር ነበረች። ብዙ ሊቃውንት እነ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ እነባስልዮስ፣ እነጎርጎርዮስ ዘጠኙ ቅዱሳን በብዛት ከኢስታንቡል ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ ነበር። ከአክሱም መንግሥት ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው። ስለዚህ የቤዛንታይን መንግሥት (ቱርኮች) ከፐርሺያ ከአሁኗ ኢራን ጋር ለመዋጋት ጸልየው ተዋግተው መስቀሉን መልሰዋል። በዚያ ወቅት ለፈሰሰው ደም የአምስት ቀን ጾም ስለነበር ያ አሁንም ድረስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እየተጾመ ነው። እነርሱ ትተውታል እኛ ግን እስከ አሁን እየፆምነው ነው። በአጭሩ ይኸው ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የጾሙ ሳምንታት የተለያየ ስም አሳቸው፤ ስሞቹ ምንድን ናቸው? የስያሜያቸው ምክንያት ምንድን ነው?**

**ንቡረ እድ ኤልያስ፡-** ትክክል ነው። የፆሙ ወቅት በውስጡ ብዙ ክፍልፋዮች አሉ። የመጀመሪያው ሳምንት ዘወረደ ይባላል። ይህ ጌታ ለእኛ ሲል መውረዱን የምናስብበት ነው። ሁለተኛው ቅድስት ነው። ስለቅድስና ያተኩራል። ሰንበትን የሚያሳስብ ሲሆን፤ በዛ ምሳሌ በመንግሥት ሰማይ እረፍት እንዳለ ማሳያ ነው። ሦስተኛው ደግሞ ሙኩራብ ነው። ሙኩራብ አይሁዶች የሚያመልኩበት ቤተ አምልኮ ማለት ነው። የጸሎት መታሰቢያ ነው። በየሳምንቱ ቅዳሜ እየተሰበሰቡ ጸሎታቸውን የሚያካሂዱበት፣ ሃይማኖታቸውን የሚማሩበት፣ ሐዋርያት እና ጌታ ራሱ ሃይማኖቱን ያስፋፉበት ነው።

አይሁድ ማለት አማንያን ማለት ነው። ጌታም ከአብርሃም የመጣ ዘር ነው። የድንግል ማሪያም ልጅ ነው። ክርስትና የመጣው በአይሁዳውያን በኩል ነው። ለዓለምም ያዳረሱት አይሁዳውያን ናቸው። አይሁዳውያን ክርስቶስን የሰቀሉ ብቻ ሳይሆኑ የተቀበሉም ናቸው። አይሁዶቹ ጥበበኞች ናቸው። አይሁዶች በእስያ፣ በሮም፣ በግሪክ፣ በሰሜን አሜሪካ እና በአፍሪካ በሊቢያ በግብፅ በሱዳን በኢትዮጵያ በየመን በእነዚህ ሁሉ ሙኩራብ አቋቁመዋል። ይህ ለሐዋሪያት ምቹ መደላድል ፈጥሮላቸዋል። ይመጣል የተባለው መጥቶ ተሰቅሎ ሞቶ አድኖናል ማመን አለባችሁ ብለው አንዱ ሌላውን እያሳመነ ክርስትና ተስፋፍቷል። ስለዚህ ይህ ሳምንት በሙኩራብ መሲሁ እርሱ ነው ብለው ክርስትናን ያስፋፉ እነርሱ በመሆናቸው ይህንን ለማስታወስ በሙኩራብ ክርስትና እንደተስፋፋ ለማሰብ የተሰየመ ነው። አራተኛው ሳምንት መጻጉ ነው። ይህ ሳምንት ጌታችን በፈወሰው ለ38 ዓመት በሽተኛ በሆነው ሰው ስም የተሰየመ ነው።

በአጠቃላይ ግን በፈወሳቸው ባዳናቸው እና አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግራቸው እንዲፈታላቸው ጌታችንን ጠይቀው የተፈታላቸውን ለማስታወስ ነው። እዚህ ላይ ሙታንን እንዴት እንዳስነሳ፣ የተራቡትን እንዴት እንደመገበ፣ ቤተክርስቲያን እንዴት መሥራት እንዳለባት የሚያሳይ ነው። ጌታችን ለሐዋሪያት የሞቱትን አንሱ፣ የታመሙትን ፈውሱ፣ ለምጣሞቹን አንፁ፣ በነፃ ያገኛችሁትን በነፃ ስጡ፤ የተራቡትን አብሉ፤ የተጠሙትን አጠጡ፤ የታረዙትን አልብሱ፤ የሞተውን ቅበሩ፤ የታሠረውን እና የታመሙትን ጠይቁ እንግዳ ሲመጣ ተቀብላችሁ አስተናግዱ ብሏል። ይህ ሁሉ ማኅበራዊ ግዴታ ነው። ለዚህ ነው ቤተክርስቲያን እርሱን መሠረት ያደረገችው።

አምስተኛው ደብረ ዘይት ነው። ነገረ ምጻትን የሚያስታውስ ነው። ጌታ እንደሚመጣ የሚያስታውስ ሲሆን፤ መጥቶ ሰዎች ላይ እንደሚፈርድ የምናስታውስበት ነው። ሰዎች ይነሳሉ፤ ተነስተውም እንደየሥራቸው እንደሚፈረድባቸው እና እንደሚፈረድላቸውም የምናስታውስበት ነው። ስድስተኛው ገብርኄር ይባላል። ደግ እንደቃሉ የሚኖር ተሸላሚ አገልጋይ ማለት ነው። ሰባተኛው ኒቆዲሞስ ይባላል። በጣም የተማረ የአይሁድ አለቃ በነበረ ሰው ስም የተሰየመ ነው። ይህ ሰው የነበረበት ቡድን የእየሱስ ክርስቶስ ተቃዋሚ ሲሆኑ፤ እርሱ ግን ተለይቶ የክርስቶስ ደጋፊ ሆኖ በአስተውሎት ይከታተል ነበር። ይመጣል ብለን ስንጠብቀው የነበረው መስዑ እርሱ ነው። የሚል እምነት ስለነበረው በማታ ሄዶ ጌታ ጋር ትምህርት ይማር ነበር።

ክርስቶስ ስለጥምቀት አስተምሯል። ሰው ዳግመኛ መጠመቅ አለበት። መንፈሳዊነት ያስፈልጋችኋል። መንፈሳዊነት እና የእግዚአብሔር ልጅነት የሚገኘው በጥምቀት መሆኑን ያስተማረ መሆኑን በዮሐንስ ምዕራፍ ሶስት ላይ ተቀምጧል። እርሱን እናስባለን። ቀጥሎ ያለው ሆሳዕና ነው። ሆሳዕና ማለት ትርጉሙ መድኃኒት ማለት ነው። ቃሉ ግስም ስምም ይሆናል። ግስ ሆኖ ሲፈታ አሁን አድነን ማለት ነው። ስም ሲሆን ለዳዊት ልጅ መድኃኒት መሆን ይገባሃል የሚል ነው። ዓለም በትክክል መሲዑ እንደሚመጣ የሚረዳበት ነው።

መሲዑ በአህያ ላይ ይመጣል ተብሎ ተነግሯል። ያዕቆብ የሚመጣውን መሲዑን አንበሳ ብሎ ገልጾታል። ጌታችን ክንድህ በጠላት ደንደስ ላይ ነው። መንግሥትህ እና ገዢነትህ ከአንተ አይጠፉም ተብሏል። አህያውን በወይራ ያስራል። ልብሱን በወይን ኩታውን ደግሞ በወይን ደም ያጥባል ተብሏል። እየሱስ ክርስቶስ በአንበሳ የተመሰለው አሸናፊነቱን እና ኃያልነቱን ለማሳወቅ ነው። በጠላት ደንደስ ላይ ማለት ትከሻው በዲያብሎስ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ነው። መንግሥትነትህ የዘላለም ነው ፍፃሚ የለውም የተባለው ዘላለማዊ መሆኑን ለማሳወቅ ነው።

አህያውን በወይራ ያስራል የተባለውም አህያ ደግ እና ታዛዥ ናት። አህያ ምዕመናን ናቸው። ወይራው ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ምዕመናንን ያከብራቸዋል፤ ያነፃቸዋል ማለት ነው። ልብሱን በወይን ያጥባል፤ ኩታውን በወይን ደም ያጠራል ማለት በልብስ የሚመሰሉት እስራኤላውያን ሲሆኑ፤ በኩታ የሚመሰሉት ደግሞ ከእስራኤል ውጭ ያሉ እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰዎች ናቸው። እነዚህን ሁሉ ያጠምቃቸዋል፤ ያድናቸዋል ለማለት ነው። ይህ በራሱ ቅኔ ነው። እግዚአብሔር ራሱ የቅኔ መምህር ነው። ሆሳዕና ይህንን ሁሉ ለማሳወቅ የቀረበ ነው። ትንቢት የተነገረለት ይመጣል የተባለው መድኃኒት እርሱ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡

በዚህ ሳምንት በፊትም በኋላም በቀኝም በግራም ሽማግሌም ሕፃናትም ሴትም ወንድም ሁሉም ሰው ተከትሎት እያመሰገነ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቷል። ይህ ትንቢት የሚያሳየው ቤተመቅደሱ የመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ናት። የእርሱ ተከታዮች በሙሉ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገቡ የሚያሳይ ነው። ከዛ በኋላ ሰሞነ ህማማት ነው። ይህ ሰሞን የተቀበላቸውን መከራዎች የምናስብበት ነው። ሰኞ እና ማክሰኞ የአይሁድ ምክር ነበር። ‹‹እንግደለው፤ የለም ሕዝቡ ተቀብሎታል እና ሕዝቡ ይነሳብናል፤›› ብለው ሲከራከሩ ሰኞ እና ማክሰኞ ሳይስማሙ ቀሩ። ረቡዕ ግን እንዲገደል ተስማሙ። ለመግደል ቢስማሙም በዕለቱ ማድረግ አልቻሉም። ሐሙስ በሙሴ ጊዜ የተጀመረው የፋሲካ በዓላቸው ነበር። ስለዚህ ሐሙስ የፋሲካ በዓል ይለፍ ብለው ሐሙስ ማታ ግን ያዙት። ሌሊት ወደ ሊቀ ካህናቱ ጊቢ ወስደው ከሰሱት፤ ሲነጋ ደግሞ ሊቀካህናቱ የመፍረድ እንጂ የመግደል ሥልጣን ስላልተሰጣቸው የሮማ ወኪል ጲላጦስ ጋር ወሰዱት። ጲላጦስ በደል አላገኘሁበትም፣ ቢልም ሰሚ አጣ። ፖለቲካው እንዳይበላሽ ብሎ ፍርድ አዛባ።

ከአዳም ጀምሮ ሁሉም በአንድነት የእግዚአብሔርን መንገድ ስተዋል። አንድም እንኳን ከኃጢያት ያመለጠ የለም። ኃጢያተኛ ደግሞ ፍርድ አለበት። ስለዚህ ሁሉም ሊቀጣ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ቸር ነው። ሰዎችን ከቅጣት ለማዳን በእርሱ አሠራር ኃጢያታቸውን ይቅር ለማለት ቤዛነት ያስፈልጋል። ቤዛነት ኃጢያቱን የሚሸከም ተለዋጭ ነው። ምትክ ማለት ነው። ቤዛ የሚሆነው አካል ኃጢያት ያልሠራ መሆን አለበት። ሰው ሆኖ ደግሞ ኃጢያት ያልሠራ የለም። ስለዚህ ይህንን የሚችለው እግዚአብሔር ሰው ሆኖ በሰውነት አምላክ ሆኖ በእግዚአብሔርነት እርሱ ራሱ በጥበቡ የማይሞተው ለመሞት ሥጋ ለበሰ፤ ቤዛ ሆኖ በሰው ምትክ ሞቶ አዳነን።

ሞት ማለት ሥጋ እና ነፍስ ተለያየ ማለት ነው። በክርስትና እምነት የሰው ሞት ሥጋ ከነፍስ መለየት ነው። በሃይማኖት መንፈሳዊ እና ቁሳው ዓለም እንዳለ የታመነ ነው። እየሱስ ክርስቶስም ሥጋው እና መንፈሱ ተለየ። በነፍሱ ከአዳም ጀምረው ታስረው ወዳሉ ወደ ረቂቃን ነፍሳት ሄደ። ቤዛ ስለሆነላቸው ወደ ገነት አስገባቸው። በአምላካዊ ጥበብ የሞተውም ይቅር ያለውም እርሱ ነው። ፍርዱ እና አዳኝነቱን እንዴት እንዳደረገ የሚያሳይ ነው። እንደ አምላክነቱ ፈረደ፤ እንደ አባትነቱ ይቅር አለ። መሰዋዕት የሆነ፤ መሰዋዕት የተቀበለ፤ መሰዋዕት ያቀረበ እርሱ ነው። ይህ የአምላክ ረቂቅ ሥራ ነው። ከዛ በኋላም አሁንም ኃጢያት አለ። ነገር ግን በጥምቀት፤ በዕምነት፤ በደሙ ከሞት ጋር እንተባበራለን።

በትንሳኤው የመንፈስ ሞት የለም። ከሞት አዳነን የምንለው ከሥጋዊ ሞት ሳይሆን ከመንፈሳዊ ሞት ነው። እርሱም ‹‹አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ። › ብላል። እያንዳንዱ ክርስቲያን ሲሞት ነፍሱ በእግዚአብሔር እጅ ነው። ትንሣኤው ትንሳኤያችንን ማሳያ ነው። ሰው ትንሣኤ የክርስቶስ ሳይሆን የእርሱ ትንሣኤ መሆኑን ማሰብ አለበት። እግዚአብሔር እኮ አልሞተም፤ እንኳን እግዚአብሔር ሰይጣን እና መላእክት አይሞቱም። አያረጁም አይራቡም፤ አይጠሙም። የሞተው በለበሰው ሥጋ ብቻ ለእኛ ቤዛ ለመሆን ነው። ሞቱም ትንሣኤውም ለሰው ተብሎ ነው። ትሞታላችሁ ትንሣኤ አላችሁ ማለት ነው። በምጽአት ጊዜ ሙታን ተነሥተው ማለቂያ የሌለው ሕይወትን ይኖራሉ። በዚያ ማርጀትም ሆነ መታመም የለም።

**አዲስ ዘመን፡-በዓሉን በተመለከተ የሚስተላልፉት መልእክት ካለ?**

**ንቡረ እድ ኤሊያስ፡-** ይህች ዓለም ፈጣሪ እስከሚጠራን መቆያችን መሆኗ ይታወቃል። ዓለም እርስ በርሷ የምትተዛዘን የምትረዳዳ እንድትሆን አድርጎ አሳይቶናል። አሁን በሀገራችን የሰላም መደፍረስ ይታያል። ይህ ክርስቲያናዊነትን አይገልጽም። እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀገሩን አይወድም ለማለት አልደፍርም። አንዳንድ ሰው ብሶት ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን ኢትዮጵያን እወዳለሁ ማለት በቃል ሊሆን አይገባም። በተግባር መውደድ ያስፈልጋል። በዋነኛነት ኢትዮጵያ የሃይማኖት ሀገር ናት። ሁላችንም ፈጣሪን እንወዳለን። ሃይማኖተኞች መገዳደልን የሚያወግዙ እና መገዳደል እንዳይኖር የሚያስተምሩ ናቸው። በተለይ የኦርቶዶክስ እምነት እዚህ ላይ ጠንካራ ነው። የሚረግሙህን መርቅ ይላል፡ ፤ የሚያሳድዱህን ፀልይላቸው የሚል ነው። ማህተብ ያሰረ የገዛ ወንድሙን መግደል የለበትም። ይህ ሲታይ ንጹህ ክርስቲያን ነን ለማለት አያስደፍርም።

መጽሐፉ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን ጭራሽ የሰው ልጅን እንዳትገድል ይላል። ኢትዮጵያ ለእኛ አታንስብንም፤ ኢትዮጵያውያን ከሆንን እና በኢትዮጵያ ካመንን በድንበር የምንጣላበት ምክንያት የለም። ኢትዮጵያዊ ሆነን ለአንድ ወረዳ ድንበር መሬት መጋት የለብንም። ለማንም ኢትዮጵያዊ የኢትዮጵያ ምድር የእርሱ መሆኑን ማወቅ አለበት። ቦታው ለአስተዳደር ምቹነት ይከፋፈል ይሆናል። ከዚህ በተረፈ ሀገራችንን እያመሰ ያለውን ነገር ልብ ማለት ይገባል። ይህ ሁሉንም ይጎዳል። ስለዚህ የሁላችን ሀገር እንደሆነች አስበን መገንባት አለብን።

የሃይማኖት ተቋማትም ከማንኛውም ነገር ነፃ ሆነው የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ተከትለው ለሁሉም እኩል አባት ሆነው ማስተማር አለባቸው። ትልቋ ሀገር ረስተው በትንንሽ ነገሮች መጨቃጨቅ የለባቸውም። ነገሮችን በውይይት መፍታት አለባቸው። ይህቺን በተፈጥሮ ሀብቷ መተኪያ የሌላትን ሀገር በሰላም እንጠቀምባት። ሰፊ መሬት እና ምቹ አየር አለ። ስለዚህ ከመነጣጠል ይልቅ በሰላም እንኑር። የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ልሒቃን ማስተዋል አለባቸው። ይህ ሁሉ ችግር በ1960ዎቹ በተለይ የኢትዮጵያ እሴት እና ጸጋ ችላ በመባሉ የመጣ ጣጣ ነው።

ከአባቶች የወረስነውን ፀጋ በሙሉ አብዮቱ አሳጥቶናል። እምቢተኝነት እና አመፅ ፀረ ሃይማኖት ከእግዚአብሔር አርቆ እስከ አሁን እያናከሰን ነው። ይህንን ነገር ኢትዮጵያውያን ቆም ብለን ማየት አለብን። በለው ግደለው የሚባለው ቀርቶ ተወው አትርፈው፤ አፈሙዝ ቀርቶ ወንድሜ እህቴ መባባል አለብን። በውይይት ችግሮች መፈታት አለባቸው። የተበደለም ተካክሶ ለሃይማኖታችን፣ ለእሴቶቻችን፣ ለትውፊቶታችን ትኩረት ቢሰጥ እና ከአባቶች የመጣውን አጥብቆ መያዝ ቢቻል የተሻለ ውጤት ይገኛል። ስልጣኔ አይጠላም፤ ፍትሕ እና እኩልነት መኖር አለበት። እርቅ እና ይቅርታ መምጣት አለበት። የተበደለ የሚሸነፈው ሲካስ ነው። ይህ ፅድቅ ነው። ክርስቶስ በሞቱ ፍቅሩን ገልጾ ይቅር እንዳለን የይቅርታ ሰዎች እና የዕርቅ ሰዎች ብንሆን መልካም ነው። በዚህ መልኩ ትንሣኤን ማሳለፍ አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ እጅግ አመሰግናለሁ።**

**ንቡረ እድ ኤሊያስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ለአደጋ መንስኤ እንደሆንን ሁሉ መፍትሔውም እንሁን!

ታሪኩ ዘለቀ

በዓለማችን በአሁን ወቅት የብዙ ዜጎችን ሕይወት እየቀጠፉ ከሚገኙ ሰው ሠራሽ አደጋዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የትራፊክ አደጋ ነው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እኤአ በ2023 ያወጣው መረጃ እንደሚያመለክተው በዓለማችን በ24 ሰከንድ ውስጥ አንድ ሰው በትራፊክ አደጋ ሕይወቱን ያጣል። በየዓመቱ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በዚሁ አደጋ ሕይወታቸውን ያጣሉ።

በሁሉም የዓለም ክፍሎች የትራፊክ አደጋዎችን መስማት እየተለመደ መጥቷል። እነዚህ አደጋዎች የሕይወትና የንብረት እንዲሁም የአካል ጉዳትን በከፍተኛ ደረጃ እያደረሱ ይገኛሉ። ይህ አደጋ የማይመለሰውን የሰውን ሕይወት እየወሰደ ነው።

የትራፊክ አደጋ ቀላል የማይባል ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ቀውስ እያስከተለ ይገኛል። ትራንስፖርት አገልግሎት ከዜጎች እንቅስቃሴና ከተሽከርካሪዎች ዝውውር ጋር ተቆራኝቶ ባለመመራቱ እየደረሰ ያለው አደጋ በየቀኑ እየጨመረ ነው።

በኢትዮጵያም በአሁን ወቅት የትራፊክ አደጋ የብዙዎችን ሕይወት እየቀጠፈ፣ ብዙዎችን ለአካል ጉዳት እየዳረገ፣ የብዙዎች ሕይወት እያመሰቃቀለ፣ ሕፃናት ያላሳዳጊ አዛውንቶችን አለጧሪ ቀባሪ እያስቀረም ይገኛል። በተለያዩ ጊዜያት የትራፊክ አደጋ አሳሳቢነት ይነሳል፤ ግንዛቤ ለማስጨበጥም ሆነ አደጋውን ለመቀነስ ንቅናቄዎች ይከናወናሉ። ይሁን እንጂ ችግሩ የሚያስከትለው የሰውም ሆነ የንብረት ኪሳራ ማስቆም አልተቻለም።

የዓለም ጤና ድርጅት በየጊዜው በሚያወጣው ሪፖርት እንዳመለከተው በዓለም ላይ የትራፊክ አደጋ እየጨመረ ነው። ለመጨመሩ ዋነኛ ምክንያት እየሆኑ ያሉት ደግሞ እያደጉ ያሉ የሶስተኛው ዓለም ሀገራት ናቸው ብሏል። ሪፖርቱ እንደተቃርኖ ያነሳው እነዚህ የዓለምን ሁለት ሶስተኛ የሚያህል ሕዝብ የያዙ ሀገራት ያሏቸው የተሽከርካሪ ቁጥር አነስተኛ ቢሆንም በአደጋው ግን አንደኛ መሆናቸውን ነው።

የተሽከርካሪ ቁጥራቸው ከሕዝባቸው የሚልቅ አንዳንድ ሀገራት የትራፊክ አደጋ ምጣኔአቸው እጅግ ትንሽና የለም በሚባልበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ ትያዝ እንጂ የተሽከርካሪዎቿ ቁጥር አንድ ሚሊዮን እንኳ የሞላው በቅርቡ ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያ ከፍተኛ አደጋ ከሚያስተናግዱ ሀገራት ተርታ የምትመደብ ነች።

ይሄ ለምን ሆነ ተብሎ በየጊዜው ጥናቶች ይጠናሉ፣ አዋጅ፣ ሕግ፣ ፖሊሲ፣ መመሪያ፣ ደንብና የመሳሰሉትም ይረቃሉ፣ ይጸድቃሉ። ነገር ግን እራሳቸው መመሪያዎቹ ይሁኑ አተገባበራቸው ለውጥ ሲያመጡ አይታይም። ከሪፖርት ፍጆታ ከመዋል አላለፉም።

በ2015 በጀት ዓመት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በደረሱ የትራፊክ አደጋዎች 3 ሺህ 577 ሰዎች ሲሞቱ 5 ሺህ 818 ሰዎች ላይ ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት ደርሷል። ይህ ማለት ቢያንስ በየቀኑ 13 ሰዎች ይሞታሉ እንደማለት ነው። በንብረት ላይ በደረሰ አደጋ በቢሊዮኖች የሚቆጠር ሀብት ከጥቅም ውጭ ሆኗል።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቀነስ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ቢከናወኑም የትራፊክ አደጋን መስማት የእለት ተእለት ተግባራችን ሆኗል። ለእነዚህ አደጋዎች መበራከት ድርሻ አላቸው የሚባሉ አካላት አሉ።

በመጀመሪያ የአሽከርካሪዎች የባህሪ ችግር እንደሆነ በተለያዩ ጥናቶች ተረጋግጧል። ጥናቶች እንደሚሉት 68 በመቶው በአሽከርካሪዎች ችግር፣ ሁለተኛው ለአደጋዎች መከሰት 14 በመቶ ድርሻ የያዘው የተሽከርካሪ የቴክኒክ ችግር፣ ሶስተኛው የመንገደኞች የመንገድ አጠቃቀም ችግር፣ አራተኛው የመንገድ ችግር፣ ሌላኛው የአየር ፀባይ ሁኔታ የራሱ የሆነ ድርሻ አለው።

> **አሽከርካሪዎች፣ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛዎች፣ የተሽከርካሪ መርማሪዎች፣ ሕግ አስከባሪ አካላት ለሀገርና ለሕዝብ ቅድሚያ በመስጠት ውድ የሰው ሕይወትና የንብረት ውድመትን በማትረፍ 82 በመቶ አደጋን መቀነስ ይቻላል ማለት ነው**

የጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩት ለትራፊክ አደጋ መበራከት ምክንያት ከሆኑት ነገሮች መካከል የአሽከርካሪ ብቃት አለመኖር፣ ጠጥቶ ማሽከርከር፣ እንደ ጫት ያሉ አነቃቂ ነገሮች ወስዶ ማሽከርከር፣ የመንገድ ብልሽት ፣የተሽከርካሪ ብቃት ጉድለትና መሰል መንስኤዎች ናቸው።

ለአብነት ያህል በሀገራችን በ2014 በጀት ዓመት ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ የደረሰበት ሲሆን ከ40 ሺህ በላይ የትራፊክ አደጋዎች ተከስተዋል። ለእግረኞች ቅድሚያ አለመስጠት፣ ከፍጥነት በላይ ማሽከርከርና እርቀትን ጠብቆ አለማሽከርከር የሚሉት የትራፊክ ደንብ ጥሰቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ።

በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ስድስት ወራት በተከሰቱ የትራፊክ አደጋዎች 1 ሺህ 368 ዜጎች ሕይወትን ሲቀጥፍ 2 ሺህ 600 ሰዎች ከፍተኛ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል። በዚህም የትራፊክ አደጋ ከ1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ብር በላይ የንብረት ኪሳራ ማድረሱም ታውቋል።

በኢትዮጵያ በአማካኝ በየቀኑ ቢያንስ 13 ሰዎች በትራፊክ አደጋ ምክንያት ሲሞቱ 31 ያህሉ ደግሞ ከባድ የአካል ጉዳት እንደሚያስተናግዱ መረጃዎች ይነግሩናል። 68 ነጥብ 1 በመቶ ያህሉ አደጋዎች የሚከሰቱት ምቹ በሆኑ መንገዶች መሆኑ ሲሰማ በራሱ ለምን የሚል ጥያቄ እንዲነሳ ያስገድዳል። ዝቅተኛ የተሽከርካሪ ቁጥር ያላት ከፍተኛ የትራፊክ አደጋ የሚከሰትባት ሀገር የሚል ቅፅል የሰጧትም አልጠፉም፤ ለኢትዮጵያ።

ይህ ለምን ሆነ ሲባል ብዙ ምክንያቶችን ማንሳት እንችላለን። በቁጥሮች ማስረጃነት ስንመለከት 68 በመቶ በአሽከርካሪዎች ብቃት ማነስና ቸልተኝነት የሚመጣ አደጋ እንዲሁም 14 በመቶ ደግሞ በተሽከርካሪ ቴክኒክ ምክንያት የሚደርስ ነው። አሽከርካሪዎች፣ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛዎች፣ የተሽከርካሪ መርማሪዎች፣ ሕግ አስከባሪ አካላት ለሀገርና ለሕዝብ ቅድሚያ በመስጠት ውድ የሰው ሕይወትና የንብረት ውድመትን በማትረፍ 82 በመቶ አደጋን መቀነስ ይቻላል ማለት ነው።

ከትራፊክ አደጋዎች መበራከት ጋር ተያይዞ የደንብ አስከባሪዎችና የትራፊክ ባለሙያዎች የክትትልና የቁጥጥር ሥራ መላላት አስተዋፅኦ አለው። ባለሙያዎች ከአሽከርካሪዎች ጋር በመመሳጠር ደንብንና ሥርዓትን ከማስከበር ይልቅ በሕገ ወጥ መንገድ የግል ጥቅማቸውን ሲያሳድዱም ይስተዋላል። ታዲያ የሕግ የበላይነትን ከማስጠበቅ በኩል የአሠራር ጥሰቶችን በሚፈፅሙት ላይ ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

በእጆቻችን የምንይዛቸው መኪኖች ያለብንን ኃላፊነት መወጣት እንድንችል ቀድሞ ጥያቄ የሚነሳባቸው ናቸው። በሰላም ወጥቶ መግባት ለነገ የተቀመጠ ትልቅ ህልም ማሳካት፣ ለሌሎች ሀዘን ተጠያቂ ለመሆን ይህንን እና ከፀፀት የፀዳ ቀንን እንድናሳልፍ ሁላችንም ኃላፊነታችንን መወጣት አለብን።

ከዓመታት በፊት የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ የፍጥነት ወሰንን መነሻ አድርጎ ለውጥ ለማምጣትም በመንግሥት ደረጃ መጀመሩ እናስታውሳለን። ለተከታታይ ዓመታትም ንቅናቄው ስለመካሄዱ አይረሳም። ይህ የ‹‹እንደርሳለን›› ዘመቻ ያመጣው ውጤት ምንድነው? የት ደረሰ? ቀጣይስ ምን መሠራት አለበት? የሚሉና መሰል ጉዳዮችን አንስቶ ምክክር ማድረግ ያስፈልጋል።

የትራፊክ አደጋ ሀገርና ሕዝብ እያደረሰ ካለው ተያያዥ ቀውሶች አንፃር ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ህብረተሰቡም ከመዘናጋት ሊወጣ በጥንቃቄ ሊጓዝ ይገባል። ሁላችንም ዛሬ በወሬ የምንሰማው ነገ ላይ በእኛና በቤተሰባችን ላይ ሊደርስ ከሚችለው አደጋ ራሳችንን ለመጠበቅ ሌላውንም ለመጠበቅ ካሁኑ ሥራ መጀመር አለብን።

በአሽከርካሪዎች ምክንያት የሚደርስ አደጋ አንድም ሕጉን በሚገባ ባለማወቅ የሚከሰት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በአሽከርካሪ ቸልተኝነት ወይም ትኩረት ባለመስጠት ምክንያት የሚፈጠር ነው። በዚህም ብቁና ሕግ አክባሪ አሽከርካሪዎች በማፍራት ብቻ ሊደርስ ከሚችለው የትራፊክ አደጋ 68 በመቶውን መቀነስ እንችላለን ማለት ነው። ስለዚህ ብቁና ሕግ የሚያከብር አሽከርካሪ ማፍራት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ይጠበቃል።

ለጥቂት ጊዜ ለውጦችና ቁጥጥሮች ይታዩና ተመልሶ ወደነበረበት አዘቅት ይወርዳል። ዋና ከተማዋን ጨምሮ በሁሉም አካባቢዎች ተሽከርካሪዎች ከአቅማቸው በላይ ሲጭኑ የሚቆጣጠራቸው አካል የለም። ከስንት አንድ ቢገኝ እንኳ ብጣሽ ሳንቲም ተቀብሎ፣ የራሱንም ክብር አዋርዶ፣የሰውንም ሕይወት ክብር አውርዶ ተሽከርካሪውን ለውድመት ተሳፋሪውን ለሞት ወደሚዳርገው አደጋ ይነዳዋል።

ለእነዚህ አደጋዎች መንስኤ ከአሽከርካሪው ጀምሮ፣ ተሳፋሪዎች፣ ተቆጣጣሪዎች ሁላችንም ነንና መፍትሔውም የጋራችን መሆን አለበት። ቁጥጥሩ እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት እንጂ ኪስን ለማደለብ እንዳይሆን የአሽከርካሪ ብቃት በየጊዜው ቢመዘን፣ ጉዳት ካደረሰም የማያዳግም ወስዶ መንጃ ፍቃዱን እስከመጨረሻው እስከመንጠቅ ድረስ መድረስ ቢቻል፣ ጥፋተኛ ተሳፋሪና እግረኞችም የሚቀጡበት መንገድ ቢመቻች፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ በዘመቻ ሳይሆን በተከታታይ ለውጥ የሚያመጣ ትምህርት ቢሰጥ አደጋው የማይቀንስበት ምክንያት አይኖርም።

በቁጥጥር ስራውም የደህንነት ቀበቶ መመሪያ በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል፣ራዳርን በመጠቀም ከፍጥነት በላይ የሚያሽከረክሩ አሽከርካሪዎችን መከታተል፣ ፎርጅድ የመንጃ ፍቃድን መቆጣጠር፣ ከመናኽሪያ ውጪ የሚጭኑ ተሽከርካሪዎችና በተመረጡ አካባቢዎችም ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ በማድረግ የቴክኒክ ጉድለት ያለባቸውን የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።

ሰውን ያህል ትልቅ ፍጥረት ይዞ ለመጓዝ የተዘጋጀ አሽከርካሪ የተሰጠውን አደራ በአግባቡ መወጣት ከቻለ፣ ታሞ ችግር አጋጥሞት አሊያም በተለያየ ምክንያት ሕክምና ፈልጎ በቴክኒክ ብቃት ቁጥጥር ተቋም የተገኘ ተሽከርካሪ ደህንነት በማረጋገጥ በኩል ደግሞ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች ሌላው ቀርቶ በዚህ መኪና የእኔ ሰው ሊጓዝ ይችላል የሚል የህሊናን ጥያቄ መመለስ ከቻሉ፣ በእግሩ የሚንቀሳቀሰው ነዋሪም ለደቂቃ መቆም ተስኖት፣ ትእግስት ርቆት ራሱን ለአደጋ ማጋለጥ ቢቆጠብ፣ እኔ ልቅደም እኔ ልቅደም ዓይነት ያልተገባ እሽቅድምድም በመንገዶች ላይ የሚያደርጉ አሽከርካሪዎች ከዚህ ተግባራቸው መታቀብ፣ ልንገለገልባቸው በራሳችን በተፈጠሩ ተሽከርካሪዎች ምክንያት መሞታችን፣ ጉዳት ማስተናገዳችን መቀነስ ከፍ ሲልም እስከ ወዲያኛው ማስቆም እንችላለን።

# ተናጋሪው ዶሴ

# የግድያው ሚስጥር ፍቅር ወይስ ጥላቻ?

**አስመረት ብስራት**



የዖታዊ ፍቅር አተያይ አንዱ ከሌላው የሚለያይ ቢሆንም፤ አንዳንድ ሰዎች ግን ፍቅርን ቃላትም ሆነ ጽሑፍ አይገልጸውም ሲሉ ረቂቅነቱን ለማሳየት ይሞክራሉ። በውስጥ ስሜት የሚገለጽ ነው ይላሉ። አንዳንዱ ፍቅሩን በውስጡ ይዞ ለሚወደውም ሰው ሳይነግር፣ የቅርቤ ናቸው ለሚላቸው ሰዎች እንኳን ስሜቱን ሳያካፍል ለብቻው ይብሰከሰካል። በፍቅር የተነሳ የሚያለቅሱ፣ የሚያዝኑ፣ እስከ መታመም ደረጃ ይደርሳሉ። ሕመማቸውም ፀንቶባቸው የአእምሮ ታማሚ የሚሆኑም ይኖራሉ።

ፍቅር ከባድ የሆነ ስሜት ያለው፤ በስቃይ፤ በስብራት፤ በደስታና ሀዘን ይገለጻል። በሰዎች ዘንድ ጠንካራና ጀግና ነው ተብሎ የሚነገርለትን ሰው እንኳን የማንበርከክ አቅም አለው። ፍቅር በብዙዎች ላይ ኃያልነቱን የሚያሳይ እንደሆነ ቢታወቅም፤ ስሜታቸውን ግልጽ አድርገው ላፈቀሩት ሰው ፍቅራቸውን በመግለጽ እፎይታ ለማግኘት የሚሞክሩም አይጠፉም።

በፍቅር ውስጥ ስቃዩንም የሚያጣጥሙት አሉ። ከብዙ ስቃይ በኋላ የሚገኘው ፍቅር ጣዕም አለው የሚሉ አይጠፉም። በተቃራኒውም ፍቅርን በማጣጣል አሳንሰው ለማየት የሚሞክሩም አሉ። የተለያዩ ሰዎች ለፍቅር የተለያየ ትርጉም እና ድምዳሜ የሚሰጡት ለዚህም ነው። እዚህ ላይ ፍቅር መስጠት እንጂ መቀበል እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። ሆኖ መገኘት እንጂ በማስመሰል ለራስ ትልቅ ግምት በመስጠት የሚገለጽ መሆንም የለበትም።

ፍቅር አንዱ ለሌላው ማሰብን እንጂ ሞትና ስቃይ መመኘት፣ ለመግደል መነሳሳት መሆን የለበትም። ፍቅር ደስታን በሚሰጥ ዓለም ውስጥ ተያይዞ መስመጥ እንጂ መለያየትን አይወክልም። አንዱ ለሌላው ደስታ መጨነቅ ማበሳጨት አይደለም። በታላቁ መጽሐፍ ላይ እንደተገለፀው፤ ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም። አይመካም፤ አይታበይም። የማይገባውን... በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ነሐስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል ሆኜአለሁ በሚልም በመጽሐፉ ሰፍሯል። በዚህ መልኩ የተሞካሸው ፍቅር ለምን ባልተገባ መንገድ ይገለፃል? የሚል ጥያቄ ይፈጥራል።

በፍቅር ሰበብ አንዱ በሌላው ላይ ጭካኔ በተሞላበት መንገድ የአካልና የሞት ጉዳት ሲያስከትል ይስተዋላል። ስለፍቅር ጉዳይ ለጽሑፌ መነሻ የሆነኝ በአዲስ አበባ ከተማ ፖሊስ መዘገብ ላይ የሰፈረው መረጃ ነው።

ለዛሬ ያቀረብንላችሁ ተናጋሪ ዶሴ «ከእኔ ጋር በፍቅር ጓደኝነት ለመቀጠል ፈቃደኛ አልሆንሽም» በሚል አስገድዶ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በመፈጸም ሕይወቷ እንዲያልፍ በማድረግ በአንዲት ሴት ላይ ተደራራቢ በደል ስለፈፀመ ግለሰብ ታሪክ ነው። ታሪኩ እንደሚከተለው ነው።

### አስጨናቂው የፍቅር ጥያቄ

ቁመቱ አጠር፣ ደልደል ያለ ሰውነት ያለው ወጣት ነው። ተክለ ሰውነቱና ገጽታው በአጠቃላይ ዓይነ ግቡ የሚባል ዓይነት ሰው ነው። ፍቅረኛ ቢሆን የሚጠላ ዓይነት ወንድ አይደለም። ከታሪኩ መረዳት እንደሚቻለው የፍቅር ትርጉም የሚገባው ሰው አይደለም። ፍቅርም ይዞት አያውቅም። ከእለታት አንድ ቀን በጠዋት ወደ ሥራ ጣደፍ ጣደፍ እያለ በመሄድ ላይ ሳለ ነበር የቀይ ዳማ ለግላጋ ወጣት ከፊት ለፊቱ የተመለከተው።

እንዳያት ልቡ ደነገጠ። ወጣቷ ታምራለች፤ የሆነ ተአምራዊ ውበት ያላት ሴት ሆና ታየችው። ዓይኑን ከሷ ላይ መንቀል ተሰኖት አፉን እንደከፈተ አጠገቡ ስትደርስ በዓይኑ ተቀብሏት አፉን ሳይዘጋ በዓይኑ ሸኛት። ልክ ከዓይኑ ስትሰወር ከገባበት የቁም ቅዠት ባነነ። ያቺ ለአፍታ አይቷት ያፈዘዘችውን ወጣት ሙሉ ቀን ሲያስባት ከአእምሮው ውስጥም ሳትወጣ ቀኑን ዋለ።

ከሥራ ሲመለስ፤ ጠዋት ላይ ወጣትዋን ያየት ቦታ ቆሞ እስከ ምሽት ጠበቃት። ተስፋ ቢያደርግም አላገኛትም። በነጋታው ጠዋት ሥራ አልነበረውም። በልቡ ውስጥ የቀረችውን ወጣት ለማግኘት ብሎ በተለመደው ቦታ ሄደ። እንደ ሞኝ በመንገዱ ላይ ቆሞ አመሸ። በዚህ ሁኔታ ሳምንቱን ሙሉ፤ ድንገት ያደነዘዘችውን ወብ ፊት ያላትን ልጅ ሊያገኛት ቀርቶ ሊያያት አልቻለም።

ከቀናት ጥበቃ በኋላ ተስፋ ቆርጦ ራሱን አረጋግቶ ሥራውን መሥራት በጀመረ በሳምንቱ ልጅቷን ድጋሚ በድንገት አያት። ዓይኑን ማመን ያቃተው ወጣት ያን ዕድል አላሳለፈም። ተከትሏት መኖሪያዋ ድረስ በመሄድ የት እንደምትኖር አረጋገጠ። በልቡ የተመኛትን ለቀናት ዓይኑ ላይ ተስላ ሌላ ምንም ነገር እንዳይመለከት የከለለችውን ወጣት መኖሪያ በማወቁ ግዳይ እንደጣለ ጀግና ዓይነት ስሜት ተሰማው። ልቡም በኩራት ተሞላ። ደስ አለው።

መኖሪያ ቤቷን ካወቀ በኋላ መመላለሱን ተያያዘው። ፍቅረኛዬ ካልሆንሽ ብሎ መውጫ መግቢያ አሳጣት። የፍቅር ጥያቄ አይሉት፣ ውትወታ ትንፋሽ አሳጣት። ተወዳጇ በበኩሏ ከአፍቃሪ ነኝ ባዩ ለመገላገል መንገድ ቀየረች። መውጫ መግቢያ ሰዓቷንም እየለዋወጠች አማራጮችን በሙሉ ብትሞክርም ወጣቱ ከቤቷ ደጃፍ ዞር ሊል አልቻለም። ማስጨነቁን ቀጠለ።

በቀላሉ በራሷ ልትወጣው አልቻለችም። ነገሩ ጠንከር ብሎ ግራ ሲገባት ለወላጆቿ ተናግራ ቢገስፁትም ቢያስፈራሩትም አሻፈረኝ አለ። "ወደድሽም ጠላሽም የኔ ነሽ " በማለት መዛትና ማስፈራራቱን ቀጠለ።

### ወጣትዋ የፍቅር ጥያቄውን ባለመቀበሏ የደረሰባት አሰቃቂ ድርጊት

የአሥራ ሰባት ዓመቷ ራህመት መሐመድ ተምራ ከፍተኛ ቦታ የመድረስ ህልም ያላት ልጅ ነበረች። በትምህርቷ በጣም ጎበዝ፣ በወላጆቿና በመምህራኖቿ የተወደደች ነበረች። የአሥራ አንደኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን፣ ከትምህርቷ ውጭ ያለውን ሰዓት ቤተሰቧን በማገዝ በመልካም ሥነ ምግባር የምትመራ ጠንቃቃ ተማሪ ናት።

ይህች ሁሉን አሟልቶ የሰጣት ይህ ቀረሽ የማትባል ወጣት ከእለታት በአንዱ ቀን አብዱ ኪያር ዩሱፍ የተባለ ወጣት ዓይን ውስጥ ገባች። ራህመት የፍቅር ግንኙነት ሃሳብ ያልነበራት ሙሉ ትኩረቷ ትምህርቷ ላይ ብቻ የሆነች ሴት ነበረች። እያንዳንዷን ሰዓት ወጤታማ የሚያደርጋትን ተግባር በማከናወን ታሳልፍ ነበር። እንኳን የፍቅር ጓደኛ ስለወንድ ማሰብ አትፈልግም ነበር።

የእርሷ ፍላጎት ምንም ይሁን ምን አፍቃሪዋ አፈቀርኩሽ ያላትን ልጅ ማግኘት የሞት ሽረት ጉዳይ ሆኖበት በኃይል ሊያገኛት ያቅድ ጀመር። ጠልፎ ለማስቀመጥና የልቡን ለመሙላት የወሰነው ይህ አፍቃሪ ራህመት ለብቻዋ የምትወጣበትን አሳቻ ሰዓት ለማወቅ አድፍጦ ሲጠባበቅ ቆየ። ያለወትሮው አፍቃሪ ነኝ ባዩ ሰው ከዓይኗ የተሰወረባት ራህመት "እፎይ ተገላገልኩ" በሚል ስሜት ዘና አለች።

ተመላልሶ ሲያቅተው የተዋት እንጂ ክፉ ነገር ያሰበባት አልመሰላትም ነበር። እንደሚወዳትና አብሯት መሆን እንደሚፈለግ ሲነግራት፤ በምንም ሁኔታ የእርሱ መሆን እንደማትችል አስረግጣ ስትነግረው የቆረጠለት መሰሏት ነበር። እንቢታው ከሚያርቀው ይልቅ እልህ ውስጥ የከተተው አፍቃሪ አድፍጦ ሲጠባበቅ ከቆየ በኋላ ከእለታት በአንዱ ቀን የጣለው ወጥመድ የሚፈልገውን ያዘለት።

ጭጋጋማ ቀን ነበር። በነጩ ችፍ ችፍ እያለ የዋለው ዝናብ እኩለ ቀን አካባቢ እንደመቆም ብሏል። ጳጉሜን 01 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 6፡30 ሰዓት አካባቢ ነበር። በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ሰፈራ ቀርሳ ቢላ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ጥጉን ይዞ ሲጠብቃት ቆየ። ዝናቡ ጋብ ሲል ራህመት ዣንጥላዋን ይዛ ከቤቷ ወጣች። ሳታስበው ከኋላዋ መጥቶ ያዛት። ባላሰበችውና የሰው እንቅስቃሴ በሌለበት ጭር ባለው መንገድ ላይ ያዛት። ራህመት ለመጮህ ስትሞክር በጠንካራ እጆቹ አፏን አፈነው።

ራህመት ከእኔ የፍቅር ጓደኝነት ጥያቄን ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነችም በሚል ምክንያት መንገድ ላይ ጠብቆ አንገቷን አንቆ በመያዝ በአካባቢው ወደሚገኝ ካባ እየጎተተ ወሰዳት። ራህመት ላለመሄድ ስትታገለው በለበሰችው ልብስ የወገብ ማሰሪያ ጨርቅ አንገትዋን አንቆ መሬት ላይ በመጣል በወደቀችበት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሊፈጽምባት ሲል ጩኸት ታሰማ ጀመር። በድጋሚ በልብስ ማሰሪያው ጨርቅ አንገቷን አጥብቆ በመያዝና እራስዋን እንዳትከላከል በማድረግ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ፈጸመባት። በድጋሚ አንገቷን በወገብ ማሰሪያ ጨርቅ በማነቅ ሕይወቷ እንዲያልፍ አደረገ።

በወቅቱ በርቀት ጉዳዩን የተመለከቱት የዓይን እማኞች በፍጥነት ሄደው ፖሊስ ለመጥራት ቢሞክሩም የወጣት ራህመትን ሕይወት ሊያተርፉ አልቻሉም። ፖሊስ በቦታው ሲደርስ ተጠርጣሪው አስከሬኑን ለመደበቅ ሲሞክር እጅ ከፍንጅ ተያዘ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ተጠርጣሪውን በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ ማድረግ ጀመረ። ተጠርጣሪው የእምነት ክህደት ቃሉን ተቀብሎ፤ የፎረንሲክ ምርመራውን አያይዞ የዓይን እማኞችን ቃል ተቀብሎ መረጃውን በተገቢው መልኩ አደራጀ።

ተጠርጣሪው በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶበት በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕግ አንቀጽ 620(2)(ሀ) እና (3) መሠረት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት እንዲቀጣ ሲል ማስረጃውን አቀረበ።

### የአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር

የፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት ጉዳዩን ተመልክቶ ፍርድ ቤት አቀረበ። የአቃቤ ሕግ የክስ ዝርዝር እንደሚያመለክተው ኪያር ዩሱፍ የተባለ ተከሳሽ በጳጉሜን 01 ቀን 2015 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 6፡30 ሰዓት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ሰፈራ ቀርሳ ቢላ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የ17 ዓመት የሆነችውን የግል ተበዳይ ከእኔ ጋር በፍቅር ጓደኝነት ለመቀጠል ፈቃደኛ አልሆነችም በሚል ምክንያት መንገድ ላይ ጠብቆ አንገቷን አንቆ በመያዝ በአካባቢው ወደሚገኝ ካባ በሚወስዳት ጊዜ ላለመሄድ ስትታገለው በለበሰችው ልብስ የወገብ ማሰሪያ ጨርቅ አንገትዋን አንቋታል።

መሬት ላይ በመጣል በወደቀችበት የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሊፈጽምባት ሲል የግል ተበዳይ ጩኸት ስታሰማ በድጋሚ በልብስ ማሰሪያው ጨርቅ አንገቷን አጥብቆ በመያዝና እራስዋን እንዳትከላከል በማድረግ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የፈጸመባት እና አንገቷን በእጅ እና በልብስ የወገብ ማሰሪያ ጨርቅ በማነቅ ሕይወቷ እንዲያልፍ በማድረጉ በአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ምርመራ ተጣርቶበት በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዘርፍ በሴቶችና ሕፃናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ዐቃቤ ሕግ ዳይሬክቶሬት በወ/ሕግ አንቀጽ 620(2)(ሀ) እና (3) መሠረት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ 11ኛ ወንጀል ችሎት ክስ ቀርቦበት ክርክር ሲደረግ ቆይቷል።

### ውሳኔ

በክርክሩ ሂደትም የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ከተሰማ በኋላ ተከሳሽ እንዲከላከል ብይን ተሰጥቶ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ ፍርድ ቤቱ በተከሳሽ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ በመስጠት በ25 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ወስኗል።

መዝናኛ
# ማረፊያ/ ትዝብት

## የማስታወቂያዎች ጉዳይ …

መልካምሥራ አፈወርቅ

በቅርቡ አንደ ወዳጃችን «በመንገዴ ታዘብኩት» ያለውን አንድ እውነት እየተደነቀ አጋራን። የሰማነው ጉዳይ ፈገግ ባያስብልም ሀሳቡን ያደመጥነው በጨዋታ አዋዝተን ነበር። እሱ እንደነገረን በእግሩ እየተጓዘ ሳለ ከአንድ ሕንጻ አናት ላይ የተሰቀለው አንድ ምስል ትኩረቱን ይስበዋል። ጠጋ ብሎ ሲያስተውለው በላዩ «የቁንጅና ማሰልጠኛ» የሚል ጽሁፍ ተለጥፎበታል። እይታው በዚህ ብቻ አልተቋጨም።

በጉልህ የምትታየው አንዲት ጥቁር ሴት ከፊል አካሏ ልብስ አልባ ሆኖ እርቃኗን ተጋልጣለች። ይህቺ ሴት በተራቆተ ሰውነቷ ምን ማስተላለፍ እንደተፈለገ ባይታወቅም የማስታወቂያው መለጠፍ ግን ቁንጅናና ውበትን ለሚሹ ሁሉ ስልጠና ለመስጠት መሆኑን ያመላክታል።

እኛም ይህን የአደባባይ ላይ ማስታወቂያ መነሻ አድርገን እየተስተዋለ ያለውን እውነታ በመጠኑ ዳሰስነው። እውነትም ጉዳዩ አሳሳቢ በሚባል መልኩ መረን መልቀቅ ጀምሯል። የዘመናችን ማስታወቂያዎች ያለ ሴቶች ድምቀት አይሰሩ ይመስል በእያንዳንዱ ጉዳይ እነሱን ስንቅር ማድረጉ ተለምዷል። እርግጥ ነው ሴት ልጅ ድንቅ ውበት ይገለጽባታል። እንዲህ ሲባል ግን የክቡር አካሏ ጥቅመኞች እንዳሻቸው ይዘዙባት ማለት አይደለም። አሁን ላይ በስፋት የሚስተዋለው ግን ይህን ሀሳብ የሚቃረን ሆኗል። ሴት የኮስሞቲክስ ማሳያ፣ ሴት የሳሙናና የልብስ አጠባ መገለጫ፣ ሴት የአጉል ዳንሶች መማረኪያ መሆኗ ብርቅ እየሆነ አይደለም።

ይህ ብቻም አይደለም። በእኛ አገር የማስታወቂያ ተሞክሮ ሴት ልጅ ከፍታዋ ሳይሆን ዝቅታዋ ብቻ የሚመሰከርባቸው መገለጫዎች ሞልተውናል። እንዲያም ሆኖ ከሚመለከታቸው አካላት የአሰራር መመሪያና ጠበቅ ያለ እርምጃ ሲተገበር አይስተዋልም። ከዓመታት በፊት ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶች አለመደፈናቸው ደግሞ ሌሎች በተቀደደላቸው ቦይ ኮለል ብለው እንዲፈሱ ምክንያት ሆኗል።

የማስታወቂያ ነገርን ስናነሳ በርካታ ጉዳዮችን መምዘዝ ይቻላል። አሁን ላይ ብዙዎች ራሳቸውን የሚገልጹበት፣ የስራ መስካቸውን የሚያሳዩበት አቋራጭ መንገድ የማስታወቂያው ዘርፍ ነው ለማለት ያስደፍራል። እንዲህ መደረጉ ክፋት የለውም። ማንነትን በቅጡ ለማሳየት የስራ ውደድርን በተግባር ለማውጣት ያግዛል። ምንም እንኳን በተለምዶ «ጥሩ ዕቃ ማስታወቂያ አያሻውም» ቢባልም ይህን ዘርፍ በአግባቡ ለተጠቀመበት ግን አስፈላጊነቱ አያጠያይቅም።

አንዳንዴ ደግሞ ሰዎች አውቀውም ይሁን ሳያውቁ በማስታወቂያቸው ያልተገቡ ጉዳዮችን ሲነካኩ ይስተዋላል። ለዚህ እውነታ አንድ ጉዳይን ልጥቀስ። ኢትዮጵያ የግብረሰዶማውያንን ዓላማና ድርጊት ከሚቃወሙትና ፍጹም ከማይደግፉት ሀገራት መሀል ግንባር ቀደሟ ናት።

በአንድም ይሁን በሌላ እነዚህ አካላት በዚህች ምድር ግብራቸውን ለማስፋፋት ያደረጉት ሙከራ አልተሳካላቸውም። እንዲህ ሲባል ግን በህጋዊ መንገድ አልጸደቀላቸውም እንጂ ጭራሽ የሉም፣ አልተስፋፉም ማለት አይደለም። እንደሚታወቀው ግብረሰዶማውያኑ ራሳቸውን የሚገልጹበት ዓርማና መለያ አላቸው። ይሁንታውን ባገኙባቸው ሀገራትም በመለያቸው ማንነታቸውን እያስተዋወቁ ዓላማቸውን ያስፋፋሉ።

የእነዚህ አካላት መለያ በህብረ ቀለማት የደመቀ ቀስተደመናማ መሳይ ነው። እዚህ ላይ የሚያውቁት ያውቁታልና ዝርዝር ሁኔታውን ማስፈር ተገቢ አይሆንም። አሁን ግን በአንዳንድ ማስታወቂያዎች በግልጽ እንደሚስተዋለው ይኸው ዓርማ የተለያዩ ቁሶች መለያና ማስታወቂያ ጭምር እየሆነ ነው። ይህ ማለት ደግሞ በሌላ አቋራጭ ዓርማና መለያው እየተዋወቀና ዓላማውን እያስፋፋ ነው ለማለት ያስደፍራል።

ይህን እውነት የሚያውቁ አንዳንዶች በማስታወቂያዎቹ መመሳሰል ጥርጣሬ ሊያድርባቸው ይችላል። ምናአልባትም ከዚህ አልፈው እያዩት ያለው ገጽታ በትክክል ምርታቸውን እያስተዋወቀ ነው ብለው አያምኑም ይሆናል። እንዲህ ቢያስቡ ደግሞ አይፈረድም። ተጽዕኖ ፈጣሪውን ጉዳይ ዓይናቸው ቀድሞ አይቷልና ዓይምሯቸው የሚቀበለውን ለይቶ ይመርጣል።

እዚህ ላይ ስለ ማስታወቂያዎቹ ተመሳስሎ ጥያቄ ቢነሳ «ሳላውቅ ነው» ይሉት ምላሽ ይሰራ አይመስለኝም። ምንአልባት በጉዳዩ ላይ አጥብቆ ጠያቂ ቢኖር የኃላፊነቱን ጉዳይ ንግድ ፈቃዱን ለሰጠው አካል ያሳልፈው ይሆናል። ይህ ክፍል ቢጠየቅ ደግሞ አስቀድሞ በተመሳሳይ ዓርማና መለያ ለሌላ አካል የሰጠው ይሁንታ እንደሌለ መናገሩ ግልጽ ነው። እንዴት ከተባለም ባለደማቅ አርማዎቹን እነ «እንትኔ» በህጋዊ ፈቃድ የሚንቀሳቀሱ አለመሆናቸውን ማሳወቁ አይቀሬ ይሆናል።

እንደ እኔ ዕምነት ግን ከዚህ ሁሉ ችግር ሰዎች በማስታወቂያቸው ከመንቀሳቀሳቸው በፊት አስቀድመው ሊያስቡበት ይገባል። ውሎ አድሮ በውጤቱ ላይ ስብራት ለሚያስከትልባቸው እንከንም ቅድመ -ጥናት ቢያድርጉ ኪሳራ አይገጥማቸውም።

በቅርቡ አንድ የሜካፕ ማስታወቂያ በተለያዩ ሚዲያዎች ሲንሸራሸር ተስተዋለ። ይህ ሜካፕ በአንዲት ሴት ከዋኝነት የተመራ ሲሆን ዋንኛ ግቡ ለሙሽሮች መዋቢያነት ተብሎ የተዘጋጀ ነበር። ከመልዕክቱ ለማወቅ እንደተቻለው ሙሽሪት በዕለተ ሰርጓ በቬሎ አምራ ስትወጣ ለመድመቂያዋ ዋንኛ ምክንያት በዚህ የፊት ክሬም መፍካትና መቅላት መሆኑን ለማሳየት ነው።

ይህን መልዕክት በታሰበው ልክ ተደራሽ ለማድረግ የበዛ ጥረት ስታደርግ የታየችው ሴት ውሎ አድሮ በግሏ ተቃውሞን ማስተናገዷ አልቀረም። ስለፊት ሜካፑ በጥልቀት እናውቃለን ያሉ በርካቶች ስለጉዳቱ በመረጃ ሲያብራሩ አልዘገዩም። እነሱን ተከትሎ ስለዚህ የመዋቢያ ሜካፕ አደገኛነት በወጉ ማስረዳት የያዙት የቆዳ ሀኪሞችም የጉዳዩን አሳሳቢነት ገሀድ ለማድረግ አስተማማኝ እማኞች ሆነዋል።

ይህ ሁሉ የግንዛቤ መነቃነቅ የተፈጠረው ማስታወቂያ ሲሰራ የራስን ጥቅም ብቻ በማስቀደም ስለሌሎች ማሰብ ያልተለመደ በመሆኑ ነው። ማስታወቂያውን ይዛ የወጣችው ሴትም ብትሆን የምታስተላልፈው ጉዳይ ምን ጥቅምና ጉዳት አለው የሚለውን እውነት ያሰበችበት አይመስልም።

ሁኔታው የሚፈቅደው ለሰርግና ለሙሽሪት ስለሆነ ብቻ ቬሎዋን ለብሳ በእርግጠኝነት «ሞክሪው» ብላ ስታውጅ ራሷ አድርጋውና አረጋግጣው እንደሆነ ማሳያዎች የሉም። ይህን ያስተዋሉ በርካቶች በሚተላለፈው መልዕክት እርግጠኝነት ተማምነው ምርቱን ለመጠቀም ዓይናቸውን እንደማያሹ መገመቱ ቀላል ነው።

በርካቶቻችን እንደምንረዳው ማስታወቂያ የራሱ የሚባል ኃይል አለው። በብዙዎች ዘንድ በዚህ ዘርፍ የተነገረና የታየ ሁሉ ትክክለኛና እውነተኛ ነው ተብሎ ይታመናል። በተለይ ጉዳዩን ታዋቂ ሰዎች የሚያስተዋውቁት ከሆነ የአሜኔታው ጥግ ወደር የለውም። ይህ አይነቱ ሀቅ ባለበት ሜካፕን የመሰሉ ምርቶች በብዙሀን ላይ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይሆንም።

ሜካፑን ከመጠቀም በኋላ ለሚደርሱ የቆዳና መሰል ችግሮች ማስታወቂያ አስነጋሪዎቹ ቢጠየቁ ደግሞ አንዳች ማስተባበያ አይኖራቸውም። ኃላፊነቱን ለመውሰድም የሚተባበሩ አይሆንም።

ብዙዎች እንደሚሉት በተለይ ሜካፕና መሰል መገልገያዎችን አስመልክቶ ወደ አፍሪካ የሚላከው ምርት እንደ መሞከሪያ የሚቆጠር ሸቀጥ ነው። ልክ ከሀገረ- ቻይና ለአውሮፓና ለአፍሪካ ተብለው እንደሚለዩት ይዘቶች ሁሉ የሜካፑም ጉዳይ በዚህ ደረጃ የሚታወቅ መሆኑ ይነገራል። ስለዚህ እውነት የሚያውቁም ይሁኑ «አናወቅም» ባዮቹ ሸቀጦቹን እንደወረደ ተቀብለው ኪስን በሚያሞቅ ትርፍ «እነሆ» ማለታቸው ተለምዷል።

ይህን የሸያጭ መድረክ በማስፋትና በማዳመቅ ታዲያ ትልቁን ድርሻ የሚወጡት የማስታወቂያ አካላት ናቸው። አብዛኞቹ ጉዳዩን ከስሩ፣ ሳያጣሩ ሳይመረምሩ ለትርፋቸው ብቻ መሯሯጥን ያውቁበታል።

የአንዳንድ ዕቃዎች ጥራትና የታዋቂነት ጣራም እንዲሁ ነው። በማስታወቂያ ጩኸትና ተጽዕኖ ተጠቃሚው እጅ ከገቡ በኋላ ውጤቱ እንደታሰበው ላይሆን ይችላል። ብዙ ግዜ እንዲህ አይነቱ አጋጣሚ ሲኖር አምራችና አከፋፋዮች፣ በዳግም ማስታወቂያ ችግሩን ለማሳወቅ ይሞክራሉ። የእኛም ጆሮ ቢሆን «በተመሳሳይ ምርት እንዳትታለሉ፣ የምርታችንን መለያና ዓርማ እወቁ» ወዘተ.. ይሉ አባባሎችን ለምደናል።

ማስታወቂያን በአግባቡ አውቀንና ተረድተን ከተጠቀምንበት ቱርፋቱ ለብዙሀን ይተረፋል። ዓላማችን ገንዘብና የተለየ ትርፍ ብቻ ከሆነ ግን እየከበርን ሳይሆን በእኩል እየከሰርን መሆኑን ልናውቀው ይገባል። ከምናገኘው ዕውቅና ይበልጥ ብዙሀንን ጎድተን የምናልፍበት መንገድ ደግሞ ምቹ ሊሆን አይችልም።

እንደ ግል ጥቅማችን ሁሉ ከብዙሀን አመኔታን ማግኘት ታላቅ መከበር ነው። ይህ እውነታም እንደ በዛ ትርፍ ይቆጠራል። እንዲህ መሆኑ ጥቂት አትርፈን በብዙ መክበርን ይመሰክራልና የሁልግዜውን ተግባራችንን መልካም ያደርገዋል።

# ዓለም አቀፍ

## የ 75 ሺህ ዓመቷ ኒያንደርታል ሴት ፊት ይፋ ሆነ

የሳይንስ ሊቃውንት የኒያንደርታል ሴት በሕይወት እያለች ምን እንደምትመስል የሚያሳይ አስደናቂ ምስል ይፋ አድርገዋል። ምስሉን መሠረት ያደረጉት ደግሞ በቁፋሮ የተገኘ ለስላሳ አጥንት ላይ መሆኑ ተገልጿል። ተመራማሪዎች አጥንቶቹን እንደገና ከመገጣጠማቸው በፊት ማጠናከር ነበረባቸው። በኋላም ባለሙያዎች ልዩ የ3ዲ ሞዴል ለማዘጋጀት በቁ።



ምስሉ 'የኒያንደርታልስ ምስጢሮች' በሚለው ዘጋቢ ፊልም ላይ ለዕይታ ቀርቧል። የዘጋቢው ፊልም ዓላማ ከ40 ሺህ ዓመታት በፊት ስለጠፉት የሰው ዘሮች ስለሚታወቁ ነገሮች ለመመርመር ነው። ቅርጹ ለእነዚህ ሰዎች ፊት ያዘጋጅላቸዋል።

"ከማንነታቸው ጋር እንድንገናኝ የምትረዳን ይመስለኛል" ሲሉ በኬምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ፓሌአትሮፖሎጂስት የሆኑት ዶክተር ኤማ ፖሜሮይ ተናግረዋል። "ከየትኛውም አካል ጋር መሥራት መቻል በጣም አስደሳች እና ትልቅ ዕድል ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

ሞዴሉ የተሠራበት የራስ ቅል በኢራቅ ኩርዲስታን ሻኒዳር ዋሻ ውስጥ የተገኘ ነው። እአአ በ1950ዎቹ ቢያንስ 10 የሚደርሱ የኒያንደርታል ወንዶች፣ ሴቶች እና ህጻናት ቅሪተ አካል የተገኙበት ድንቅ ቦታ ነው። እአአ በ2015 አንድ የብሪቲሽ ቡድን በኩርድ ባለሥልጣናት ግብዣ ቀረበለት። ብዙም ሳይቆይ ሻኒዳር ዚ የሚል ስያሜ የተሰጠው እና አከርካሪ፣ ትከሻ ፣ ክንዶች እና እጆችን ጨምሮ የግለሰቡን የላይኛው አካል ያካተተ አዲስ ቅሪተ አካል አገኙ።

የራስ ቅሉ ወደ 2 ሴንቲ ሜትር ገደማ ተጨፍልቋል። ይህም ከበርካታ ዓመታት በፊት ከዋሻው ላይ በወደቀ ድንጋይ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለ። በሻኒዳር አዲሱን ቁፋሮ የመሩት የካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲው ፕሮፌሰር ግሬም ባርከር "ራስ ቅሉ ልክ እንደ ፒዛ ጠፍጣፋ ነበር" ብለዋል።

"ከዚያ አሁን ወደምታየው መሸጋገር በጣም አስደናቂ ጉዞ ነው። አንዳንድ ጊዜ እንደ አርኪኦሎጂስት የተለየ ነገር ላታገኝ ትችላለህ። ያለፈውን ነገር በመዳሰስህም ትገረማለህ። ልዩ የሆነ ነገር ምን እንደሆነ እንረሳዋለን።" በአካባቢው የጥንታዊ ቅርሶች ቢሮ ፈቃድ፣ የራስ ቅሉ ስብርባሪዎች ወደ ዩናይትድ ኪንግደም ተወስደው እንዲገጣጠሙ የተደረገ። ውስብስብ የሆነው ሥራ ለማጠናቀቅ ከአንድ ዓመት በላይ ፈጅቷል።

የተገጣጠመው የራስ ቅሉ በየአቅጣጫው ፎቶ እንዲነሳ ተደረገ። ይህም በ3ዲ ህትመት ስመጥር ለሆኑት የደች አርቲስቶች አድሪ እና አልፎንስ ኬኒስ ተሰጠ። አርቲስቶቹ የጥንት ሰዎችን በ3ዲ በማዘጋጀት ተክነውበታል። ሴት መሆኗን እርግጠኛ ናቸው። የዳሌ አጥንቶች ለማረጋገጥ ቢረዱም ከላይኛው የሰውነት ክፍል ጋር አልተገኙም።

ይልቁንም ተመራማሪዎቹ ከሴት ዘረመል ጋር በተያያዙ እና ጥርስ ውስጥ በሚገኙ የተወሰኑ ዋና ዋና ፕሮቲኖች ላይ ተመርኩዘው ሴት መሆኗን አረጋግጠዋል። የቅሪተ አካሉ ቁመት አነስተኛ መሆኑም ድጋፍ ይሰጠዋል ተብሏል።

በ40ዎቹ አጋማሽ ላይ እንደሞተች ይገመታል። ይህንንም እስከ ሥሩ ድረስ በበሰበሱ ጥርሶቿ መለየት ተችሏል።"ጥርሶች በዚህ ደረጃ በሚበሰብሱበት ጊዜ እንደቀድሞው ማኘክ አይሆንላትም። በመሆኑንም እንደቀደመው መብላት አትችልም" ሲሉ ዶ/ር ፖሜሮይ ተናግረዋል።

"ሌሎች የጥርስ ጤንነት መጓደል ምልክቶች አሉ። አንዳንድ ኢንፌክሽኖች እና የድድ በሽታም ነበሩ። በወቅቱ ወደ ተፈጥሯዊ የሕይወቷ መጨረሻ እየደረሰች ነበር ብዬ አስባለሁ።" ነው ያሉት፡፡ኒያንደርታሎችን ከእኛ ዝርያ ጋር በማነጻጸር አደገኛ እና ያልተወሳሰቡ እንደሆኑ አድርገው ሳይንቲስቶች ለረዥም ጊዜ ይቆጥሩ ነበር።እነዚህ አመለካከቶች ግን በሻኒዳር ከተገኙት ቅሪተ አካሎች በኋላ መለወጣቸውን መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

ዋሻው የቀብር ሥርዓት ስለመኖሩ ማሳያ ነው። አስከሬኖች ከረዥም የድንጋይ ምሰሶ አጠገብ ባለው ጉድጓድ ውስጥ በጥንቃቄ ተቀምጠዋል። ሁሉም አስከሬኖች የተቀመጡበት መንገድ ተመሳሳይ ነው። አንዳንዶች እነዚህ ኒያንደርታሎች አበቦችን ተከትለው ዋሻዎቹ ውስጥ የገቡ ሊሆኑ እንደሚችሉ እንዲከራከሩ አድርጓቸዋል። ይህም ምናልባት መንፈሳዊ መነቃቃትን ወይንም ሃይማኖትንም ሊያመለክት ይችላል መባሉን ተመልክቷል።

የብሪታንያ ተመራማሪዎች ቡድን ግን የአበባው ብናኝ እዚያ የተገኘው ንቦች ወይም ደግሞ በአከስሬኑ ላይ ከተቀመጡ የአበባ ቅርንጫፎች ሊሆን እንደሚችል ያስባሉ። "በአበቦቹ ምክንያት ሳይሆን ቅርንጫፎቹ እራሳቸው ጅቦችን ወደ አስከሬኑ እንዳይገቡ መከላከል ይችሉ ነበር" ሲሉ የሊቨርፑል ጆን ሞሬስ ዩኒቨርሲቲ ባልደረባው ፕሮፌሰር ክሪስ ሃንት ተናግረዋል።

"ቀብር የሚለውን ቃል ለመጠቀም አልደፍርም። ከቀሳውስት እና ከቤተክርስቲያን ሃሳብ ለመራቅም 'ማስቀመጥ' የሚለውን ቃል የምጠቀም ይመስለኛል። ይህንን ወግ እንደያዙት ምንም ጥርጥር የለውም" ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

# የአዕምሮን ጦርነት ማሸነፍ

አስናቀ ፀጋዬ



በሕይወታችን እንዳንለወጥ ያደረጉን ጠላቶቻችን ብዙ ናቸው። በጣም የምንፈልገውና በሕይወታችን ውስጥ ልናሳካ የምንመኘው ነገር እውን እንዳናደርግ ወደኋላ የጎተቱን፣ የተግባር ሰው እንዳንሆን ያደረጉን፣ እጀምራለሁ ያልነውን እንዳንጀምር፣ የጀመርነውን እንዳንጨርስ የከለከሉን በርካታ ጠላቶች አሉ። አንዳንዶቹ ጠላቶቻችን አዕምሯችንን ተቆጣጥረውታል። እነዚህ ጠላቶች ሃሳብ ብቻ፣ ጭንቀት ብቻ እንዲኖረን፣ የናፈቅንን ለውጥ እንዳናይ፣ ጊዜያችን እንዲባክን አድርገውናል።

ታዲያ እስከመቼ እነዚህ ጠላቶች ይጫወቱብናል። ስለዚህ መጀመሪያ ጠላቶቻችን እነማን እንደሆኑ ለይተን ማወቅ አለብን። ከዛ አንድ በአንድ እያንዳንዱ ላይ ጦርነት እናውጃለን። አንዳንዶቹ ጠላቶቻችንን ፊት ለፊት እንጋፈጣቸዋለን። አንዳንዶቹን ደግሞ ቀስ ብለን እያለሳለስን፤ እያጫወትን እንጥላቸዋለን። ሌሎቹን ጠላቶቻችንን ግን ወዳጃችን እንደርጋቸዋለን።

ሰን ዙ የተሰኘ ደራሲ the art of war በተባለ መጽሐፉ ‹‹ራስህንም ጠላቶችህንም የምታውቃቸው ከሆነ መቶ ጦርነት አያስፈራህም። ራስህን ብቻ የምታውቅ ከሆነ፤ ጠላቶችህን የማታውቸው ከሆነ ግን ብታሸንፋቸው እንኳን ነገ የመሸነፍና የመውደቅ ስጋት አለብህ። ጠላትህንም ራስህንም የማታውቅ ከሆነ ግን ሁልጊዜም በጦርነት በዝረራ ትሸነፋልህ›› ሲል አስፍሯል። ስለዚህ ራሳችንንም ጠላታችንንም የምናውቅበትን መንገድ ማወቅ ይኖርብናል።

ሮበርት ግሪን ዓለም ያጨበጨበለት ድንቅ ደራሲ ነው። ‹‹33 strategies of war›› በሚለው መጽሐፉ አስገራሚ 33 የጦር ሕጎችን አስቀምጧል። ሕጎቹ ጦርና ታንክ፣ መድፍና መትረየስ ታጥቀው ጦር ሜዳ ላይ ለሚደረጉ ጦርነቶች ብቻ አይደለም። በዚህ ዓለም ላይ ከራሳችን ጋር ላለን ግንኙነት፣ ከሰዎች ጋር ላለን ግንኙነት፣ አይምሯችን ውስጥ ለሚደረጉ ማንኛውም ዓይነት ጦርነቶች፣ የሃሳብና የጭንቀት ችግሮች ሁሉ መፍትሄ ናቸው። በጣም የሚያስገርመው የመጀመሪያው ሕጉ ነው። ይህ ሕግ ‹‹wage war on your enemies›› ይላል። ጠላቶችህ ላይ ጦርነት አውጅባቸው እንደ ማለት ነው።

ጠላት ጠላት ነው። አንተን ከመጣልና ወደኋላ ከማስቀረት ውጭ ሌላ ትኩረት የለውም። አንተ ደግሞ ህልም አለህ። ትልቅ ፍላጎት አለህ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ፈጣሪህ ወደዚህ ምድር ያመጣህ ለትልቅ አላማ ነው። አላማህንና ህልምህን ለማሳካት ስትጓዝ ሊያደናቅፍህ ይችላል። እንዴት አድርገህ ነው ታዲያ ይህን ጠላት የምታሸንፈው? እነሆ መልሱ.....

የመጀመሪያው እንዳትለወጥ ያደረገህ፣ አቁሞ ያስቀረህና ትልቁ ጠላትህ ስንፍናህ ነው። ለነገ ብለህ ያሳደርከው፤ ማድረግ እያለብህ ያላደረከው። መሥራት እያለብህ ያልሰራኸው ሥራ በሙሉ ባለህበት ቆመህ እንድትቀር፤ ገቢህ እንዳይነቃነቅ አድርጎሃል። ሰዎች ሁሌም አሸናፊ የሚሆኑት ስንፍናቸውን ታግለው ሲሉ ነው። እንደውም ሰምታችሁ ከሆነ ‹‹ጀግና ማለት ራሱን የሚያሸንፍ ነው፤ ያኔ ማንም አይጥለውም›› ይባላል። እውነት ነው። ትልቁ ጦርነት ያለው ውስጥ ነው። ፈታውራሪውና ትልቁን ውስጣዊውን ጦርነት የሚመራው ደግሞ ስንፍና ነው።

እስኪ እሠራዋለሁ ያልከውን ስፖርት መሥራት ብትጀምር፣ እጀምረዋለሁ ያልከውን ንባብ ወይም አዲስ ኮርስ፣ አዲስ የቋንቋ ልምምድ አልያ በቅርቡ እጀምረዋለሁ ያልከውን አዲስ ቢዝነስ ብትጀምረው፣ ትምህርትህን በደንብ አድርገህ ብታጣና፣ ያሰብከውን፣ ያለምከውንና የቀድከውን በሙሉ ብታደርግ፣ ለራስህ የገባኸውን ቃል ብትጠብቅ ምን ዓይነት ሰው እንደምትሆን አስበው! አንተን ማን ነው የሚያቆምህ? የትኛውንም ህልምህን ታሳካዋለህ።

ይህን ግን እንዳታደርግ ስንፍና እየጎተተህ ነው። ያንተ ሕይወት የሚቀየረው መንግሥት ሲቀየር አይደለም። ሥርዓት ሲለወጥ አይደለም። ሚስትህ፣ ጓደኞችህ፣ ቤተሰቦችህ፣ በዙሪያ ያሉ ሰዎች ሲስተካከል አይደለም ሕይወትህ የሚቀየረው። ሕይወትህ የሚቀየረው ስንፍናህ ከስልጣኑ ሲወርድ ነው። ያንተን ሕይወት የሚያዘው ማነው? አንተ ነህ ወይስ ስንፍናህ ነው? እስኪ ተመልከት አንዳንድ ጊዜ ደክሞሃል። ተኛህ። ኧረ ተኝተህ አርፍድ! ለምን ቲቪ አታይም! አሁን እኮ ደብሮሃል! ፈታ የሚያደርግህ ነገር ያስፈልግሃል .... ወዘተ አድርግ እያለህ የተቆጣጠርህ ስንፍናህ ነው። እናዳትለወጥ ያደረግህ እሱ ነው።

ስንፍናህ ላይ ጦርነት አውጅ። እንዴት አድርጌ? ካልክ መጀመሪያ ምን ያህል ከምትፈልገው ነገር እያስቀረህ እንደሆነ አስብ። ያመጣብህን ጉዳት አስበው። በስንፍናህ ምክንያት ስንት ነገር እንዳመለጠህ አስብ። በነገራችን ላይ ራስህን የምትቀይረው ለራስህ ብቻ ብለህ አይደለም። አንተን የሚፈልጉና አንተን የሚጠብቁ ቤተሰቦች አሉህ። ሀገርህ ትጠብቅሃለች። ታዲያ በስንፍናህ ምክንያት እንዴት ነው ከዚህ ሁሉ ነገር የምትቀረው? ስንፍናህን ካልቀበርከው ሊቀብርህ ነው። እንዴት አድርጌ ላስተካክለው ካልክ....

ሁልጊዜ ምቾት የሚነሳህና የሚጎረብጥህን ነገር ማድረግ ተለማመድ። ምን ማለት ነው ለምሳሌ አንተ ሁልጊዜ በሙቅ ውሃ ይሆናል ገላህን የምትታጠበው። እስኪ ነገ ተነስተህ በቀዝቃዛ ውሃ ታጠብ። የጤና ችግር የማያመጣብህ ከሆነ ነው ታዲያ! ወይ ደግሞ ስፖርት እሰራለሁ ብለህ ብዙ ጊዜ ለራስህ ቃል ገብተህ ሊሆን ችሏል። እስኪ በጠዋት ተነስተህ መሮጥ ጀምር። ወይም ቀለል ያለ የአካል እንቅስቃሴ አድርግ። ማንበብ የማትወድ ከሆነ ራስህን አስጨንቀህ፤ ቁጭ አድርገህ አንድ አምስት ገፅ ለማንበብ ሞክር። ይህንን በየቀኑ ደጋግመው።

ራስህን ማስጨነቅና ከምቾት ማስወጣት ስትጀምር የሆነ ነገር አስበህና አቅደህ የመፈፀም ብቃትህ ይጨምራል። ራስህ ላይ አዛዥ ሁን። ራስህን ምቾት እየነሳህ ብዙ ርቀት ውሰደው። የሆነ ነገር ልታደርግ አስበህ ግን እኮ ደክሞሃል፣ ደብሮሃል፣ ለምን አትተኛም፣ ለምን ቲቪ ከፍተህ አታይም ሲልህ፣ ከምትፈልገው ነገር ሊያስቆምህ አይምሮህ የሆነ ሃሳብ ሲያመጣ እጅ ከፈንጂ ያዘውና እንደዚህ አድርገህማ ሰነፍ አታደርገኝም ብለህ ያሰብከውን ነገር ወደተግባር ግባ። ስንፍና የተባለ ጠላታችንን መዘረር ይቻላል። ነገር ግን ትእግስትና ፅናት ይጠይቃል።

ለምን መሰለህ ዛሬ አሸነፍኩት ብለህ፤ በጣም ቆንጆ የሥራ ቀን አሳልፈህ በማግስቱ አቅሙን አሰባስቦ መጥቶ ሊያሸንፍህ ይችላል። ሰነፍ ሊያደርግህ ይችላል። ስለዚህ ሁልጊዜ ላታሸንፈው ትችላለህ። ራስህን እንዳትጎዳ ለምንድነው ጎበዝ ያልሆንኩት፣ የሰነፍኩት ብለህ አትናደድ። በፅናት ለማሸነፍ መታገል አለብህ እንጂ እጅ መስጠት የለብህም። አንዳንድ ጊዜ ትናንሽ ግጥሚያዎችን ልትሸነፍ ትችላለህ ዋናው ነገር ትልቁን ጦርነት ማሸነፍህ ነው።

መቼም ታውቃላችሁ የዋንጫ ቡድን አንዳንዴ ነጥብ ይጥላል፤ ይሸነፋል፤አቻ ይወጣል። ሁሉንም ጨዋታ በተከታታይ አያሸንፍም። ነገር ግን አብዛኛውን ጨዋታ ስለሚያሸንፍ ዋንጫውን ይበላል። አንዳንድ ጊዜ ልትሸንፍ ትችላለህ። ስህተት ልትሰራ ትችላለህ። ነገ ጠዋት እነሳለሁ ብለህ ተኝተህ ልታረፍድ ትችላለህ። ችግር የለውም! በማግስቱ ግን ራስህን መልሰህ አነቃቅተህ ወደ ሥራ መመለስ አለብህ። ስንፍናህ ላይ ጦርነት አውጅበት!

ሁለተኛው አይምሮህን ተቆጣጥሮ እንዳትለወጥ፣ በሰዎች ለውጥ እንዳትቀና የሚያደርግህ፣ አንተን ባለህበት የሚያስቀርህ ትልቁ ጠላትህ ፍርሃት ነው። ብዙ ዓይነት ፍርሃት አለ። ያመኑትን ለማድረግ የሚፈሩ ሰዎች አሉ። ብዙ ነገር መጀመር ይፈልጋሉ። አዲስ ነገር ውስጥ መግባት፣ አዲስ ቢዝነስ፣ አዲስ ሥራ ግን ቢበላሽብኝስ ሰዎች ምን ይሉኛል ብለው የሚፈሩ በርካታ ሰዎች አሉ። አንዱ አንተ ልትሆን ትችላለህ። ከስንፍና ቀጥሎ የሰው ልጅ ላይ እንደፍርሃት ጢባ ጢቤ የሚጫወት ነገር የለም።

ሰዎች እድሜያቸው ሰባና ሰማንያ ካለፈ በኋላ በሕይወታችሁ መለስ ብላችሁ ሄዳችሁ ማስተካከል የምትፈልጉት ነገር ምንድን ነው? ‹‹በጣም የሚቆጨኝ ድሮ አደርጋለሁ ብዬ ሰዎችን ፈርቼ እንዲህ ቢሆንስ ብዬ ያላደረኳቸው፤ በፍርሃቴ በምክንያት ያጧቸው ነገሮች ተመልሼ ሄጄ ባደርጋቸው›› ይላሉ። አየህ ! አንተ ብቻ አይደለህም። ብዙ ሰዎች ይፈራሉ።

እስረኛው ሁለት ምርጫ ቀረበለት። አንደኛው እዚህ ገመድ ላይ ተንጠልጥለህ ብትሞት ይሻልሃል፤ ሁለተኛው በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ብታልፍ ይሻልሃል። መጀመሪያ የሚንጠለጠልበትን ገመድ አየው። ከዛ ድቅድቅ ጨለማውን በደንብ አየውና ቶሎ ወሰነ። አይ እዚህ ገመድ ላይ አንጠልጥሉኝ አለ። ሰዎች ግን ስቀው ያንን ትንሽ ድቅድቅ ጨለማ ብትጓጓ ኖሮ ነፃ ያወጣህ ነበር፣ ከእስር ይፈታህ ነበር አመለጠህ አንተ ግን ገመዱን መረጥክ አሉት። አንዳንድ ግዜ በሕይወታችን የምንፈራቸው ነገሮች መድረሻቸውን ስለማናውቅ ነው። ቀጥሎ ምን እንደሚፈጠር ስለማናውቅ ነው። ነገር ግን ሕይወታችንን የሚቀይሩ ነገሮች ይኖራሉ።

ከምቾት መውጣት እንፈራለን። ለምን? እንዲህ ብሆንስ፣ ይሄ ነገር ቢገጥመኝስ እንላለን። በጣም የሚገርመውና ሕይወታችንን የሚቀይረው ከፍርሃታችን ጀርባ ያለው ነገር ነው። እሺ! ፍርሃቴን እንዴት ላጥፋው ካላችሁ ፍርሃት የሚጠፋው በዝግጅት ነው፤ በጭፍን ድፍረት አይደለም። የሚዘጋጅ ሰው፣ አቅምን ያፈረጠመ ሰው ማንም ሊዋጋው አይሞክርም። ራስህን ብቁ ስታደርግ፣ ራስህን ስታዘጋጅ በእውቀት፣ በልምድ፣ በገንዘብና በማንኛውም ነገር ራስህን እያዘጋጀህ ስትሄድ ፍርሃት ራሱ ይፈራሃል።

ቀስ እያልክ ነው ፍርሃትን የምታሸንፈው። ራስህ ላይ እየሰራህ፣ በራስ መተማመንህን እየገነባህ ቀስ እያልክ ጭራውን ትይዘዋለህ። ያኔ ራስህን ለመለወጥ ትጀምራለህ። የሚያስፈራህን ነገር ትጋፈጠዋለህ። ነገር ግን በአንድ ጊዜ ከመሬት ተነስተህ ፊት ለፊት ፍርሃትህን መጋጨት የለብህም። ያ ዋጋ ያስከፍልሃል። ስለዚህ ተዘጋጅ። በሕይወትህ ትልቅ ነው ብለህ የምታስበውን ነገር ለማሳካት ምንድን ነው የሚያስፈልግህ፣ ምን ዓይነት ዝግጅት ነው የሚያስፈልግህ፣ ምን ዓይነት የትምህርት ደረጃ፣ እውቀት፣ ልምድ፣ ገንዘብ ነው የሚያስፈልግህ? በትንሹ ብትጀምረውስ? ደረጃ በደረጃ የፈራኸውን ችግር ብትዳፈረውስ ? ሕይወትህ እስከመጨረሻው ይቀየራል።

ሶስተኛው ትልቁ ጠላቶችህ አላማህ እንዳይሳካ መሰናክል የሆኑ ሰዎች ናቸው። ሁሉም ሰው ላንተ መልካም ሊሆን አይችልም። እንኳ አንተ የሃይማኖት መሪዎች ሳይቀር በሰዎች ተገፍተዋል። መልካም ሆነው ሳለ የሰዎች ምላሽ ግን አሉታዊ ይሆናል። ስለዚህ ሁሉም ሰው ይወደኛል ብለህ አታስብ። ሁሉንም ሰው ለማስደሰትም አትሞክር። እንደውም ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ ከአንተ አላማ ጎን የሚሰለፉ። ሌሎቹ ደግሞ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ከአላማህ በተቃራኒ የሚሰለፉ። እነዚህ ሰዎች ሁሌም ባለህበት ቆመህ እንድትቀር፣ እነርሱን እንድትመስል በተለያየ መልኩ ተፅእኖ ሊያሳድሩብህ ይችላሉ።

እነዚህ ሰዎች ፊት ለፊት መጥተው አይጫኑህም። በእጅ አዙር ግን ይቆጣጠሩሃል። ታዲያ መቼ ነው ከእነርሱ እስረኝነት ነፃ የምትወጣው? ጠላት ማለት ጎራ ለይቶ በግላጭ ፊት ለፊት የሚያጠቃ ብቻ አይደለም። አብሮ ሆኖ ስሜትና አይምሮህ ላይ የበላይነት ይዞ የሚነዳህም ጠላት ነው። እነሱ ላይ ነው ጦርነት የምታውጀው። የሆነ ነገር ስታስብ አሉታዊ ነገር የሚነግሩህ ሰዎች አሉ። ህልምህን፣ አላማህን ያሰብከውን ነገር ስትነግራቸው ሁልጊዜ በፍፁም እንደማይሆን፣ አንተ ልታሳካው እንደማትችል የሚነግሩህ ሰዎች አሉ። አትችልም፣ አርፈህ ቁጭ በል፣ የት ልትደርስ ነው፣ በዚሁ መቀጠል አይሻልህም የሚሉ ሰዎች አሉ።

ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር መዋል አቁም። ውሎህን ቀይር። መድሃኒት እሱ ብቻ ነው። የእነርሱን አስተሳሰብና አይምሯውን መቀየር አትችልም። መጀመሪያ ራስህን ነው መቀየር የምትችለው። ስለዚህ ሕይወት ምርጫ ነው። ወይ እነርሱን ትመርጣለህ ወይ ደግሞ አላማህን። ቀጣዩን የሕይወትህን አዲሱን አቅጣጫ ትመርጣለህ። እውነተኛ ለውጥ ስታመጣ የምትርቃቸው ጓደኞችህ ይኖራሉ። የምታስቀይማቸው ቤተሰቦች ይኖራሉ። የጠፋኸው ግን ለመልካም ነው። ራስህን በመልካም ሰዎች በሚለውጡ፣ ከአላማህ ጋር አብረው በሚሄዱ ሰዎች መክበብ አለብህ። ከዛ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለውጡን ታየዋለህ።

አራተኛው የራስህ ጠላት ራስህ ነህ። አንተ ራስህን የወቀስከውንና የጠላኸውን ያህል ማንም አልወቀሰህም። ብዙ ሰዎች ራሳቸውን የሚያጠፉት በውጫዊ ምክንያት አይደለም። ከራሳቸው ገራ የለየለት ግጭት ውስጥ ገብተው ነው። አንተን የሚቀየር ትልቅ ኃይል የተቀመጠው ደግሞ ውስጥህ ነው። ውስጥህ፣ ስሜትህና መንፈስህ ሲጠነክር ምንም ነገር በዚህ ዓለም አያቆምህም። ውስጥህ ሲልፈሰፈስ ግን የሰዎች መጠቀሚያ ትሆናለህ። የሆነ ነገር ሲጠፋ እየደጋገምክ ራስህን የምትወቅሰውና የምትሰድበው ከሆነ በራስ መተማመንህ ይጠፋና ስሜትህና አቅምህ ኩምሽሽ ይላል።

ከዓመታት በፊት ባጠፋኸው አንድ ጥፋት ምክንያት ሺ ጊዜ በየቀኑ ራስህን ትቀጠቅጠዋለህ። ራስህን ትወቅሰዋለህ። እንዲህ ባላደርግ ኖሮ እያልክ ትቆጫለህ። አንድ ጊዜ ራስህን ከወቀስከው አይበቃም? ለዛ ነው የራስህ ጠላት ራስህ ነህ የምንለው። እስካሁን ያወጅከው ጦርነት ነው። አሁን ግን ራስ ላይ የምታወጀው ፍቅር ነው። ያደረካቸውን መልካም ነገሮች አስብ። ፈጣሪህ ፅናቱንና ትእግስቱን ባይሰጥህ ኖሮ የማታልፋቸው ብዙ መሰናክሎች ነበሩ።

ስለዚህ ራስህን ከመውቀስ ይልቅ ፈጣሪህ ያደረገልህን ነገር እያሰብክ ማመስገን በጣም ወሳኝ ነው። ጉልበት ይሰጥሃል። ትላንት ያሳካኸውን ስታስብ ነገ አያስፈራህም። ብዙ ነገር ማሳካት እንደምትችል ልበ ሙሉ ትሆናለህ። ራስህን አበርታው፤ ራስህን አጠንክረው!!

# የገጠሩን ሕዝብ ማዕከል ያደረጉት የፀሐይ ኃይል ማመንጫ መሠረተ ልማት ሥራዎች

በኃይሉ አበራ

ኢትዮጵያ ለኤሌክትሪክ ኃይል ልማት ሊውሉ የሚችሉ በርካታ እምቅ አቅሞች እንዳላት ይታወቃል። የኤሌክትሪክ ኃይል ሊመነጭባቸው የሚችሉ አያሌ ትላልቅ ወንዞች ባለጸጋ ናት፤ በእነዚህ ወንዞች ብዙ ሺ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል እያመረተች ትገኛለች። ከንፋስ ኃይልና ከፀሐይ ኃይል አቅሞቿ ኃይል ማመንጨት ጀምራለች። ከጂኦተርማል፣ ከደረቅ ቆሻሻም እንዲሁ የኤሌክትሪክ ኃይል በስፋት ለማምረት እየተሠራ ነው።

በሀገሪቱ ከተለያዩ ምንጮች ከሚመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል በአብዛኛው ተጠቃሚ እየሆነ ያለው የከተማው ሕዝብ ነው። 80 በመቶ በገጠራማ አካባቢዎች የሚኖረው ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ኃይል እንደማያገኝ መረጃዎች ያመለክታሉ።

መንግሥት የገጠሩን ሕዝብ መቶ በመቶ የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ለማድረግ ሀገራዊ የኤሌክትሪክ ተደራሽነት እቅድ አዘጋጅቶ እየሠራ መሆኑን ይፋ አድርጓል። ይህን ለማሳካት ደግሞ ዋናውን የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ብቻ መጠበቅ እንደማያዋጣ ታምኖበት፣ አነስተኛ ግሪድ የሆኑ የኃይል መሠረተ ልማት ሥራዎች በስፋት እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በዚህ ምክንያት በመንግሥት ከፀሐይ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨቱ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶታል። የኢትዮጵያ መልከዓ ምድር አቀማመጥ በምድር ወገብ አቅራቢያ መገኘቱ፣ ከፀሐይ ኃይል ለሚመነጭ ኢነርጂ ምቹ እንደሚያደርጋት መረጃዎች ያመለክታሉ። በዚህ እምቅ ሀብት ላይ ሰፊ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን መሥራት እና በዘርፉ የተሰማሩ ማህበራትን ማበረታታት ዘርፉን ለማሳደግ የራሱ ጉልህ ሚና እንዳለው ይታመናል።

ኢትዮጵያ ለፀሐይ ኃይል ካላት አቅም እና ለዚህ ዘርፍ ካላት ምቹነት አኳያ ሲታይ ግን በሀገሪቱ በፀሐይ ኃይል መሠረተ ልማት በኩል ብዙም እንዳልተሰራበት ይታወቃል። በቤት ለቤት የኢነርጂ ፍላጎት ጭምር የፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ አቅርቦት ላይ መሥራት ሰፊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ሁሉ፣ አብዛኛውን የገጠር አካባቢ ከፀሐይ ኃይል ከሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል በአማራጭነት ተጠቃሚ ለማድረግ ሰፊ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ያስፈልጋሉ።

በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የኢነርጂ ዘርፍ ዋና አማካሪ አቶ ጎሳዬ መንግሥቴ፣ የፀሐይ ኃይል /solar energy/ ቴክኖሎጂ በሀገሪቱ እንዲስፋፋ እየተደረገ መሆኑን አስታውሰው፣ ቴክኖሎጂው አዋጭ እየሆነ መምጣቱንም ገልጸዋል።

በፀሐይ ኃይል ልማት የተሰማሩ ማህበራት በዘርፉ ለሀገሪቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የኃይል ዘርፉን በተለይ ዋናውን የኃይል ቋት ከማስፋፋት በተጨማሪ ከዋናው የኃይል ቋት ወይም ግሪድ ውጭ የሆነውንና በአሰፋፈሩ የተበታተነውን አብዛኛውን በገጠር የሚኖር ሕዝብ ለመድረስ እየተሠራ ይገኛል። ይህን አማራጭ ኃይል ለመብራት፣ ለሞይባል ቻርጅ አገልግሎትና ለሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶች ለማዋል ጭምር የፀሐይ ኃይል / ሶላር ኢነርጂ/ ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት እንደ ኢሴዳ (Ethiopian Solar Energy Development Association) የመሳሰሉት ማህበራት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑንም አቶ ጎሳዬ ጠቅሰዋል። መሰል ማህበራት እንዲቋቋሙ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እገዛ እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሀገር አቀፉን የኃይል ፕሮግራም ለማሳካት ከሚሰራባቸው መንገዶች አንዱ የግሉ ዘርፍ ማሳተፍ መሆኑን ጠቅሰው፣ የግሉ ዘርፍ ሚና ወሳኝ መሆኑንም አመልክተዋል። ከፋይናንስ አኳያ የዓለም ባንክ፣ የአፍሪካ ልማት ባንክ፣ ጂአይዜድ፣ የአውሮፓ ህብረት እና ሌሎችም የፋይናንስ ምንጮች ለእዚህ አማራጭ የኃይል ልማት ድጋፍ እንደሚያደርጉ አቶ ጎሳዬ ጠቅሰው፣ እነዚህን የፋይናንስ አቅሞች ወስዶ ተግባራዊ ማድረግ ላይ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ወይም አልሚዎች አቅማቸውን ማጎልበት እንደሚኖርባቸው አቶ ጎሳዬ አመላክተዋል። ለዚህም መንግሥት የአቅም ግንባታ ድጋፎችን እና ርዳታ ያደርጋል ብለዋል።

እንደ ሀገር ሲታይ በኢትዮጵያ የሚታየው የፀሐይ ኃይል /energy/ ተጠቃሚነት እዚህ ግባ የማይባል እንዳልሆነ የጠቀሱት አቶ ጎሳዬ፣ ካለው አቅም አኳያ



ከሀብቱ ተጠቃሚ ለመሆን ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ አስታውቀዋል። የፀሐይ ኃይል በትልቅ የኃይል ቋት (solar farm) የሚባለውን ለመሥራት በርካታ አልሚዎች ሊመጡ የሚችሉባቸው ፕሮጀክቶች መኖራቸውንም አስታውቀዋል።

ይህ ከዋናው የኃይል ቋት ጋር ሊገናኝ እንደሚችልም ጠቅሰው፣ ከውሃ እንደሚመነጭ የኤሌክትሪክ ኃይል ሁሉ ከፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ለዋናው ግሪድ የሚሸጥበት ሁኔታ እንዳለም አስታውቀዋል። 100 እና 200 ሜጋ ዋት የሚሆኑትን የግሉ ዘርፍ ሊያለማቸው የሚችሉ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ እነዚህን ያህል አቅሞች በመንግሥት እና በግል አጋርነት ማዕቀፍ እንዲገነቡ እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል።

አቶ ጎሳዬ እንዳብራሩት፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ከፀሐይ ኃይል እንዲመነጭ የሚደረግበት መንገድ ኦፍ ግሪድ ቴክኖሎጂ ይባላል፤ ኦፍ ግሪድ ከዋናው የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ጋር ካልተያያዙ የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ውጭ የኤሌክትሪክ ኃይል በማመንጨት ለተጠቃሚዎች እንዲዳረስ የሚደረግበት መንገድ ወይም ሚኒ ግሪድ ማለት ነው።

በሚኒ ግሪድ ብዙ ጊዜ በአንዳንድ ሀገራት ከ10 ወይም 20 ኪሎ ዋት ጀምሮ እስከ አንድ ሜጋ ዋት፣ በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ እስከ 10 ሜጋ ዋት ድረስ እንዲመነጭ ይደረጋል። ይህም የኤሌክትሪክ ኃይል ዋናውን የማስተላለፊያ ወይም የማከፋፈያ መሥመር ሳይጠቀም ለተጠቃሚ የሚቀርብበት መንገድ ነው። የተመረተው የኤሌክትሪክ ኃይል ከአንድ አካባቢ ፍጆታ አያልፍም። ለአንድ የገጠር ከተማ በዚህ ግሪድ የመብራት አገልግሎት መስጠት ይቻላል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ኃይል የማመንጨትና ማሰራጨቱ ሥራ የራሱ ግሪድ ይኖረዋል። በሀገሪቱ የዚህ ዓይነት ሚኒ ግሪድ በስፋት እንዲለማ እየተደረገ ይገኛል። በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አማካይነትም 11 ሚኒ ግሪዶች በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ ሆነዋል። 25 ሚኒ ግሪዶች በአፍሪካ ልማት ባንክ ድጋፍ በተለያዩ ክልሎች እየተሠሩ ሲሆን፤ 100 ያህል ሚኒ ግሪዶች ደግሞ ሊሠሩ ዝግጅቶች እየተደረጉ ይገኛሉ።

በቀጣይም ከ200 በላይ ሚኒ ግሪዶች ይሠራሉ። ግማሹ በግሉ ዘርፍ፣ የተቀሩት ደግሞ በህብረት ሥራ ማህበራት ባለቤትነት ወጣቶችን በማደራጀትና በመቅጠር የሚሠሩ ይሆናሉ። ሁለት መቶ ሚኒ ግሪዶች ይሠራሉ ሲባልም በየአካባቢዎቹ በሚገኙ ኪስ ከተሞች ወይም አካባቢዎች እና ዋናው ግሪድ የማይደርስባቸውን አካባቢዎች ታሳቢ ተደርጎ ነው። ግሪዶቹ የኤሌክትሪክ ኃይል ከዋናው ግሪድ ለመሳብ አዋጭ በማይሆንባቸው አካባቢዎች የሚገነቡ ይሆናሉ።

የሚኒ ግሪዶች ተፈላጊነትም በዋነኛነት የአካባቢውን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ እንዲለወጥ ማድረግ ነው። ሌላው ትኩረት ተደርጎ የሚሠራበት መስኖ ይሆናል። ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉት የውሃ መሳቢያ ሞተሮች ናፍጣ የሚጠቀሙ ናቸው። የናፍጣው ዋጋ ውድ እየሆነ መጥቷል። ስለዚህ በናፍጣ የሚጠቀሙ የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን ከመጠቀም ይልቅ በፀሐይ ኃይል የሚሠሩትን መጠቀም ይሻላል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በፀሐይ ብርሃን የሚሰሩ ውሃ ፓምፕ አምራቹ ኃይል እንዲያመርት፣ አካባቢውንም ከመበከል ለመታደግ ያስችላል። ወጪውም ከነዳጅ ወጪ በጣም ይቀንሳል። ከተቻለም የፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ ሁልጊዜ የሚገኝ እንደመሆኑ በዓመት ሁለት ሶስት ጊዜ ማምረት ያስችላል። ለመጠጥ ውኃ እና ለኤሌክትሪክ አገልግሎት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

በናፍጣ የሚሠራ የውሃ መሳቢያ ፓምፕ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ አይደለም። ሀገራት የካርቦን ልቀት ለመቀነስ ታዳሽ ኃይል ጥቅም ላይ እንዲውል ያስገነዝባሉ። ከዚህ ሁሉ አኳያ ሲታይ በፀሐይ ኃይል በሚመረት የኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰሩ ፓምፖች ፋይዳ ከፍተኛ ነው። አካባቢን የማይበክል ቴክኖሎጂ መጠቀም በራሱ ከውጭ የተወሰነ የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘትም ያስችላል፤ ሕብረተሰቡም የዚህ ተጠቃሚ መሆን ያስችለዋል ሲሉም አብራርተዋል።

ሚኒ ግሪድ ምርታማነት ማምጣትን እንዲሁም ማህበራዊ ሕይወት መለወጥን ታሳቢ ያደርጋል። ማህበረሰቡ ምርታማ ካልሆነ፣ የሚኒ ግሪድ ታሪፍ ከዋናው ግሪድ ይወደዳል። ለምሳሌም የህብረት ሥራ ማህበራት፣ ቡና አልሚዎች፣ ሌሎች እንደ አቮካዶ ያሉ የገበያ ምርቶችን ወደ ውጭ የሚላኩ አልሚዎችና ላኪዎች ከዋናው ግሪድ አኳያ ሲታይ ታሪፉ የተለየ ቢሆንም፣ ያዋጣቸዋል ሲሉ የኢነርጂ ዘርፍ ዋና አማካሪው አቶ ጎሳዬ መንግሥቴ አስገንዝበዋል።

አቶ ጎሳዬ ወደ ሚኒ ግሪድ ልማቱ የገቡት የሀገር ውስጥ የግል ዘርፍ ማህበራት ውስን መሆናቸውን ጠቅሰው፣ የሚኒ ግሪድ ልማቱ እንዲስፋፋ የግሉ ዘርፍ እና የሀገር ውስጥ ማህበራት በስፋት እንዲገቡ የአቅም ግንባታ ሥራዎች እንደሚሰሩ አስታወቀዋል።

ከዚህ ውጭም የቤት ውስጥ የፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ /ሶላር ሆም ሲስተም / የሚባል እንዳለም አመልክተዋል። በየቤቱ የተለያዩ የፀሐይ ኃይል መሠረተ ልማት ዓይነቶችን በመትከል በክሊኒኮችና በትምህርት ቤቶች ጭምር ደረጃውን የጠበቀ የፀሐይ ኃይል የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት እንዲኖር በማድረግ መብራት እንዲያገኙ ለማድረግ በስፋት እየተሠራ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በተለይ ገጠሩ አካባቢ ላይ ከልማቱ ጋር አብሮ የሚሄድ ወደፊት የሴቶችንም ጫና የሚቀንስ ንፁህ ምድጃ (Cleen cooking) ጭምር ለማሰራጨት የፀሐይ ኃይል / ሶላር ኢነርጂ/ ቴክኖሎጂ ፋይዳንም አስታውቀዋል። ይህ ቴክኖሎጂ ለማብሰያ በሚውልበት ሁኔታም ላይ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማስፋፋት ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ይህም በዝቅተኛ ኑሮ ላይ የሚገኙ ማህበረሰቦችንና በጣም በርቀት ቦታ ያሉ የሚገኙ የገጠር አካባቢዎችን ማዕከል ባደረገ መልኩ በዓለም ባንክ ፕሮግራም በተለየ ፓኬጅ እንደሚሰራም አመልክተዋል።

ቴክኖሎጂ ለሚያበለፅጉ አካላትም የተወሰነ ማበረታቻ በመስጠት ቴክኖሎጂው በርካሽ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል። በዚህም ሕብረተሰቡ እንዲደፋፈር እና እንደ ወፍጮ ቤት፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ በመሳሰሉት ላይ እንዲሠራ እና እንዲለወጥ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

እነዚህን ሚኒ ግሪዶች በስፋት እየያዘ ያለው መንግሥት መሆኑን ጠቅሰው፣ የግሉ ዘርፍ መሥራት ሲፈለግ ሥራ አዋጭ እንዲሆን እና ሕብረተሰቡም ላይ አላስፈላጊ ታሪፍ እንዳይጭኑ ለማድረግ መንግሥት ለግሉ ዘርፍ ድጎማዎችን የሚያደርግበት ሁኔታ እንደሚኖርም ጠቁመዋል። ወደፊት ዋናው ግሪድ በአካባቢዎቹ ሲደርስ የሶላሪ ሚኒ ግሪዱ ወደ ዋናው ግሪድ እንደሚካተትም አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ሶላር ኢነርጂ ልማት ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ተዋበች ወርቁ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ ማህበሩ ንፁህ እና ታዳሽ ኃይል ለማቅረብ ዘላቂ አማራጮችን በማስተዋወቅ እየሠራ ይገኛል። ታዳሽ የኃይል አቅርቦት የሚያቀላጥፉ መሣሪያዎችን ተደራሽ እንዲሆኑም ተጠቃሚዎችንና አከፋፋዮችን በማስተሳሰር እና ከክልል የኢነርጂ ቢሮዎች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን በማድረግ አቅራቢዎች ቴክኖሎጂውን ወደ ገጠሩ አካባቢ እንዲያሰራጩ እየሠራ ነው።

ማህበሩ ከተመሠረተ 10 ዓመታት የሞሉት ሲሆን፣ በእነዚህ ዓመታትም ከመንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ዘርፎች ጋር እየሠራ ነው። በተለይም ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ጋር እንደ ፀሐይ ኃይል ባሉት /ሶላር ኢነርጂ/ ታዳሽ ኃይል ልማቶች ላይ በሚታቀድበት ወቅት ይህንኑ በሚያቀላጥፉ ተግባራት ውስጥ ይሳተፋል። ለወደፊቱ ለሚደረገው የታዳሽ ኃይል ልማት ፈር መያዝም ቁልፍ ድርሻውን እየተወጣ ይገኛል።

ተግባራዊ እንቅስቃሴው ላይም ትልቁ ተግዳሮት የነበረው ቴክኖሎጂው አዲስና በየጊዜው የሚቀያየር በመሆኑ ከታሪፍ አመዳደብ፣ እቃውን ካለማወቅ ጋር የተያያዙ ችግሮች ይገጥሙ ነበር። ቴክኖሎጂውን የመረዳት ችግር አንዱ ዋነኛ ችግር በመሆኑ ከሁለት ዓመት በፊት የሶላር ታሪፍ መመሪያ ( Solar Customs Handbook ) በማዘጋጀት ሥራ ላይ መዋሉን አስታውሰዋል። ይህም ሲዘጋጅ ከፋይናንስ ሚኒስቴር፣ ከውሃና ኢነርጂ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ከንግድ ሚኒስቴር፣ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ እና ኢሴዳ የግሉን ዘርፍ ወክሎ መመሪያው የበለፀገ መሆኑን ተናግረዋል። ይህ መመሪያ ከተዘጋጀ በኋላም እንደማጣቀሻ የሚያገለግል በመሆኑ በተሻለ ችግሮችን መቅረፍ መቻሉን ጠቅሰዋል።

መመሪያው ከሁለት ዓመት በኋላ በቅርቡ መሻሻሉን ጠቅሰው፣ መመሪያው የግል ዘርፉ በሶላር ሚኒ ግርድ የኃይል አቅርቦቱ ላይ ትክክለኛው ታሪፍ ምን እንደሆነ ባለማወቁ የሚፈጠሩትን የመረጃ ክፍተቶች እንደሚፈታ አመላክተዋል።

ከ350 ዋት በታች ያሉ የፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ ቴክኖሎጂዎች በአጠቃላይ እውቅናቸው ሳይረጋገጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ የጥራት ሰርተፊኬት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር እየተሠራ መሆኑንም ዋና ሥራ አስኪያጇ ገልጸዋል። ቀደም ሲል ትልቅ ተግዳሮት የሆነውና ገበያውን በብዛት የያዘው ከደረጃ በታች የሆነ ምርት እንደነበር አስታውሰው፣ ጥራቱን ያልጠበቀ የሶላር ምርት ሀገር ውስጥ እንዳይገባ አስገዳጅ ከሆነ በኋላ ችግሩን መቀነስ መቻሉንና በሂደትም ዜሮ ለማድረግ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የሶላር ቴክኖሎጂዎቹን በአብዛኛው የሚጠቀመው የገጠሩ ሕብረተሰብ ነው ያሉት ወይዘሮ ተዋበች፣ የከተማው ነዋሪ በዚህ ላይ የሚገባውን ያህል እውቀት እንደሌለውም አስታውቀዋል። እርሶ አደሩን በመጠበቅ ቴክኖሎጂውን መጠበቅ እንደሚቻል ተናግረው፣ የገጠሩም ሆነ የከተማው ሕብረተሰብ የፀሐይ ኃይል ኤሌክትሪክ ኃይል ቴክኖሎጂ ላይ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ እንደሚገባ አስታውቀዋል። ቴክኖሎጂውን ለመጠበቅ ተጠቃሚውን ጥራቱን ካልጠበቀ የቴክኖሎጂው ምርት መጠበቅ እንደሚገባ አስገንዝበው፣ የተጠቃሚውን ፍላጎት መጠበቅ ላይ በትኩረት እንደሚሠራ አስገንዝበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓሉን በመረዳዳት እናክብር!

ኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ በርካታ አኩሪ እሴቶች አሏቸው። ከእነዚህ ውስጥ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴቶቻችን በዋነኛነት ተጠቃሾች ናቸው። ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲያጋጥሙ መሰናክሎችን በመረዳዳትና በመደጋገፍ የማለፍ ጥበብን ከማዳበራቸውም በላይ ለተበደሉት መሸሸጊያ፤ ለተሰደዱት መጠለያ ሆነው ዘልቀዋል።

ኢትዮጵያውያን ተፈጥሯዊም ሆነ ሰው ሰራሽ ችግሮች ሲያጋጥማቸው በመረዳዳትና በመደጋገፍ የማለፍ ጥበብን የታለበሱ ሕዝቦች ናቸው። በረሃብም ሆነ በድርቅ፤ በግጭትም ሆነ በጦርነት ወቅት በመረዳዳት አስከፊ ጊዜያቶችን አሳልፈዋል።

ኢትዮጵያውያን የእምነት ልዩነት ሳይበግራቸው ደስታንም ሆነ ኀዘንን በጋራ ያሳልፋሉ።የሀገራቸውንም ዳር ድንበር ይጠብቃሉ፤ ወራሪን በጋራ ድል ይመታሉ፤ በልማት ይሳተፋሉ ፤ሀገራቸውን ጥሪ ስታደርግላቸው ያለምንም ማመንታት ከጎኗ ይቆማሉ። ይህ አንድነታቸውን አብሮነታቸውም ከበበርካታ የዓለም ሕዝብ ዘንድ ትልቅ ክብርና ግርማ ሞገስ አጎናጽፏቸዋል። በአርአያነትም እንዲወሰዱ አድርጓቸዋል።

ኢትዮጵያውያን ዘር ፤ ቀለምና ኃይማኖት ሳይለዩ የተቸገረን መርዳት፤ የተራበን ማብላት፤የተጠማን ማጠጣትና የታረዘን ማልበስ ያውቁበታል። እንኳን ርስ በርሳቸው ይቅርና ባህር አቋርጦ፤ ድንበር ተሻግሮ ለመጣ ስደተኛ ጭምር በራቸውን ክፍት አድርገው ፤ ያላቸውን አካፍለውና ፍቅር ለግሰው ማኖር የሚችሉ ሕዝቦች መሆናቸውን በርካታ የታሪክ መዛግብት የሚያወሱት ሃቅ ነው።

ኢትዮጵያውያን ከመካ የተሰደዱ የነብዩ መሐመድ ተከታዮችንና ቤተሰቦችን ተቀብላ በማስተናገድና በማኖርና የጎላ ታሪክ ያላትና ለእስልምና ኃይማኖትም ባለውለታ ተደርጋ የምትቆጠር ሀገር ከመሆኗም ባሻገር ይህ አኩሪ ታሪክ ሺህ ዘመናትን ተሻግሮ ዛሬም ድረስ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ስደተኞች ተቀብላ በእንክብካቤ የምታስተናግድ ሀገር ነች።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) የረመዳንን ጾም ምክንያት በማድረግ የተለያዩ የኢፍጣር (ጾመኞችን የማብላት) መርሃ ግብሮችን ሲያካሂዱ ቆይተዋል። ሀገራቸውን ጥለው የተሰደዱና ኢትዮጵያን መጠጊያ ያደረጉ የሶማሌ፤ የሶርያ፤ የየመንና የተለያዩ ሀገር ስደተኞችን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቤተመንግሥታቸው ድረስ ጠርተው አስፈጥረዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞችን ቤተመንግሥት ድረስ ጋብዞ ማስፈጠር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ወደ ሥልጣን ከመጡ ጊዜ ጀምሮ የቀጠለ በጎ ተግባር ነው። በዚህ ተግባራቸውም ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የነበራትን እንግዶችን የመቀበል ታሪክ አስቀጥለዋል።

ከ98 በመቶ በላይ አማኝ የሆነው ኢትዮጵያ ሕዝብ ያለውን በማካፈል ያምናል።ሰ ዎች ሲቸገሩ የሚጨክን አንጀት የለውም። ከመሶቡ ቆርሶ፤ ከኪሱ ቀንሶ ያለውን ይሰጣል። የርሱ ቤት ደምቆ የጎረቤቱ እንዲቀዘቅዝ አይፈቅድም። ይህም አኩሪ ባህል ኢትዮጵያውን በችግር እንዳይንበረከኩና ችግርን ድል ነስተው እንዲኖሩ አድርጓቸዋል።

ይህ የመተሳሰብ ፤ የመረዳዳትና የመደጋገፍ እሴት በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጠናክሮ ቀጥሏል። በተለይም አቅመ ደካማ ለሆኑ ዜጎች ማዕድ ማጋራትና የችግረኞች ቤት እድሳት በዚህ ረገድ ተጠቃሾች ናቸው።

በዝቅተኛ ኑሮ ሕይወታቸውን ሲገፉ የቆዩ ነዋሪዎችን ቤት በማደስ ዜጎች በተለይም በኋለኛ ዘመናቸው በተሻለ መጠለያ ውስጥ እንዲኖሩ የሚያደርጉ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ዛሬ የእኛነታችን መገለጫዎች እየሆኑ ነው። በየዓመቱም ክረምት በመጣ ቁጥር የበርካታ አቅመ ደካማ ዜጎች ቤቶች እየታደሱ ዜጎችን ከዝናብና ከብርድ የመታደጉ ተግባር በመንግሥት፤መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና በነዋሪው ተሳትፎ እውን እየሆነ ነው።

በሌላም በኩል በአቅም ማነስ ምክንያት በቀን አንድ ጊዜ እንኳን ራሳቸውን መመገብ የማይችሉ ዜጎችን በጋራ ማዕድ እንዲቆርሱ በማድረግ ረገድ የተጀመሩት በጎ ተግባራት የኢትዮጵያውያንን በጎ እሴቶች ማስቀጠያዎች እየሆኑ ነው። በተለይም በበዓላት ወቅት አቅመ ደካሞች በዓላትን በእኩል ተደስተው እንዲሳልፉ በበጎ ፈቃድ ወጣቶች ጭምር የሚከናወኑ የማዕድ ማጋራት በጎ ሥራዎችን ለተመለከተ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለውን መተሳሰብና መረዳዳት የሚያመላክት ነው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያውያን ከመረዳዳትና ከመደጋገፍ ውጪ መገለጫም የላቸውም። ኢትዮጵያም ቆማ መቀጠል የቻለችው ዜጎቿ በሚከውኗቸው መልካመም ተግባራት ነው።ስለዚህም እነዚህን በጎ እሴቶች በማጠናከር ኢትዮጵያን የማጽናቱ ተግባር በተለይም በዚህ የትንሳዔ በዓል ወቅት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ክብርን ከራስ - ለራስ

መልካምሥራ አፈወርቅ

የሰው ልጆች ክብር በብዙ መንገድ ይገለጻል። ስለራሱ ታላቅ ቦታ የሚሰጥ ትውልድ ደግሞ ሌላውን ለማክበር አይገደውም። ሰዎች በተሻለ ቦታ በተገኙ ቁጥር አእምሯቸው ከመልካም ነገር ላይ ያርፋል። እንዲህ በሆነ ጊዜ ውስጣታቸው በጎውን እየተመኘ አካላቸው ከተሻለው ቦታ ይገኛል።

ሰሞኑን «ጽዱ ጎዳና፣ ኑሮ በጤና» በሚል መርህ ሀገር አቀፍ ንቅናቄ መካሄድ ጀምሯል። የዚህ ንቅናቄ ዋንኛ ዓላማ የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶችን በመገንባት ክብርን ጠብቆ የመጸዳዳት ባህልን ለማዳበር ነው። ይህ ታላቅ ዓላማን ያነገበ እንቅስቃሴ የተለየ ትኩረት ተችሮታልና የብዙሃንን እጀችና ድጋፍ የሚሻ ሆኗል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት አስተባባሪነት የቀረበው ይህ ሀገር አቀፍ ጥሪ መላውን ወገን የሚመለከት በመሆኑ ለሁሉም «ይድረስ፣ ይሰማ» ተብሏል። ሀገራችን በተለይም አዲስ አበባ በአሁኗዊ አቋሟ ከፍተኛ በሚባል የከተማ መልሶ ግንባታ ላይ ትገኛለች። ከዚህ አኳያ ሊጀመር የታሰበው የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶች ግንባታ ፈጣኑን ለውጥ በመደገፍና ሂደቱን በማፋጠን ከፍተኛውን ሚና ይጫወታል።

አዲስ አበባ ከተማችን የአፍሪካ ህብረት መዲና ብትሆንም እዚህ ለመድረሷ በርካታ ችግሮችን እየተሻገረች አልፋለች። የህብረቱ መቀመጫ ኢትዮጵያ ላይ መዝለቁን የማይሹ አንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት ለተቃውሟቸው እንደምክንያት የሚጠቅሱት የከተማዋን ንጹህ ያለመሆን እውነታ ነው።

ከዚሁ የንጽህና ጉድለት ጋር ተያይዞ ሳይነሳ የማያልፈው የመጸዳጃ ቤቶች ችግርና በእኩል የሚስተዋለው በመንገድ ላይ የመጸዳዳት ልማድ ነው። ይህ እጅግ ነውር የሆነ፣ ነገር ግን እንደባህል ተዋርሶን የዘለቀ ድርጊት የሀገራችንን ገጽታ በክፉ የሚያስነሳ ሆኖ ዘመናትን አብሮን ተሻግሯል።

ሁሌም በመንገድ ላይ የመጸዳዳት ጉዳይ ከተነሳ ሀገራችን በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ትሆናለች። ችግሩ አስከፊና ተገቢነት የሌለው መሆኑ ቢታወቅም እስከዛሬ በቀላሉ ለመቅረፍና ከቆሻሻ የጸዳ አካባቢን ለመፍጠር ሳይቻል ቀርቷል።

ዓይንን በሚስቡ የከተማችን ማዕከላዊ ስፍራዎች «በዚህ ቦታ መጸዳዳት በሕግ ያስቀጣል» የሚል ማሳሳቢያ በጉልህ ደምቆ መታየቱ ተለምዷል። በእንዲህ አይነት ቦታዎች ሆኖ መገኘት የግድ ይመስል ማሳሳቢያው በተቃራኒው ተተግብሮ ታያል። ይህን አስነዋሪ ድርጊት ለመከላከልም በሁኔታው ተሳትፈው የሚገኙ ቢኖሩ የተጠቀሰው የገንዘብ ቅጣት እንደሚጠብቃቸውም መጠቀሱ ብርቅ አይደለም።

ከህሊናና ከጥቂት ገንዘብ ቅጣት በላይ የሆነው ድርጊት ግን በሕግ የተፈቀደ ይመስል በየቦታው መስፋፋቱ አዲስ አይደለም። የቆሻሻ ገንዳ ባለበት ፣ የአጥር ከለላ በሚታይበት፣ የውሃ ቱቦና መፋሰሻ በሚገኝበት ስፍራ ሁሉ መጸዳዳት የተለመደ ሆኖ አብሮን ቆይቷል።

በአንድ ስፍራ ተጎራብተው የሚገኙ የቀበሌ ነዋሪዎች አንድ የመጸዳጃ ጉዳጓድን ለበርካታ አባወራዎችና ቤተሰቦቻቸው የማዋሉ እውነታ የተለመደ ነው። በነዚህ ሥፍራዎች ንጽህናው ያልተጠበቀና ቁጥሩ ተደራሽ ያልሆነ አገልግሎትን መጋራት የተለመደ ነው። ይህ እውነት የሕይወትን አስከፊ ገጽታ የሚያሳይና የሰዎችን ክብርና የመኖር መብት በእጅጉ የሚጋፋ አይነተኛ ምሳሌ መሆን ይችላል።

ይህ አይነቱን ችግር መፍትሄ ለመስጠት አንዳንድ የበጎ አድራጎት ተቋማት የተሻለ የመጸዳጃ ቤቶችን በመገንባት ለግልጋሎት ሲያበቁ ይስተዋላል። ችግሩ ከቀድሞው በተሻለ እፎይታ ቢኖረውም በዘላቂነት መፍትሄ ላይ ለመድረስ ግን በቂ የሚባል አይደለም።

በከተማችን በተለያዩ ቦታዎች በነበሩ ጥረቶች ለችግሩ መፍትሄ ለመስጠት ተሞክሯል። ተንቀሳቃሽ መጸዳጃ ሥፍራዎችን በማዘጋጀት፣ በመንገድ ላይ ዘላቂ ማረፊያዎችን በመሥራት እግረኞች በጥቂት የሳንቲም ክፍያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን አስተውለናል። ይህ እንቅስቃሴ በተለይ በከተማዋ መሀልና ዋና ዋና ስፍራዎች ቀላል የማይባል ድርሻን አበርክቷል።

እነዚህ ዘላቂ የመናፈሻ ሥፍራዎች ተጠቃሚዎች ሻይ ቡና ብለው በጥቂት ክፍያ አገልግሎቱን የሚያገኙበት በመሆኑ ለለበርካቶች ታላቅ መፍትሄን ይዞ ዘልቋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአነስተኛና ጥቃቅን የተደራጁ ወገኖች የአካባቢውን ንጽህና እየጠበቁ ተጨማሪ ገቢ እንዲኖራቸው ሚናው ከፍ ያለ ነው።

አንዳንዴ እነዚህ ሥፍራዎች ላይ የውሃ እጥረት ባጋጠመ ጊዜ የንጽህናው ጉዳይ ጎልቶ ሊታይ ይችላል። ይሁን እንጂ እግረኞች እንደዋዛ በየጥጋጥጉ መጸዳዳትን ባህል ያደረጉበትን አጋጣሚ በመሻር በኩል ታሪክን ቀይሯል። ከተወሰነ ጊዜያት ወዲህ ይህ አይነቱ መልካም ልማድ መበራከቱ በርካቶችን ለመጥቀም ምክንያት ሆኗል።

በአንዳንድ የከተማችን ቦታዎች የተለመደውን የመንገድ ላይ መጸዳዳት ለማስቀረት ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል። በተለይ በርካታ የሕዝብ እንቅስቃሴ በሚስተዋልባቸው አካባቢዎች አገልግሎቱን በማስፋት ችግሩን መታደግ ተችሏል። አሁን በሥራ ላይ ባይሆኑም በመገናኛ አካባቢና ዙሪያው ተዘጋጅተው የነበሩ በርከት ያሉ ዘመናዊ መጸዳጃዎች የብዙሃኑን ክፍተት ሲሞሉ መቆየታቸውን ልብ ይሏል።

በቅርቡ ተግባራዊ መሆን የጀመረው የአዲስ አበባ ኮሪደር ልማት ዘመናዊነትን የተላበሰ ከመሆኑ ጋር ሥፍራውን የሚመጥን የመጸዳጃ አገልግሎት ሊኖረው እንደሚገባ ግልፅ ነው። ሃሳቡን ዕውን ለማድረግም ከሁሉም ወገን የተለየ ዝግጁነትና የበዛ ፍላጎት ይጠበቃል።

በርካቶች እንደሚሉት በከተማችን አንዳንድ ሥፍራዎች ለመጸዳጃ ሲባል የተዘጋጁ ቦታዎች ጠቀሜታቸው በእጅጉ የጎላ ነው። በእነዚህ አካባቢዎች አገልግሎትን ሽተው የሚሄዱ ተጠቃሚዎችም ተገቢውን ክፍያ ማከናወናቸው የግድ ይላል። አሁን ላይ ግን በአንዳንድ ሥፍራዎች የተጋነነ ክፍያ መጠየቁ ችግሩ እንዲስፋፋ ምክንያት እየሆነ ይገኛል።

አንዳንድ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት በአንዳንድ የመጸዳጃ አገልግሎቶች ለአንድ ጊዜ ብቻ እስከ አስራአምስት ብር ክፍያ ይጠየቅባቸዋል። ማንም ሊገምተው እንደሚችለው አንድ ሰው ይህን ያህል ክፍያ ከሚጠየቅ ዞር ብሎ የራሱን አማራጭ መውሰድ ፍላጎቱ ይሆናል። እንዲህ አይነት ክፍተቶች በተደጋገሙ ቁጥር ደግሞ ዓላማው በታቃራኒው ተጉዞ ችግሩን እንደሚያሰፋው ግልጽ ነው።

ከተማችን አዲስ አበባ ዘመናዊነትን ለመላበስ ስትዘጋጅ አስቀድማ አብሯት የቆየውን ክፉ ልማድ በማስወገድ ሊሆን ይገባል። ውብና ዓይን የሚስቡ ህንፃዎች፣ ጽዱና ዘመናዊ መንገዶች፣ ማራኪ ዛፎችና መዳረሻዎች ባሉበት በመንገድ ላይ መጸዳዳት ይሉት አስነዋሪ ልማድ ሊቀጥል እንደማይገባ ግልጽ ነው።

ይህ የሀገራችንን መልካም ስም ያቆሸሸ ፣ሁሌም በመረጃና በክፉ ማሳያ የምንጠቀምበት ባህል ከስሩ ተወግዶ ታሪክ ይቀየር ዘንድ የተጀመረው የእንቅስቃሴ ዘመቻ ሂደቱን ሊያፋጥን ርምጃውን ቀጥሏል። ሰዎች ሰው በመሆናቸው ተከብረው ሌሎችንም ያከብሩ ዘንድ መልካም የሚባለውን የመጸዳዳት ባህል ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላል።

አሁን አዲስ አበባ በፈጣን የለውጥ ርምጃ ላይ ትገኛለች። እስከዛሬ በዓለም ላይ የጠለሸውን ገጽታዋን አጽድታ ስሟን ታድስ ትለውጥ ዘንድ የመጸዳጃ ቤቶች ታሪክ ሊቀየር የግድ ይላል። የሰው ልጅ በማንነቱ ክቡር ነው። ሌሎችን አክብሮ ራሱን የሚያከብር ትውልድ በበዛ ቁጥር ማንነት በተሻለ ሥፍራ ጎልቶ ይታያል።

ዛሬ ከትናንቱ ማንነት በተሻለ ተለውጠናል ስንል አፋችንን ሞልተን ለማውራት የሥልጣኔ መገለጫ የሆነው የንጽህና ጉዳይ ከእኛ ጋር ሊሆን ግድ ይላል። አሁን የታሪካችን ጥላሸት፣ የማንነታችን ክፉ ስም በመልካም ሊለወጥ ጊዜው ደርሷል።

የራስን ክብር ይዞ ለሌሎች መልካምነትን የማሳለፍ አንዱ መገለጫ ክብርን ጠብቆ የመጸዳዳት ባህልን ዕውን ማድረግ ነው። የሕዝብ መጸዳጃ ቤቶችን ለመገንባት በሚኖረው ሂደትም የእያንንዱ ዜጋ ዐሻራ የሁሉም ወገን ተሳትፎ ሊተገበር የግድ ይላል። እንዲህ ሲሆን በጽዱ ጎዳና ኑሮና ሕይወትን በጤና ለመምራት ይቻላልና።

ማህበራዊ

# ማህደረ ጤና

## ለሴቶች ጤና የቆመው ‹‹ሔዋን››

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ ጥቂት የማይባሉ ሴቶች በልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ምክንያት ተገቢውን የሕክምና አገልግሎት ሲያገኙ አይታይም። በተለይ በሚገጥማቸው የገንዘብ እጥረት ምክንያት የጤና መታወክ ሲገጥማቸው ለመታከም ይቸገራሉ። በወሊድ ወቅት ደግሞ ተገቢውን የሕክምና ክትትል አግኝተው ለመውለድ ችግር ይገጥማቸዋል። ይህን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት ታዲያ ሴቶች በገንዘብ እጥረት ምክንያት የሕክምና አገልግሎት ሳያገኙ እንዳይቀሩ የሚያስችል ‹‹ሔዋን›› የተሰኘ የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ተመስርቶ ከሰሞኑ ስራውን በይፋ ጀምሯል።

ፕሮፌሰር እድልአየሁ በቀለ ‹‹ሔዋን›› በተሰኘው የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት መስራችና የቦርድ አባል ናቸው። በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ ደግሞ የስነተዋልዶ ጤናና መብት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ብሎም በአዲስ አበባ ከተማ አንጋፋ ከሚባሉ የሕክምና ተቋማት ውስጥ አንዱ ነው። ሆስፒታሉ ከምስረታው ጀምሮ ገቢያቸው አነስተኛ ለሆኑ ዜጎች የሕክምና አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል። የሕክምና አገልግሎቱን እያሰፋ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች የተለያዩ ሕክምና አገልግሎቶችን ከሰባ አምስት ዓመታት በላይ እየሰጠ ይገኛል።

በዚህ የሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ሆስፒታሉ በርከት ያሉ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር ያሉባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎችን እያገዘ ነው። በተለይ ሴቶች ካለባቸው ማኅበራዊ ተፅእኖ አኳያና በሕክምና ሂደት የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ከነዚህ ውስጥም መድሃኒቶችን ለመግዛት መቸገር፣ ተመላልሰው ሕክምና የሚያስፈልጋቸው እናቶች የማደሪያ፣ ትራንስፖርትና ምግብ ወጪ መቸገር፣ የወለዱ እናቶች ጨቅላ ሕፃናቶቻውን የማሞቂያ ክፍል ገብተው ሲታከሙ እነሱ የሚቆዩበት ቦታ ማጣትና መሰል ችግሮች ይጠቀሳሉ።

በነዚህ ችግሮች ምክንያት የሕክምና መቆራረጥና ከሕክምና መቆራረጥ ጋር የተያያዙ የከፉ ጉዳቶች ሲጋጥማቸው ይታያል። ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ ከቅርብ ግዜ ጀምሮ በሆስፒታሉ ኮሌጅ በሚገኘው የማህፀንና ፅንስ ሕክምና ክፍል ባሉ ሃኪሞችና የጤና ባለሞያዎች ከደሞዛቸው ተቆራጭ በማድረግና ጥቂት በጎ አድራጊ ግለሰቦችን በማስተባበር ለሴቶች የተለያዩ የሕክምና አገልግሎት ድጋፍ እያደረጉ ይገኛሉ።

ይሁንና በኢትዮጵያ የሚታየው የኢኮኖሚ ችግር እየሰፋ በመሄዱና የሴቶች ታካሚዎች ቁጥርም ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ በመምጣቱ ብሎም ሴቶች የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት እየገጠሟቸው ያለው የገንዘብ እጥረት ከቀን ወደ ቀን ከፍ እያለ በመምጣቱ በዚህ መልኩ መቀጠሉ አዋጭ ሆኖ አልተገኘም። ከዚህ አንፃር የተጀመረውን መልካም ስራ በስፋትና በዘላቂነት ለማስቀጠል እንደ በጎ አድራጎት ድርጅት መቋቋምና በዚህ መልኩ መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ይህንኑ በመገንዘብ የተለያዩ ሕጋዊ ፍቃድ የማግኘትና የመመዝገብ ስራዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። ለዚህም ስራ ከሆስታሉ የፅንስና ማህፀን ሕክምና ክፍል ኃላፊዎች ጀምሮ መምህራን፣ ሃኪሞች፣ አዋላጅ ነርሶች፣ የኮሌጁ አስተዳደርና ተማሪዎች ትልቅ አስተዋፅኦ አድርገዋል። ሴቶች ወደ ሆስፒታሉ ሲመጡ የሚደርሱባቸውን ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ‹‹ሔዋን›› የተሰኘ የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ተመስርቶ በይፋ ስራውን ጀምሯል፤ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራምም አካሂዷል። አርቲስት የትናየት ታምራትን ደግሞ የድርጅቱ የክብር አምባሳደር አድርጎ ሾሟል።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ የፅንስና ማህፀን ስፔሻሊስትና ሔዋን በተሰኘው የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ ዶክተር ወንድሙ ጉዱ በበኩላቸው እንደሚገልፁት ድርጅቱን ለመመስረት ያስፈለገበት



ፕሮፌሰር ድልአየሁ በቀለ፤



ዶክተር ወንድሙ ጉዱ፤



ወይዘሮ ዘምዘም መሃመድ፤

ዋነኛ ምክንያት በእለት ተእለት ስራዎች የሕክምና ወጪያቸውን መሸፈን የማይችሉ ሴቶች በብዛት መታየታቸው ነው። ከዚህ በመነሳት ሴቶቹ ችግሩን ይዘው ሲመጡ መከላከልና መፍታት የሚቻል በመሆኑ የሕክምና ወጪያቸውን መሸፈን የማይችሉት እዛው በተወሰነ መልኩ በበጎ ፍቃደኝነት የመርዳትና ወደ ማኅረሰቡ በመውረድ ችግሮቹን የማቃለል ስራ ተሰርቷል። በዚህም መልኩ ነው ስራው የተጀመረው።

ወደ ማኅበረሰቡ ተወርዶ የሚሰራው ስራ ሴቶችን በትምህርትና በኢኮኖሚ የማብቃት፣ የጤና መረጃዎችን መስጠት፣ ቅድመ ካንሰር ልየታ ምርመራዎችን ማድረግ፣ የሴቶች ጤና ላይ የፖሊሲ ማእቀፍን እንዲጎለብት ማገዝና ጥናትና ምርምር ላይ በመመርኮዝ የሴቶችን ጤና ማበልፀግን ያካትታል። ስለዚህ ስራው ሲጀመር የሕክምና ወጪ የሚያንሳቸውን ሴቶች መርዳት ቢሆንም አሁን ላይ ስራው አድጎ የሴቶችን ጤና ወደ ማበልፀግ ስራ አድጓል። ስለዚህ አሁን ላይ በዋናነት የሚሰራው ስራ የሴቶችን ጤና ማበልፀግ ነው።

ለሴቶቹ እርዳታ እየተደረገ ያለው በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የማህፀንና ፅንስ ሕክምና ክፍል ነው። የእርዳታ ስራው ከተጀመረ ሁለት ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን በነዚህ ሁለት ዓመታት ግዜ ውስጥ በሕክምና ክፍሉ ሀኪሞች፣ መመህራን፣ ተማሪዎችና ሌሎች በጎ ፍቃደኛ ግለሰቦች አማካኝነት 80 የሚደርሱ እናቶች ድጋፍ አግኝተዋል። እስከ 150 ሺ የሚጠጋ ገንዘብም ለነዚህ እናቶች ሕክምና ወጪ ሆኗል።

ዋና ስራ አስኪያጁ እንደሚያስረዱት ሆስፒታሉ የሚፈልገውን የሕክምና አገልግሎት ሰጥቶ ጨርሻለሁ ማለት ይችላል። ነገር ግን በእለት ተዕለት የሚታየው የሴቶች የሕክምና ወጪ ችግር ይህን በጎ እርዳታ ለማከናወን አስገድዷል። በሴቶች በኩል የሚታየው የሕክምና ወጪ የመሸፈን ችግር ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ መጥቷል። ይህም ችግር በተለያዩ ምክንያቶች የመጣ ነው። አንደኛው ምክንያት የሴቶች የኢኮኖሚ እቅም ማነስ ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የኢኮኖሚ ሁኔታው ቢሻሻል በዛው መጠን የሕክምና ወጪ በከፍተኛ ደረጃ መጨመር ነው። ዛሬ ላይ የላብራቶሪ፣ አልትራሳውንድ፣ የሲቲ ስካንና ኤም አር አይ፣ ለየት ያሉ የደም ምርመራዎች ወጪዎች ከፍ ብለዋል።

በተመሳሳይ የመድሃኒት ዋጋም የዛኑ ያህል እየጨመረ መምጣት በተለይ ደግሞ ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑ የመድሃኒት አይነቶች ከታካሚዎች የመግዛት አቅም በላይ መሆን ለችግሩ መስፋት አይነተኛ ሚና ተጫውተዋል። በጥናት በተደገፈ መረጃ መሰረት ደግሞ ለታካሚዎች ከሚታዘዙ አራት አምስት መድሃኒቶች ውስጥ አራቱ ከታካሚው የመግዛት አቅም በላይ መሆንም የሴት ታካሚዎችን ችግር አባብሶታል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሴቶች ሁለንተናዊ ጤና ሲባል በርካታ ነገሮችን ያካትታል። ሴቶች ገና በታዳጊነት የእድሜ ክልል ውስጥ በትምህርት ቤት እያሉ ግልፅ የሆነ የፆታ ልዩነት ይታያል። ትንሽ ከፍ ሲል ደግሞ ያለ እድሜ ጋብቻ ችግሮች ይታያሉ። ይህም በራሱ በሴቶች የሚያደርሰው የራሱ የሆነ ጫና አለው። በኢትዮጵያ በአብዛኛው የቤተሰብ ገቢ አመንጪ

‹‹ሴቶች ልጆች ትምህርት ቤት እንዲቆዩ የትምህርት ሚኒስቴር ድርሻ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች ድርሻ ነው፡፡ ሴቶች በትምህርት ቤት በቆዩ ቁጥር ደግሞ በአካልም፤ በአእምሮም እየበቁ ይሄዳሉ። ውሳኔ ሰጪም ይሆናሉ፡፡ ለዚህ ታዲያ ሴቶችን ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም ትምህርት ቤት ላይ እንዲቆዩ መሰራት አለበት፡፡››

ወንዶች እንደመሆናቸው ሴቶች የኢኮኖሚ ጥገኛ ስለሚሆኑ ይህም በሴቶች ላይ የሚያደርሰው የሥነ ልቦናና ማኅበራዊ ተፅእኖ ይኖረዋል።

እነዚህና መሰል ነገሮች በሴቶች ላይ የጤና ጫና ይፈጥራሉ። ዋነኛ መነሻውም ይኸው ነው። ከዚህ አለፍ ሲል ደግሞ ሴት በመሆናቸው ምክንያት ከወንድ የተለዩ የሕክምና ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። የማኅፀን በር ጫፍና የጡት ካንሰር ለሴቶች የተለዩ በሽታዎች ናቸው። ስለዚህ ማኅበረሰቡ ጋር ያለው ችግር፣ ሴቶች በተፈጥሮ ያላቸው ስነ ሕይወታዊ አፈጣጠርና የሴቶችን ጤና ከማበልፀግ አንፃር ፖሊሲውን ላይ በደምብ አለመሰራቱ የሴቶች ጤና ላይ ሁለንተናዊ ጫና ይፈጥራል። ይህ ደግሞ የብዙ ነገሮች ውጤት ነው።

በጤና ሚኒስቴር የእናቶች ጤና ቡድን መሪ ወይዘሮ ዘምዘም መሃመድ እንደሚናገሩት እናቶች በተለያዩ የኢኮኖሚ ችግሮች ምክንያት የሚገጥማቸውን የሕክምናና አገልግሎት መጓደል ለመቅረፍ በርካታ ስራዎች መሰራት አለባቸው። በተለይ ደግሞ አሁን ከሚታየው ድህነት አኳያ ሁሉንም ነገር በመንግስት ብቻ መሸፈን ስለሚያዳግት አቅም መፍጠርና ሴቶችን ማገዝ ያስፈልጋል።

ወደ 48 ነጥብ 9 የሚጠጉና በገጠር የሚኖሩ ሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች ለሕክምና አገልግሎት ተደራሽ ባለመሆናቸው እንደዚህ አይነቱ የበጎ አድራጎት ድርጅት መቋቋም ወሳኝ ነው። ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎት በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚገኙ ሴቶች ተደራሽ መደረግ አለበት። ከሁሉ በፊት ግን ሴቶችን በሁለንተናዊ መልኩ ማብቃት ያስፈልጋል። ልክ እንደ ጳውሎስ ሆስፒታል ሁሉ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንዲህ አይነቱን ግንዛቤ መፍጠር ከተቻለ ወደጤና ተቋማት የሚመጡ ሴቶች እና ሕፃናት በገንዘብ እጥረት ምክንያት ሕይወታቸው እንዳይጠፋ መታደግ ይቻላል።

ሔዋን የሴቶች ጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅትም በዚህ ስራው ብቻ ይገደባል ተብሎ አይታሰብም። ሌሎች የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎችም ተመሳሳይ ስራዎችን ያከናውናሉ ተብሎ ይጠበቃል። በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለ ሰው በሕይወቱ ሊኖረው የሚገባው ትልቁ ሃብቱ ጤናው እስከሆነና ሁሉንም ሴክተር አስከሚነካ ድረስ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ዘርፈ ብዙ ምላሽ ይፈልጋል።

ሴቶች ልጆች ትምህርት ቤት እንዲቆዩ የትምህርት ሚኒስቴር ድርሻ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ሴክተር መስሪያ ቤቶች ድርሻ ነው። ሴቶች በትምህርት ቤት በቆዩ ቁጥር ደግሞ በአካልም፤ በአእምሮም እየበቁ ይሄዳሉ። ውሳኔ ሰጪም ይሆናሉ። ለዚህ ታዲያ ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም ትምህርት ቤት ላይ እንዲቆዩ መሰራት አለበት። ምክንያቱም ሴቶች ለተለያዩ በሽታዎች ሲጋለጡ ወንዶች ሴቶችን መደገፍ ስላለባቸው ነው።

ከዚህ አንፃር ሔዋን ወደ ጳውሎስ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎችም የጤና ጠቋማት ለሚሄዱ ሴቶች እንደማስተማሪያ ሆኖ ያገለግላል። በተመሳሳይ የጤና ባለሞያዎችም አክብሮት፣ ሩህሩህነትና ታጋሽነት የተሟላበት አገልግሎት እንዲሰጡ መሰራት አለበት። ስለዚህ በቀጣይ ለሔዋን የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# ጓደኝነትን በሥራ አጋርነት ያደረጁ ብርቱ እጆች

ፍሬሕይወት አወቀ

አስር የሚደርሱ ድርጅቶችን በስሩ ይዟል። በሪልስቴት፣ በኮንስትራክሽን፣ በሪልስቴት ማርኬቲንግ፣ በሪል ስቴት ሕግ የማማከር አገልግሎት እና ንብረት አስተዳደር፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ ከ20 በላይ የሪል ስቴት ቴክኖሎጂ መተግበርያዎች፣ በትሬዲንግ እንዲሁም እንደ ሀገር ብዙም ትኩረት ባልተሰጠው ቤቶችን ከቴክኖሎጂ ጋር የማስተሳሰርና ስማርት የማድረግ ላይ ትኩረት አድርጎ ይሠራል። አፍታ ሜይራ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማህበር።

የድርጅቱ መስራቾች ጓደኛሞቹ ኢንጂነር ፍሬው ታምሬና አሚር አብዱልዎሃብ ይባላሉ። ጓደኝነትን ከሙያ አጋርነት አጣምረው በተለይም በሪልስቴትና ሪል ስቴት ነክ በሆኑ ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩና የሕግ፣ የማማከር አገልግሎት ጭምር የሚሰጡ የሥራ ባልደረቦች ናቸው። በተለይም ለትውልድ የሚተላለፍ ሕጋዊ ድርጅት እና ሀብት መገንባት ላይ ትኩረት አድርገው ይሠራሉ፤ እነዚህ ‹‹ከአንድ ብርቱ ሁለት መድኃኒቱ›› ያሉት ብርቱ ጓደኛሞች አዲስ የሆነውን ‹‹ፊውቸሪስቲክ ኦርጋኒክ ግሪን›› /FUTURISTIC ORGANIC GREEN (FOG)/ የተባለውን ፕሮጀክት በኢትዮጵያ መጀመራቸው ልዩ ያደርጋቸዋል።

ኢሉባቦር/ኢሉ አባ ቦራ/ መቱ አንበጣ በምትባል የገጠር መንደር ተወልዶ ያደገው ፍሬው የትምህርት ጊዜውን በጅማና በሆሳዕና አሳልፏል። የመጀመሪያ ዲግሪውን በሲቪል ኢንጂነሪንግ ሁለተኛ ዲግሪውን አርበን ፕላኒንግና ዴቨሎፕመንት ተከታትሏል። ፍሬው ሥራ ከጀመረበት የወጣትነት ጊዜው ጀምሮ የኮንስትራክሽን ግንባታ ፈቃድ በማውጣት የግንባታ ሥራውን ተቀላቅሎ ዛሬም ድረስ በኮንስትራክሽን ዘርፍ ውስጥ ይገኛል። ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከላይ ታች ሲል የቆየው ፍሬው፤ አዲስ አበባ ውስጥ ያለው ሰፊ የኮንስትራክሽን ሥራ በመዲናዋ አስቀርቶታል።

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የጋራ መኖሪያ ቤቶች እስከ ግል ድርጅቶች የግንባታ ፕሮጀክቶች ድረስ ሙያውን፣ ዕውቀቱንና ልምዱን ተጠቅሞ የሠራው ፍሬው፤ በዘርፍ ከተቆጣጣሪ መሃንዲስነት እስከ ኃላፊነት እንዲሁም በትላልቅ ሪልስቴቶች የሽያጭ ባለሙያም ሆኖ ሰርቷል። ይህም የሪልስቴት ዘርፉን በሚገባ እንዲያውቀውና እንዲረዳው አግዞታል። ከዚህም በላይ በዘርፉ የሚስተዋሉ በርካታ ክፍተቶችን የመረዳት ምቹ ሁኔታን ፈጥሮለታል።

በሪልስቴት ዘርፍ በቆየባቸው ዓመታት በርካታ ክፍተቶችን መታዘብ እንደቻለ የገለጸው ፍሬው፤ ዘርፉ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ገንዘብ ያለው ሰው ያለ ዕውቀት በዘፈቀደ ሲመራው የነበረና ብዙዎች ሲያለቅሱበት የቆየ ስለመሆኑ ተናግሯል። ፍሬው እና ባልደረቦቹም ክፍተቱን በማስተዋል ለዓመታት በነፃ የማማከር አገልግሎት ሰርተዋል፣ ይህንንም ችግር በልኩ መረዳት በመቻላቸው ዘርፉን በዕውቀት፣ በሕግና በሥርዓት መምራት እንደሚገባ በማመን ፍሬው የሽያጭ ባለሙያ ሆኖ ከሚያውቀው ጓደኛው አሚር ጋር በመሆን አፍታ ሜይራ ግሩፕን መሠረቱ።

አሚር አብዱልዎሃብ ሀረር ሂርና ነው ተወልዶ ያደገው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ሂርና የተከታተለ ሲሆን፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን አዲስ አበባ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ተከታትሏል። የመጀመሪያ ዲግሪውንም ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ በማርኬቲንግ አግኝቷል። ከትምህርት በኋላ የሥራ ዓለምን ሲቀላቀል ትንሽ በሚባል ሥራ ጀምሮ አሁን የሪልስቴት ግንባታ ሥራ ላይ ደርሷል።

የታሸገ ውሃ ከፋብሪካዎች ተረክቦ በተለያዩ አካባቢዎች የማከፋፈል ሥራ ሲሰራ ነበረው አሚር፤ ከውሃ ሽያጭ በተጨማሪም የተለያዩ የሳሙና ምርቶችን ከፋብሪካ ተረክቦ ለክልል ከተሞች በማከፋፈል ሠርቷል። ከዚህ ከፍ ሲልም የኮስሞቲክስ ዕቃዎችን በማከፋፈል ታዋቂ እንደነበር አጫውቶናል። ቢዝነሱን ለማሳደግ በነበረው ተነሳሽነትም አሚር የኤክስፖርት ሥራን ተቀላቅሎ ከቡና ውጭ ያሉ የግብርና ምርቶችን



አሚር አብዱልዎሃብ



ፍሬው ታምሬ

ማለትም ጫት፣ ሰሊጥ እና ማርን ጨምሮ ጥራጥሬና የቅባት እህሎችን ወደ ውጭ በመላክ በኤክስፖርት ዘርፍ ላይ ሰርቷል።

በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በየግላቸው ሲውተረተሩ የነበሩት ጓደኛሞቹ ፍሬውና አሚር፤ በሪልስቴት ማርኬቲንግ በጋራ የመሥራት አጋጣሚንም አግኝተዋል። አጋጣሚውም ጓደኝነታቸውን ይበልጥ አጠናክረላቸው። የራሳቸውን ሥራ በጋራ ለመሥራት ወስነው ወደ ተግባር መግባታቸውም ለዚሁ ነው።

ጓደኛሞቹ በአሁኑ ወቅት በጋራ ከሰሩት የሪልስቴት ሽያጭ ባለሙያነት በተጨማሪ በየግላቸው በትምህርትና በሥራ ልምድ ያካበቱትን ዕውቀት እንዲሁም ተሞክሮ በመደመር አፍታ ሜይራ ግሩፕን በማቋቋም የሪልስቴት ኢንቨስትመንት ሥራ ውስጥ ገብተዋል።

‹‹የምንገነባው ለሀገር ከቤት ባሻገር ነው›› የሚሉት ጓደኛሞቹ፤ FUTURISTIC ORGANIC GREEN (FOG) ዘላቂ ተፈጥሯዊ አረንጓዴ ቤቶችን መገንባት በሚል ጽንሰ-ሃሳብ ላይ ትኩረት አድርገው መሥራቱን ተያይዘውታል፤ ጽንሰ-ሃሳቡም Eco-Friendly ወይም ተስማሚ ግንባታን የሚያመለክት ነው። ዘላቂ የሆኑ ቁሳቁስን፣ ኃይል ቆጣቢ የግንባታ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ የተፈጥሮ ውህደት፤ አረንጓዴ ቦታዎች፣ መናፈሻዎች፣ ቋሚ የአትክልት ሥፍራዎችን ማልማት፣ ስማርት ቴክኖሎጂዎች፤ የቤት አውቶሜሽን፣ የኢነርጂ አስተዳደር እና የአይኦቲ ውህደትን መከተል፣ ደህንነትን ማዕከል ያደረገ ንድፍ፤ ክፍት አቀማመጦች፣ የተፈጥሮ ብርሃን፣ የአካል ብቃት መገልገያዎችን ማካተት የሚሉት በጽንሰ ሃሳቡ የተካተቱ ናቸው። የማህበረሰብ ቦታዎችን በሚመለከት የከተማ እርሻን ጨምሮ የጋራ የመዝናኛ ሥፍራዎችና የውጭ ዝግጅቶችን ያካትታል።

ጓደኛሞቹ፤ ከሪልስቴት ኢንቨስትመንት በተጨማሪም አስር የሚደርሱ የተለያዩ ለትውልድ የሚተላለፉ ድርጅቶችን መስርተው ጤናማና ዘላቂነት ያለው ትልቅ ራዕይ ሰንቀው እየሠሩ ናቸው።

በሪልስቴት ዘርፍ ሲሰሩ ያስተዋሏቸው በርካታ ክፍተቶች እንዳሉም ይጠቁማሉ። ያም ሆኖ በዘርፉ ሰፊ ፍላጎት በመኖሩ የሪልስቴት ኢንቨስትመንቱ ከነክፍተቶቹ ተጉዞ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሷል ሲሉም ይገልጻሉ። እነሱ እንዳሉት፤ በትንሹ ለመጥቀስ እንደ ሀገር ራሱን የቻለ የሪልስቴት ሕግ አለመኖሩ አንዱና ዋናው ችግር ነው።

ይሁንና ድርጅቱ ወደ ዘርፉ ሲገባ እነዚህንና መሰል ችግሮችን በሚገባ አጥንቶና በተግባር ፈትሾ በመሆኑ በዘርፉ የራሱን ድርሻ ለመወጣት አቅዶ ይሠራል። በተለይም ለአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ ልምምዶችን፣ ዘላቂ ተስማሚ የኪነ-ሕንፃ ባህሪያትን እና የተዋሃደ የተፈጥሮ እና የከተማ ኑሮን ያጣመረ የግንባታ ቴክኖሎጂ ላይ ትኩረት አድርጓል።

የሪልስቴት ኢንቨስትመንት ትላልቅ ስህተቶች ሲፈጸምበት የኖረ ዘርፍ ነው ብለው የሚያምኑት ጓደኛሞቹ፤ ጥፋቶችን ለማረም የተዘጋጁና በተለይም ዘርፉ በዕውቀትና በጥናት መመራት እንዳለበት አስገንዝበዋል። በሪልስቴት ኢንቨስትመንት እንዲሳተፉ ያስገደዳቸው በዘርፉ ያካበቱት ዕውቀትና ያሳለፉት ዕውነት እንደሆነ አመላክተው፣ በሪልስቴት ኢንቨስትመንት ሲሰማሩ ገና ከመነሻው ጀምሮ በጥናት መመስረታቸውን ይገልጻሉ። ልማታቸው የተሻለ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ያማከለ እንደሆነም አጫውተውናል።

አብዛኛውን የማህበረሰብ ክፍል ያማከለ ሲባል የሚገነቧቸው ቤቶች በካሬ አነስተኛ ሆነው ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ማለት ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያታቸው በከተማው ውስጥ ያለው የመኖሪያ ቤት ፍላጎትና ያለው አቅርቦት ተመጣጣኝ ባለመሆኑ ነው። ተመጣጣኝ ዋጋ ሲባል ድርጅቱ የሚገነባቸው ቤቶች ዋጋ አዲስ አበባ ውስጥ ካሉት ከየትኛውም ሪልስቴቶች ዋጋ ተመጣጣኝ እንደሆነና በካሬ ሜትር ከ32 እስከ 75 ሺ ብር መሆኑን ጓደኛሞቹ ይጠቁማሉ። ያም ሆኖ ሽያጩ ያዋጣል ሲሉ ይገልጻሉ። ምክንያቱም አፍታ ሜይራ ግሩፕ ዓላማ አድርጎ የሚሰራው መጠነኛ በሆነ ትርፍ አብዛኛውን ማህበረሰብ መድረስ መሆኑን አስታውቀዋል።

በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችንም እንዲሁ መቅረፍና ለደንበኞች ጥራት ያላቸውን ቤቶች በወቅቱ በማድረስ ተቀባይነትንና ታማኝነትን በማትረፍ የድርሻቸውን መወጣት ሌላው የልማታቸው ማዕከል ነው። ለዚህም አስፈላጊውን ጥናትና ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ እንደቻሉ የሚጠቅሱት ጓደኛሞቹ፤ በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግና በሌሎች ዘርፎችም ለመሰማራት ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት ትኩረት አድርገው እየሠሩ ያሉት በሪልስቴት ኢንቨስትመንት እና ተያያዥ ዘርፎች ሲሆን፤ በአፍታ ሜይራ ግሩፕ ስር የሚገኙ በሽያጭ ላይ ያሉ ስድስት ፕሮጀክቶች በሥራ ላይ ይገኛሉ።

በአንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ 15 የሚደርሱ የሪልስቴት ግንባታ ፕሮጀክቶችን አዲስ አበባ ውስጥ መጀመር እንደቻሉ የገለጹት ጓደኛሞቹ፤ በቀጣይም እነዚህን 15 ፕሮጀክቶች ወደ ግንባታ ለማስገባት አቅደው እየሠሩ ነው።

የሪልስቴት ኢንቨስትመንቶች አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ብቻ ታጭቀው መቅረት የለባቸውም የሚል እምነትም አላቸው። ወደ ክልል ከተሞች ወጣ በማለት የሪልስተቴት ኢንቨስትመንቱን ለማስፋት እየሠሩ እንደሆነ ተናግረዋል። በጅማ፣ ቢሾፍቱ እና ሆሳዕና ከተሞች የሪልስቴት ግንባታ ለማካሄድ ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል። ከዚህ በተጨማሪም መቀሌ ላይ በጥናት ደረጃ ያሉ ፕሮጀክቶች ስለመኖራቸው ያነሱት ጓደኛሞቹ፤ ሀገር አደገች፤ ከተማ ተገነባ የሚባለው ተቀራራቢ የሆነ ዕድገትና ስልጣኔ ያላቸውን ከተሞችን ማስፋፋት ሲቻል ነው ይላሉ።

ጥራትና ዘመናዊ ዲዛይን ያላቸው ቤቶች በክልል ከተሞች መቅረብ እንዳለባቸው በማመን በክልል ከተሞች ላይ ትኩረት አድርገው እንደሚሰሩ አስረድተዋል። አዲስ አበባ ላይ በተለይም ምሳሌ መሆን የሚችሉ የሪልስቴት ግንባታዎችን ለመሥራት እንጥራለን የሚሉት ጓደኛሞቹ፤ እንዲህ ዓይነት ፕሮጀክቶችን ውጤታማ ለማድረግ ሁለት ነገሮች ማለትም አቅምና ፕሮጀክት ማኔጅመንት ሲስተም ወሳኝ እንደሆኑ ያስገነዝባሉ።

አቅም ሲባል የተለያዩና አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶች ናቸው። ለአብነትም ፕሮጀክቶችን አብዝቶ መያዝ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ባለው አቅም ልክ ሊሰራ የሚችል ሥራ ለመሥራት መወሰን የግድ ነው። ፕሮጀክቶችን ለሕንፃ ተቋራጮች በመስጠት እንዲሰሩ ማድረግ እንደሚቻልና እዚህ ላይ ደግሞ ቁጥጥርና ክትትል ዋናው ጉዳይ ነው። ለዚህም አፍታ ሜይራ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ሲስተም በተባለ ቴክኖሎጂ ቁጥጥርና ክትትል ያደርጋል።

ቴክኖሎጂው በእያንዳንዱ የሥራ ቀን ምን ያህል ግብዓትና ሠራተኛ እንዳለና በግብዓቱና በሠራተኛው ልክ ሥራው መሠራትና አለመሠራቱን መቆጣጠር የሚያስችል ሲሆን፤ ሥራው ሳይሰራ ቢቀርም እንዲሁ በምን ምክንያት ሳይሠራ እንደቀረ በቀላሉ መቆጣጠርና መለየት የሚያስችል ነው ይላሉ። ይህም የተሻለ ውጤት ለማምጣት ወሳኝ በመሆኑ እየሠሩበት እንደሆነ ነው ያስረዱት።

በቴክኖሎጂው ፕሮጀክቱን ከመቆጣጠር ባለፈ ቤት የገዛ እያንዳንዱ ደንበኛ የፕሮጀክቱን የየዕለት ተግባርና አጠቃላይ ሂደቱን መከታተል የሚችልበትን ሥርዓትም ተዘርግቷል። ማንኛውም ቤት ገዢ የትም ሀገር ሆኖ በእጅ ስልኩ ፕሮጀክቱን መከታተል የሚችልበት ዕድል አለው። ግልጽነት የአፍታ ሜይራ ግሩፕ አንዱና ዋናው ዓላማ ሲሆን፤ ይህም ለድርጅቱም ሆነ ለደንበኛው ጉልህ አበርክቶ ያደርጋል።

ጓደኛሞቹ ወደ ግንባታ ከመግባታቸው አስቀድሞ የነበሩበት የሪልስቴት ሽያጭ ሥራ እንዳለ ሆኖ ነፃ የሕግ የማማከር አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበር በማስታወስ፤ ሰዎች በተለይም የሪልስቴት ሕግና አሠራር እንዲሁም የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግን አውቀው የግንባታ ሕጉንም ጭምር ተገንዝበው እንዲሸጡና እንዲገዙ የማማከር ሥራ ሲሰሩ ቆይተዋል። አሁንም እየሠሩበት ይገኛሉ። ይህም በርካታ ደንበኞችን ማፍራት እንዲችሉ ያገዛቸው በመሆኑ የሪልስቴት ኢንቨስትመንቱን በቀላሉ መቀላቀል ችለዋል።

የቤት አቅርቦት ላይ ገና ብዙ ሥራ ይጠይቃል የሚሉት ጓደኛሞቹ፣ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ የክልል ከተሞች ለአብነትም ቢሾፍቱና ዱከም ቪላ ቤቶችን እየገነቡ እንደሆነ ተናግረዋል።

አፓርትመንትም ሆነ ቪላ ቤቶችን ለመገንባት መሬት የሚያገኙበት አማራጮች በዋናነት ሶስት ናቸው። አንደኛው መሬት ገዝተው የሚገነቡበት አሠራር ሲሆን፣ ሁለተኛው የአብሮ ማልማት አማራጭ ነው። ይህም ማለት የመሬት ባለይዞታ የሆነ አንድ ሰው መሬት ኖሮት ነገር ግን የመገንባት አቅም ከሌለው፣ እነሱ አቅማቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ያላቸውን ሀብት በሙሉ ተጠቅመው ቦታው ላይ በመገንባት እንደየቦታው ሁኔታ ስሌት ተሰልቶ ለባለይዞታው የድርሻውን በመስጠት ቀሪውን ለራሳቸው በማድረግ በሽያጭ ያስተላልፋሉ። ሶስተኛው በቅርቡ የተጀመረው በመንግሥትና በግል አጋርነት/ PPP/ የሚገነባ ሲሆን፤ ለጊዜው መሬት በግል በመግዛትና በአብሮ ማልማት አማራጮች እየሠሩ ይገኛሉ።

አዲስ አበባ ላይ ብቻ 15 የሪልስቴት ፕሮጀክቶች ያሉት አፍታ ሜይራ ግሩፕ፣ በአሁኑ ወቅት ወደ ሥራ የገቡና ሽያጭ ላይ ያሉት ስድስት ፕሮጀክቶች ናቸው። በክልል ከተሞችም ቢሾፍቱ፣ ዱከም፣ ጅማና ሆሳዕና መሬት አዘጋጅተው ወደ ግንባታ ለመግባት በዝግጅት ላይ ይገኛሉ።

አጠቃላይ በተቆጣጣሪነት የሚሠሩ ሠራተኞችን ጨምሮ 52 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለው አፍታ ሜይራ ግሩፕ ኃ/የተ/የግ/ማ፣ በቀጣይ ያቀዳቸውን ፕሮጀክቶች ዕውን በማድረግ በሥራ ዕድል ፈጠራ እንዲሁም ቴክኖሎጂን በመጠቀም በሪልስቴት ዘርፉ ትርጉም ያለውና ከስህተት የጸዳ ሥራ ለመሥራት ትልቅ ራዕይ ሰንቋል።

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆአስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ስለ ጤና - ከ‹‹ቡልቡል›› አዲስ አበባ...

መልካምሥራ አፈወርቅ



**እሳቸው...**

አባ ፋጂ አባቦር መልካም ገበሬ ናቸው። በሚኖሩበት የጅማ ‹‹ቡልቡል›› ቀበሌ ጉልበታቸው አያመርተው፣ እጃቸው አያፍሰው ምርት የለም። ጤፍና በቆሎ፣ በርበሬና ቡና፣ ሙዝና አቮካዶ የልፋታቸው ሲሳይ ናቸው። እሳቸው ዓመቱን ሙሉ የሚደክሙ ብርቱ ሰው መሆናቸውን ሁሉም ያውቃል። አባ ፋጂ ከትዳር አጋራቸው ሰባት ልጆችን ወልደዋል። ከልጆቻቸው መሀል በሞት ያጧቸውን ቢያስቡም በፈጣሪ ሥራ ገብተው አያውቁም። ‹‹ያሉትን ይባርክልኝ›› ብለው በምስጋና እየኖሩ ነው።

**ሰባተኛው ልጅ...**

አያንሺ ለአባፋጂ የመጨረሻና ሰባተኛ ልጅ ሆኖ ይቆጠራል። ዓይኑ ጎላ ያለ መልኩ ደማቅ ጥቁር ነው። ቀልጣፋና ሩጫ ወዳድ በመሆኑ ከእኩዮቹ ሲዘል ሲጫወት ይውላል። እንደ ልጅነቱ ነፃነቱን የሚጋፋው ጊዜውን የሚቀማው የለም። እንዳሻው ይሆን ዘንድ ተፈቅዶለታል። አሁን ልጁ አምስት ዓመት ሆኖታል። እሱን መሰል እኩዮቹን ሲያገኝ እንደለመደው ዘሎ ተጫውቶ ይገባል።

አንድ ቀን አያንሺ ሲዘል ሲጫወት ውሎ ከቤት ደረሰ። ገጽታው እንደቀድሞው አይደለም። ቅዝዝ እንዳለ ክፍት ብሎታል። እናት አባት ሁኔታውን ቢያዩ ደነገጡ። ልጃቸው ሳቅ ፈገግታው ከፊቱ የለም። ሆዱን ታቅፎ የሚያቃስተውን ታዳጊ እየዳሰሱ ምክንያቱን ጠየቁ።

አያንሺ ውሎው ከወንድሙ ጋር ነበር። ዕለቱን የነበሩበት ዝላይ ሁለቱንም አስደስቷል። በጨዋታ መሀል አያንሺ ድንገት መውደቁን ያስታውሳል። አወዳደቁ ከባድ ነበርና ፈጥኖ አልተነሳም። ደረቱን ሰቅዞ የያዘው ሕመም አላላውስ ብሎ ትንፋሽ አሳጥቶታል። ምግብ ለመቅመስም ሆነ ጥቂት ለማውራት አልቻለም። እንደተጨነቀ፣ እንዳለቀሰ ምሽቱን ገፋ።

ሁኔታውን ያስተዋሉ ብዙዎች ‹‹ይበጃል›› ስለእሱ ይበጃል ያሉትን ሃሳብ አመጡ። ልጁ ሕመሙ ሳይገፋበት በባህል መድኃኒት እንዲታይ ተመከረ። እናት ከተባለው ቦታ አድርሰው መድኃኒቱን ሞከሩለት። መፍትሔ አልተገኘም። ሕፃኑ ሆዱ እያበጠ፣ ውስጡ እየተጨነቀ ሰነበተ።

አያንሺ እግሮቹ እንዳሻቸው አይራመዱም። ክብደቱ በእጅጉ ቀንሷል። መንገድ ከጀመረ ችሎ መራመድ ይሳነዋል። እሱን አንስተው የሚሸከሙት በሰውነቱ መከሳት ይሳቀቃሉ። በልብስ ተሸፍኖ የሚውለው ሕፃን ደህና ቢመስልም አቅም እያጣ፣ ውስጡ እየደከመ ነው።

ከቀናት በአንዱ ወላጅ እናቱ አያንሺን ይዘው ጤና ጣቢያ ደረሱ። አዳሩ ጥሩ ባለመሆኑ ሲጨነቁ አርፍደዋል። ትንሹ ልጅ ከዚህ ቀድሞ እንዲህ አልሆነም። ቢወድቅ ይነሳል፣ ቢታመም ይድናል፣ የጤና ጣቢያው ባለሙያዎች ልጁን በወጉ አስተኝተው በጥልቅ መረመሩት። ሕመሙ በሚሰማው ቦታ የቆሰለና የደማ ነገር የለም። ጨነቃቸው።

ጥቂት ቆይቶ ወደ ጅማ ሪፈራል ሆስፒታል ሊጻፍለት ግድ ሆነ። እናት አሁንም ልጁን ይዘው ከሐኪም ፊት ቀረቡ። ችግሩ መወደቁ ብቻ መሆኑን አስረድተውም መፍትሔን ጠበቁ። የሆስፒታሉ ሐኪሞች ከቀድሞው በተሻለ ምርመራቸውን ቀጠሉ። አያንሺ ለተከታታይ ሁለት ወራት አልጋ ይዞ ታከመ።

ቆይታው ሲጠናቀቅ ሐኪሞች እሱን ከበው ዳግም መከሩ። የአሁኑ ምክራቸው ከቀድሞው የተለየ ይመስላል። አሁን የሐኪሞቹ ቡድን ታዳጊው ወደ አዲስ አበባ እንዲሄድ ወስኗል። ይህን ትዕዛዝ የተቀበሉት ቤተሰቦች ትንሹን ልጅ ከተባለው ሰፍራ ለመውሰድ ዓይናቸውን አላሹም።

**አዲስ አበባ...**

አዲስ አበባ ለአባት አባ ፋጂ ሩቅና አዲስ ነው። ከዚህ ቀድሞ ወደዚህ ቦታ ያመጣቸው አንዳች ምክንያት አልነበረም።‹‹ለሀገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ›› የሆኑት ፋጂ መድረሻቸው የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሆነ። በእጃቸው ያለው ታዳጊ ዛሬም ታሟል። ራሱን ችሎ ለመራመድ፣ ምግብ አላምጦ ለመዋጥ እያቃተው ነው።

አያንሺ ስፍራው እንደገባ ፈጥኖ አልጋ አላገኘም። ኮሪደሩ ላይ በተገኘው ማረፊያ ተኝቶ ቀናትን ሊጠብቅ ግድ አለው። ጉሉኮስ እየወሰደ ጥቂት የዘለቀው ታዳጊ መኝታው ሲገኝለት መደበኛ ሕክምናውን ቀጠለ።

**የምርመራው ውጤት**

ውሎ አድሮ አባ ፋጂ የልጃቸው ሕመም የደም ካንሰር መሆኑ ተነገራቸው። እሳቸው ከዚህ ቀድሞ ስለዚህ ሕመም የሰሙት ነገር አልነበረም። እሱን መሰል ልጆች በሕመም ሲሰቃዩ ግን ችግሩ ከፍ ያለ መሆኑ ገባቸው። አባት ስለ አያንሺ ብዙ ሲያስቡ ቆይተዋል። በትምህርቱ ልቆ፣ ከፍ ያለ ደረጃ እንዲገኝ ይመኛሉ። በወጉ ቁርዓን ቀርቶ ሃይማኖቱን እንዲያከብር ይሻሉ።

አባት እውነቱን ካወቁ በኋላ ድንጋጤና ሀዘን ዋጣቸው። ሕክምናው ጊዜ የሚፈልግ ዓመታትን የሚጠይቅ መሆኑ ሲነገራቸው ደግሞ የትንሹ ልጃቸውን ሕይወት ለመታደግ ተዘጋጁ። የሕመሙን መላቅና የሚያስፈልገውን ወጪ ባወቁ ግዜ ሁሉን የመሸፈን አቅሙ እንደሌላቸው ተናገሩ። ደግነቱ ሕክምናውን በሀገር ውስጥ ማካሄድ ይቻላል ተባሉ ። የመድኃኒቱ ዋጋ ቢበዛም ከልጃቸው ሕይወት የሚበልጥ አልሆነባቸውም።

አያንሺ ክፍሉን ቀይሮ ሕክምናውን መከታተል ጀመረ። የኬሞው ሕክምና ከአቅሙ በላይ ነበር። ገና ሲጀምረው ውስጡ ይዳከማል፣ ምግብ ይጠላል፣ ጸጉሩ እየረገፈ ገጽታው ይገረጣል። ከጀርባ አጥንቱ የሚወሰደው ናሙና ለትንሹ ልጅ እጅግ የከፋ ስቃይ ነበረው።

ትንሹ አያንሺ ዕድሜው ከፍ ሲል ያቋረጠውን ትምህርት መቀጠል ይፈልጋል። እንደ እኩዮቹ ደብተር ይዞ ትምህርት ቤት መመላለስ፣ ፊደል መቁጠር፣ በመዝሙር መዝናናት ምኞቱ ነበር። ይህ እንዳይሆን አሁን ከአልጋ ውሏል። በየቀኑ የሚወሰደው ሕክምና አቅሙን እየፈተነው ነው። አዛውንት አባቱ ዛሬም ከጎኑ ናቸው። እሱን ለማሳከም ብዙ ዋጋ እየከፈሉ፣ በርከት ያለ ገንዘብ እያወጡ ነው።

ዛሬም ትንሹ ልጅ ሕክምናውን ቀጥሏል። የመዳን ተስፋ ስለተሰጠው ቤተሰቡ በጎ እያሰበ ነው። አባት ወራት በፈጀው ቆይታ ከዕለት ሥራቸው ርቀዋል። ጠንካራው ገበሬ ዛሬ ከእርሻቸው አይውሉም። ከገጠር አዲስ አበባ መመላለሱ ቢርቅም ከብዷቸው ግን አያውቅም። ሁሉን ስለእሱ ይችሉታል፣ይወጡታል።

**የአባት ተስፋ...**

አባ ፋጂ ከዚህ ቀድሞ ልጆችን ቀብረዋል። ዛሬ ግን የዓይናቸውን ማረፊያ ትንሹን አያንሺን ማጣት አይፈልጉም። የቻሉትን እያደረጉ ፈጣሪን ይማጸናሉ። ብዙ የደከሙለት ልጅ አሁን ዓይኑን እየገለጠ ነው። ያሳለፈው ስቃይና መከራ በቀላሉ አይወሳም። በርካታ የጭንቅ ቀናት ጥቂት የማይባሉ የሕመም ሌሊቶችን ገፍቷል። አባት ስቃዩን ሲጋሩ፣ ችግሩን ሲካፈሉ ከርመዋል። አሁን ያዩበት ተስፋ ግን የነገ ህልማቸውን ዕውን የሚያደርግ ነው።

አያንሺ ከሕመሙ አገግሞ ቀጣዩን ሕክምና ለመከታተል ማረፊያ ያስፈልገዋል። ለመድኃኒቱ መግዣ በየጊዜው የሚስፈልግ ገንዘብ ቀላል አይደለም። ከሆስፒታል ወጥቶ ቤት ለመከራየት የዕለት ወጪ ለመሸፈን አቅም ይጠይቃል። አባ ፋጂ ‹‹አለንህ›› የሚል ወዳጅ ዘመድ ከጎናቸው የለም።

አሁን ትንሹ አያንሺ ሰባት ሊሞላው ነው። ይህ ጊዜ ክፉና ደጉን የሚለይበት፣ ቁምነገር ማሰብ የሚጀምርበት ነው። ሁሌም የሚያስበው የትምህርት ጉዳይ ዛሬም ከውስጡ አልጠፋም። እሱ ተምሮ ሲጨርስ ዶክተር መሆን ይፈልጋል፣ ሐኪም መሆኑ የታመሙ ወገኖችን አክሞ ለማዳን ያግዘዋል።

አያንሺ ሆስፒታል በቆየባቸው ጊዚያት የሐኪሞችን ዋጋ አስተውሏል። ሙያው የታመመ የሚድንበት፣ ተስፋ የቆረጠ ውስጡ የሚለመልምበት ስለመሆኑ በራሱ የጤና ለውጥ እያረጋገጠ ነው። አንድ ቀን እሱም ማዳመጫውን በጆሮ ሰክቶ፣ ነጭ ካፖርቱን ደርቦ ጥቁሩን ጨለማ እንደሚገፍ ተስፋ አለው። ትንሹ አያንሺ ግን ዛሬም ከአልጋው እንደተኛ ነው። ነገን አላሚው ሕፃን ፍጹም ተስፋ አይቆርጥም። እንደሚድን ያውቃልና ዕቅዱ ሰፊ፣ ዓላማው ታላቅ ሆኗል።

**የጸሎቱ መልሰ...**

አሁን አባትና ልጅ ከሆስፒታል የሚወጡበት ጊዜ ደርሷል። ለእንግዳው ሰው፣ ታማሚ ልጅ ለያዘው አባት እንዲህ መሆኑ ይከብዳል። ሁሌም ግን አባት ፋጂ ወደፈጣሪያቸው ይጮሀሉ እንደማይጥላቸው ያወቃሉና ተስፋ ቆርጠው አያውቁም። አንድ ቀን ችግራቸውን ቀርበው ያዋይዋቸው ልበ መልካሞች ለጥያቄያቸው መፍትሔ አላጡም። በዚህ መሰሉ ችግር የሚመላለሱ፣ ግራ ገብቷቸው ማረፊያ ያጡ እንግዶች የሚያርፉበትን አንድ ስፍራ ጠቆሟቸው።

አባት ብቻቸውን አይደሉም። ገና በወጉ ያላገገመ ትንሽ ልጅ አብሯቸው አለ። የሰሙትን ሁሉ ተጠራጠሩ። እንዴት ሲሉም ከራሳቸው ሞገቱ። ይህ ስጋት ግን ከእሳቸው አላለፈም። እንዲሄዱ የተጠቆሙበት ቦታ እሳቸውና አያንሺን የመሰሉ የካንሰር ሕሙማን ሕፃናት እንደቤታቸው የሚያርፉበት ዕልፍኝ ነበር።

አባ ፋጂና ትንሹ አያንሺ ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ወጥተው ወደ ማቲዎስ ወንዱ የካንሰር አሶሴሽን ግቢ አመሩ። ስፍራው ሲደርሱ የጠበቃቸው አቀባበል የሰጉበትን ችግር ሁሉ አስወገደ። በዚህ ቦታ አያንሺን መሰል ሕፃናት የካንሰር ሕሙማን አርፈው ይስተናገዳሉ።

ማንኛውም እንግዳ ይህ ማዕከል ቤቱ ነው። የምግብ፣ የመኝታ የአምቡላንስና የትራንስፖርት አገልግሎት ባሻው ጊዜ ጥያቄው ሁሉ ይሟላለታል። ለመድሃኒት መግዣ እጃቸው ያጠረ ወላጆች ይህ ድርጅት የቀን መከታቸው ነው። ከተለያዩ ክልሎች መጥተው ሕክምና የሚከታተሉና በቂ ማረፊያ የሌላቸው ወላጆችና ልጆቻቸው በዚህ ቦታ አርፈው ሕክምናቸውን ይከታተላሉ። በሐኪም ቀጠሯቸው ቀን ስፍራው አድርሶ የሚመልሳቸው መኪና ሁሌም ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃቸዋል።

ይህ ቤት እስከ ዛሬ በርካታ እንግዶችን ተቀብሎ አስተናግዷል። በዚህ ስፍራ ዕንባቸው የታበሰ፣ ችግራቸው የተወገደ በርካቶች በምስጋና ይመላለሱበታል። አያንሺና አባቱ በዚህ ቤት ማረፍ የጀመሩት ከዛሬ ስድስት ዓመት በፊት ነበር። አያንሺ ከእሱ ጋር የነበሩ እኩያ ጓደኞቹ በጊዜ ቆይታ በሞት እንደተለዩት ያስታውሳል። ይህን ሲያስብ በእሱ ሕይወት መቀጠል ፈጣሪውን እያመሰገነ ነው። አሁን እሱና አባቱ በዚህ ቤት ከቤተሰብ በላይ ናቸው። በዚህ ስፍራ ከችግር አምልጠዋል፣ የክረምቱን ጎርፍ፣ የበጋውን ሀሩር አሳልፈዋል።

ዛሬ አያንሺ የአስራ አንድ ዓመት ታዳጊ ነው። ተከታታይ የሕክምና ቀጠሮ ባለው ጊዜ ከአባቱ ጋር ከጅማ አዲስ አበባ ይመላለሳል። ከሆስፒታል መልስ አረፍ የሚለው ደግሞ በዚህ ማዕከል ነው። ትናንት በክፉ የሚያስታውሰው አስጨናቂ የሕመም ጊዜ በሕክምናው ክትትል መፍትሔ አግኝቷል።

ታዳጊው ጤናው በተመለሰ ጊዜ ትምህርቱን አልዘነጋም። ጓደኞቹ ጥቂት ቢቀድሙትም ትምህርት ቤት ገብቶ ሶስተኛ ክፍል ደርሷል። ዛሬም ዶክተር የመሆን ህልሙ አልደበዘዘም። ሕመምተኞችን አክሞ የማዳን፣ ብዙሃንን የመጥቀም ህልሙ ዕውን እንደሆነ ቀጥሏል።

የአያንሺ እህት ወንድሞች ስለእሱ ያላቸው እይታ ይለያል። ሁሌም ትንሹ ወንድማቸው በጤና ቆሞ ማየትን ይሻሉ። በትምህርቱ የበረታ በሃይማኖቱ የጠነከረ እንዲሆንም ከጎኑ ናቸው።

**ትናንትናን በትውስታ ...**

አያንሺ ሲናገር አፉ እንደ ሕፃን ይጣፍጣል፣ የዋህነቱም ከገጽታው ይነበባል። ሮጦ ያልጠገበው ልጅነቱ በሕመም ፈተና ቢያዝም በየምክንያቱ ሰበብ ፈልጎ አይከፋም። ሁሌም ካገኘው ጋር ተግባቢ ነው። ከዓመታት በፊት የነበረውን ስቃይ ዛሬ በትውስታ የሚያነሱት አባት ፋጂ በተለይ በኬሞ መውሰድ ጊዜ የነበረበትን የከፋ ስቃይ አይዘነጉም።

የዛኔ ከቤተሰቡ በቅርብ የተገኙት ብቸኛው ሰው እሳቸው ነበሩ። ያለ ምግብና ውሃ ሕመምን ማስተናገድ ለትንሹ ልጅ የከፋ ስቃይ ነበር። የሰውነቱ መከሳት፣ የእጆቹ መላላጥ፣ የአካሉ መጎሳቆልና አቅም ማጣት ማንነታቸውን ፈትኖ ከጭንቀት ጥሏቸው እንደነበር ሲያስታውሱ ዛሬ የሕልም ያህል ይታያቸዋል።


**ዛሬን ...**

አሁን አያንሺ ፍጹም ደስተኛ ነው። አዲስ አበባ ደርሶ በተመለሰ ቁጥር የሚያስበው ስለትምህርቱ ሆኗል። ከልጅነቱ በውስጠቱ የሰረጸው ጽኑ ዓላማ በፈተናዎች እንደማይረታ ለራሱ ነግሮታል።

አባት ፋጂ ስለልጃቸው ሕክምና ገንዛቤ ወስደዋል። መድኃኒቱ ቢቋረጥ፣ ሕክምናው ቢዘገይ የሚመጣውን አደጋ አሳምረው ያውቁታል። እሳቸው ስልጃቸው የከፈሉት ዋጋ አይቆጫቸውም። እንደውም ለሌሎች ወላጆች ምሳሌ ሆነው በርካቶችን አስተምረዋል።

አሁን አያንሺ እያደገ ነው። ትናንት ያለፈበት የጤና ችግር በእሱ መዘናጋት እንዳይመለስ ሕክምናው ላይ ጥሩ የሚባል አስቤ አለው። ከጅማ አዲስ አበባ ሲመላለስ በምክንያት መሆኑን ያወቃል። ነገ ስለአባቱ ታላቅነት ቆሞ የሚመሰክረው እሱ በጤናወ መቆም ሲችል መሆኑ አይጠፋውም። እናም አያንሺ ብርታት መለያው ሆኗል። የዛሬን ጨለማ አንግቶ ነገን በድል ለመሻገር ከራሱ ጋር በጽናት ይታገላል። አያንሺ ትንሹ፣ ብርቱው ብላቴና።

# ስፖርት



# የማራቶን እንቁዋ የኦሊምፒክ ህልም

**ብርሃን ፈይሳ**

ሶስት ወራት ብቻ ለቀሩት 33ኛው የፓሪስ ኦሊምፒክ ሀገራት አስቀድመው ቡድናቸውን ማሳወቅና ማዘጋጀት ጀምረዋል። ከእነዚህ መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ስትሆን በተወሰኑ ርቀቶች የመጀመሪያ ምርጫ ውስጥ የተካተቱ አትሌቶች ጥሪ እንደተደረገላቸው ይታወቃል። በኦሊምፒክ መድረክ በአትሌቲክስ ስፖርት በስኬታማነት ተጠቃሽ የሆነችው ኢትዮጵያ በተለይ ለውጤታማነት ከምትጠበቅባቸው ርቀቶች መካከል አንዱ ማራቶን ነው። በዚህ ርቀትም አትሌቶች ሀገራቸውን ለመወከል እንዲያስችላቸው በተለያዩ ውድድሮች ተሳትፈው ምርጥ ሰዓትን ለማስመዝገብ የግል ጥረታቸውን በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በሴቶች ማራቶን በዓለም አቀፍ ደረጃ በአስደናቂ ብቃታቸው በቀዳሚነት ከሚነሱ አትሌቶች መካከል አንዷ የሆነችው ጎይተቶም ገብረሥላሴም፤ በዚህ ኦሊምፒክ ለመመረጥ የሚያስችላትን ሰዓት ለማስመዝገብ ጥረቷን አጠናክራ ቀጥላለች። እአአ በ2022 በኦሪጎን የማራቶን የዓለም ቻምፒዮን የነበረችው አትሌት በቀጣዩ ዓመትም ቡዳፔስት ላይ በርቀቱ የብር ሜዳሊያ ማጥለቋ የሚታወስ ነው። እአአ የ2021 የበርሊን ማራቶን አሸናፊዋ አትሌት ከዓለም ቻምፒዮና መልስ በስፔን እና የተባበሩት አረብ ኤሜሬትስ በተካሄዱ ሁለት የግማሽ ማራቶን ውድድሮች ላይ ተካፍላ ውጤታማ መሆን ችላለች።

በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆናም ሀገሯን በማስቀደም ለድል የምትተጋው ጠንካራዋ አትሌት ጎይተቶም ህልሟ በፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ ማውለብለብ ነው። ለዚህ እንዲያግዛትም በተያዘው የውድድር ዓመት በተለያዩ ውድድሮች ላይ በመካፈል ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ በቡድኑ የመካተት ጥረቷን አጠናክራ ቀጥላለች። የተያዘውን የውድድር ዓመት በጃፓን ንጎያ ማራቶን ላይ የጀመረች ቢሆንም እንደተጠበቀው ውድድሩን መፈጸም ባለመቻሏ አቋርጣ መውጣቷ የሚታወስ ነው።

ሩቅ አላሚዋ ብርቱ አትሌት በአንድ ወር ልዩነት ቀጣዩን ተሳትፎዋን ከቀናት በፊት በጀርመን በተካሄደው የሃምበርግ ማራቶን ማድረግ ችላለች። በዚህም 2ሰዓት ከ21 ደቂቃ ከ18 ሰከንድ በሆነ ሰዓት በመሮጥ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ ማጠናቀቅ ችላለች። አትሌቷ በዚህ አቋሟ ሀገሯን በታላቁ የኦሊምፒክ ውድድር ላይ ከመወከል ባለፈ በታሪክ ማህደር ስሟ የሰፈረ ስኬታማ አትሌት የመሆን ምኞቷ ገና በጅምር ላይ መሆኑን ነው የምትገልጸው። የ29 ዓመቷ ጎይተቶም ከዓለም አትሌቲክስ ጋር በነበራት ቆይታ ያለመችውን ታሪካዊ አትሌትነት ስኬት ለማጣጣምም ፓሪስ ላይ ውጤት ማስመዝገብ እንዳለባትም እምነቷ ነው።

‹‹ኢትዮጵያ እና ሩጫ የተሳሰሩ ናቸው›› የምትለው አትሌቷ ታላቁ አትሌት አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሀገሩን ወክሎ በመሮጥ ውጤት ማስመዝገቡን ለዚህ እንደ ማሳያ ታነሳለች። ‹‹እኔም አትሌት በመሆኔ እጅግ ከፍተኛ ደስታ ይሰማኛል። ኦሊምፒክን ሳስብ የአትሌቶች ሁሉ የመጨረሻ ግብ እንደሆነ ነው የምረዳው›› ስትልም የአትሌትነት ሕይወት ግቧ የኦሊምፒክ ሜዳሊያን ማጥለቅ ስለመሆኑ ታስረዳለች። ከኢትዮጵያ ታሪካዊ አትሌቶች መካከል አንዷ የሆነችው ጥሩነሽ ዲባባ አድናቂ ስትሆን በተለይ እአአ በ2008 ቤጂንግ ኦሊምፒክ በ5ሺ እና 10ሺ ሜትር ሁለት የወርቅ ሜዳሊያዎችን ያጠለቀችበት ውድድር ሁሌም ከትውስታ ማህደሯ አይሰረዝም።

ይህንን ስኬት ለማጣጣም ትጋቷን አጠናክራ የቀጠለችው ጎይተቶም ‹‹በርግጥ እኔም በዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና አሸናፊ በመሆን ሀገሬን ለስኬት አብቅቻለሁ። የዓለም አትሌቲክስ ድልም በአትሌቶች ዘንድ ትልቅ ዋጋ ያለው ነው። ነገር ግን ይህንን ስኬት በኦሊምፒክ በመድገም ህልሜን እውን ለማድረግ ጠንክሬ እየሠራሁ ነው›› ስትልም ትናገራለች። በሩጫ ስኬታማ ለመሆን የግል ጥረት ብቻውን በቂ አለመሆኑን የምትገልጸው አትሌቷ፤ በልምምድም ሆነ በውድድር ወቅት ጠንካራ አትሌቶች መኖራቸው በእጅጉ ያግዛል። ምንም እንኳን የአትሌቶቹ



በፓሪስ ኦሎምፒክ ተጠባቂ ከሆኑ ሴት የማራቶን ሯጮች መካከል አንዷ አትሌት ጎይተቶም ገብረሥላሴ ናት፤

አቅም የሚመጣጠን ባይሆንም አንዱ ሌላውን በመመልከትና በመካከላቸው የፉክክር መንፈስ በመፍጠር ማጠንከር እንደሚችል በመግለጽም፤ የተፎካካሪዎቿን አትሌቶች ጥቅም አብራርታለች።

ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

**ከኢፌዴሪ ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀኑ የሚታተም**

# የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ-ግብር ቅድመ-ዝግጅት

**ዮሐንስ ደመቀ**

ግብርናችን ከዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ ውጭ አይደለም፡፡ የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ቀጣይነትን ለማረጋገጥና ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም የተፈጥሮ ሀብታችንን ማልማት፣ መንከባከብ እና በአግባቡ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓለማችን ኃያላን ሀገራትን ጨምሮ እያስጨነቀ ያለው ጉዳይ የዓለም ሙቀት መጨመር ነው፡፡ ይህም ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እያስከተለ ይገኛል፡፡ የቀውሱም መነሻ ከፍተኛ በሆነ በካይ ጋዝ ልቀት እና በሌሎችም ተያያዥ ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት እንደሚከሰት ጥናታዊ መረጃዎች ያሳያሉ።

የችግሩም ገፈት ቀማሽ ሀገራት በተለይ ታዳጊ የሆኑት ከድህነት ጋር ተደምሮ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖባቸዋል፡፡ ድርቅ፣ ያልተጠበቀ የጎርፍ መጥለቅለቅ እንዲሁም ተያያዥ ተፈጥሯዊ አደጋዎች የችግሩ መገለጫዎች ናቸው፡፡ ለዚህም ችግር መፍትሔ አረንጓዴ ልማት ዋነኛ አማራጭ እንደሆነ ሁሉም የሚረዳው ሃቅ ነው፡፡

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ላለፉት ዓመታት የተጨበጠ ለውጥ ለማምጣት በርካታ ሥራዎችን እየሠራች ትገኛለች፡፡ ከነዚህም መካከል ታሪካዊ የአረንጓዴ ዐሻራ ቀን ልማት አተገባበር አንዱ ነው፡፡ ይህ ከሀገርም አልፎ በዓለም ደረጃ ስሟን በክብር መዝገብ ያስቀመጠችበትና በርካቶችን ያስደመመችበት ነው፡፡ ውጤቱ የተገኘው እንደ ሀገር በርካታ ተቋማት ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት ሆነው በመሥራታቸው ነው፡፡





ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለችው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ-ግብር አህጉራዊ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ሥርዓትን ለመገንባት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያበረክት ነው። ሀገር አቀፉ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ-ግብርም ሀገራቸውን ለመለወጥ ጉልበትና ገንዘባቸውን ፈሰስ እያደረጉ በሚገኙ ትጉህ ኢትዮጵያዊያን እየተከወነ የሚገኝ ቀና ተግባር ነው። በመርሃ-ግብሩ ለመድኃኒትነት የሚውሉ ሀገር በቀል ዛፎችን ጨምሮ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው እጽዋቶች የሚተከሉ ሲሆን በመርሃ-ግብሩም ኢትዮጵያውያን ተግተው እያሳኩት የሚገኝ አንጸባራቂ መርሀ ግብር ነው።

ኢትዮጵያ “አረንጓዴ ዐሻራ” ብላ የሰየመችው የችግኝ ተከላ መርሃ ግብር ማካሄድ የጀመረች በ2011 ዓ.ም ነው፡፡ ከ2011 ዓ.ም እስከ 2014 ዓ.ም ባካሄደችው የመጀመሪያ የችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 25 ቢሊየን ችግኞች ተተክለዋል፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ የተጀመረ ሲሆን በዚህኛው ምዕራፍም 25 ቢሊየን ችግኝ ለመትከል ታቅዷል፡፡

የ2016 ዓ.ም የአረንጓዴ ዐሻራ የቅድመ-ዝግጅት እና የቀጣይ የሥራ አቅጣጫዎች ላይ ብሔራዊ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ዐቢይ ኮሚቴ በቅርቡ የምክክር መድረክ አካሂዷል።

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ብሔራዊ ዐቢይ ኮሚቴ አስተባባሪ እና የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ(ዶ/ር) የመድረኩን አላማ ሲያብራሩ፤ የ2016 ዓ.ም የችግኝ ተከላ የቅድመ ዝግጅት ምዕራፍን መገምገም እና ቀጣይ የሥራ አቅጣጫዎች ላይ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም በተካሄደው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር 7 ነጥብ 5 ቢሊዮን የደን እና የፍራፍሬ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው ችግኞች መተከላቸውንም አስታውሰዋል። ሚኒስትሩ አያይዘውም በተካሄደ የዳሰሳ ጥናት የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ የጽድቀት መጠናቸውን 90 ከመቶ ማድረስ እንደተቻለም ገልጸዋል፡፡

ለዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር 6 ነጥብ 5 ቢሊየን ችግኝ ለመትከል ዕቅድ መያዙን ሚኒስትሩ ጠቅሰው ለዚህም 7 ነጥብ 2 ቢሊየን ችግኝ መዘጋጀቱን ተናግረዋል። በአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ለሚተከሉ ችግኞችም በሀገር አቀፍ ደረጃ 1 ነጥብ 2 ሚሊየን ሄክታር መሬት ለተከላ መዘጋጀቱንም ገልጸዋል። ለዘንድሮው ዓመት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በቂ ቅድመ-ዝግጅት ተደርጓል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በመጪው ክረምት ለሚካሄደው የችግኝ ተከላ ቀሪ ሥራዎች ላይ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ የግብርና ሚኒስትሩም ዶ/ር ግርማ አመንቴ ለዐቢይ ኮሚቴው ቀጣይ የሥራ አቅጣጫዎች ላይ መመሪያ ሰጥተው፤ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሶ መድረኩ ተጠናቋል፡፡